
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር- 7ኛ ዓመት ቁጥር 3 ሰኔ/ሐምሌ



ደብረብርሃን ሥላሴ /ሰሜን ሸዋ/

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## አፋጣኝ ምላሽ...

በከተማችን ውስጥ የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስና የቅዱስ ሚካኤል አብያተ ክርስቲያናት አሉ:: በሁለቱ አብያተክርስቲያናት መካከል ባሉ ካህናት መካከል ከፍተኛ አለመግባባት አለ:: በዚህ የተነሣ ብፁዕ አባታችን አቡነ በርተሎሜዎስ በገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን የሚገኙ ካህናትን ሥልጣነ ክህነት በመያዝ ከሥራ አግደዋቸው ነበር:: ነገር ግን ካህናቱ ሥልጣናችን አለአግባብ ነው የተያዘው በማለት ቅዳሴና ሌሎች አገልግሎቶችን በመፈጸም ላይ ናቸው:: ለምን ሲባሉ አዲስ አበባ ሄደን ይግባኝ በመጠየቅ እንዲመለስልን አድርገናል ይላሉ:: ይህ ደግሞ ለምእመናኑ መረበሽን ፈጥሯል:: የሚመለከተው ክፍል ለዚህ አፋጣኝ ምላሽ ቢሰጥበት መልካም ነው::

*ገድል ሽብሩ*
*ዲላ*

## ቤተክርስቲያን ተረካቢ ይኖሯታልን?

የነገዋን ቤተክርስቲያን ለመረከብ ወሳኞቹ የዛሬ ሕፃናት እንደ ሆኑ ይታወቃል:: ታዲያ እነዚህ ሕፃናት ቤተክርስቲያንን ሲረከቡ እንደ አያታቸው እንዲሆን ከዛሬው ልናስተምራቸው ይገባል:: እውነቱ ያ ሆኖ ሳለ ዛሬ ዛሬ በየከተማው ወላጆች ልጆቻቸውን የነሮናልዶንና ዚዳንን እንዲሁም ታዋቂ የፊልምና የሙዚቃ ሰዎችን ማስተዋወቅ እንጂ ቅዱሳንን እንዲወዱ የቤተክርስቲያን ፍቅር እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ወላጆች ጥቂቶች ናቸው:: ገጠርም ቢሆን በልካቸው ዱላ እየቆረጡ እየሰጡ እገሌን በዚህ ከሽ አድርገኸው ና እያሉ ዱላንና ስድብን እንዲሁም መጠጥን ማስለመድ እንጂ እጆቻቸውን ይዘው ቤተክርስቲያን በመውሰድ የሚያስለምዱ በጣም ጥቂቶች ናቸው:: ታዲያ ዛሬ ይህ ሁሉ እየተደረገ ነገ ቤተክርስቲያን ተረካቢ ይኖራታልን?

*ደጀኔ በላይ*
*ከዩ/ቅ/ገ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት*

## እንታቀብ

ቤተክርስቲያን ልጆቿን ከምታቅፍባቸው እጆቿ አንዱ ሰንበት ት/ቤት ነው:: ዛሬ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁንና ወጣቶች በየሰንበት ት/ቤታቸው በሚሰጡ ትምህርቶች ቤተክርስቲያናቸውን እያወቁ ራሳቸውንም ከመናፍቃን ንጥቂያ እየጠበቁ ነው:: ነገር ግን በአንዳንድ ሰንበት ት/ቤቶች የሚማሩ ወጣቶች ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ የማይገቡ ዓለማዊ ስዕሎችን በመሳልና በመለጠፍ ይመላለሳሉ:: ማስታወሻ መያዛቸው ባልከፋ:: ነገር ግን ስዕላቱ ከማስታወሻ ደብተሮቹ ዓላማ ጋር ፈጽሞ የማይሄዱ በመሆናቸው ይህንን የሚሠሩ ወጣቶች ተወቃሾች ናቸው:: ወጣቶች ወደ ሰንበት ት/ቤታቸው የሚሄዱት የቤተክርስቲያናቸውን ትምህርት በንጹህ መንፈስ እንዲማሩ እንጂ ሀሳብን የሚሰርቁ ስዕላትን እያዩ ሀሳባቸው እንዲከፈል አይደለምና ይህንን የምንሠራ ወጣቶች እንታቀብ::

*ቴዎድሮስ ፍቃዱ*
*ሞጆ*

## በተቀደሰው ቦታ ርኩሰት

እኔ በምኖርበት አካባቢ አንዳንድ ምዕመናን የቤተክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ እንዲሁም ካህናት በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ ከመቅደሱ 40 ክንድ ባልሞላ ቦታ ላይ በሬ÷ ላም÷የመሳሰሉትን እንስሳት እያረዱ ቅርጫ ይከፋፈላሉ:: ለመሆኑ ቤተክርስቲያናችን የተቀደሰች ሰዎችም የሚቀደሱባት እንጂ የቅርጫ መከፋፈያ ቦታ ነችን? ደግሞስ ቅድስት ቤተክርስቲያን ልጆቿ የምንሆን እኛ መሰባሰቢያ እንጂ ፈርስና የወዳደቁ ሥጋዎችን አሽትተው የሚመጡ ውሾች፣ ጅቦችና ጭልፊቶች መሰባሰቢያ ናትን? እባካችሁ ወገኖቼ በሌሎች ቦታዎችም ሆነ በእኔ አካባቢ እያወቅን በድፍረት ሳናውቅ በስህተት ይህንን የምንሠራ ካለን ስህተታችንን እናርም:: በተቀደሰው ቦታ የጥፋት ርኩሰት መሥራት አይገባምና::

*ገዛኸኝ ኃይሉ*
*ገርበ ጉራቻ*

## መዋዋስ ኃጢአት ነውን?

የሐመር መጽሔት ስርጭት ከማነሱ የተነሣና አንዳንዶቻችን ደግሞ ከዐቅም ማነስ የተነሣ እንደልብ አናገኘውም:: ከገዙትና ከሚያገኙት ተውሰን እንዳናነበው አናውስም፣ ይኸ ቅርስ ነው ብለው በሳጥናቸው ይቀብሩታል:: ማስቀመጣቸው ጥሩ ነው:: ነገር ግን መዋዋሱ ኃጢአት ነውን? መጽሔቱስ ሲዘጋጅ በተቻለ ዐቅም የቤተክርስቲያን ምእመን ሁሉ ገዝቶም ሆነ ተውሶ አንብቦ በሃይማኖቱ እንዲጠበቅ አይደለምን?

*አስረስ ገ/መድኅን*
*ቴፒ ቅ/ጊ/ሰ/ት/ቤት*

## ገጠመኜ

በእኔ ትጋት ሳይሆን እግዚአብሔር በቸርነቱ ደግፎኝ ከኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የዲፕሎማ ምሩቅ ነኝ:: ታዲያ በምረቃዬ ዕለት የገጠመኝን ሳስበው አጅግ አደነቃለሁ:: መቼም የምረቃ በዓል ከተመራቂው የበለጠ የምሩቁ/ቋን ቤተሰቦች እንደሚያስደስት ብዙዎች በምረቃ ሕይወት ያለፉ ያምናሉ:: እና እኔም የምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ደስታዬን ለመካፈል ኮሌጅ ከተገኙት ዘመዶቼ ጋር በኮንትራት ታክሲ ወደ ሰፈር ስሄድ በዝናብ የተጉራረደውን የኮተቤ መንገድ በቀስታ ስማለፍ ከተደረደሩት መኪኖች ተራ ገብተን ቆመን እንዳለ፤ አንድ የራሱን ባህል ትቶ የፈረንጆቹን ድሪቶ ባህል ሲሰብስ የሚሻማ «ጅል» በመስኮት ጠጋ ብሎ «ከኮተቤ ዲፕሎማ ሁለተኛ መንጃ ፈቃድ ይሻላል» አለ:: የመመረቂያ መገለጫ የሆነውን ጥቁር ልብስ (ገዋን) ለብሼ፣ የተበረከቱልኝን አበባዎች ታቅፌ ከፊት ወንበር የተቀመጥኩት ምሩቅና በመመረቄ ተደስተው ከኋላ አጅበው የተቀመጡት ዘመዶቼ የዚያን ወጣት «እንትን» ሰማን:: እኔና የተወሰኑት ዘመዶቼ በልጁ «እንትንነት» ሳቅን፤ የተወሰኑት ደግሞ ወርደን እንማታ አሉ::የሆነው ሆኖ በዚያች መኪና ውስጥ የነበርን ዘመዳሞች ገልጋይና ተገልጋይ ሆነን በመቆየት ተራችን ደርሶ የተጉረደውን መንገድ አልፈን ወደ ቤታችን ሄድን:: እኔ ዛሬ እሥራ ላይ ነኝ:: ያ በዝናብ መንገድ ለመንገድ ሲዞር የነበረው «እንትን» ወንድሜስ?

*ይገርማል*
*/ከፈለገ ብርሃን/*

ስምልክትም ያኔ ያስገቧቸው አንዳንድ የዘፈን መሣሪያዎች ዛሬ ድረስ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ተቀምጠው ይገኛሉ:: እንደ እነርሱ አስተሳሰብማ እነዚህ የዘፈን መሣሪያዎች ገብተው ብዙ ዕድሜ ካስቆጠሩ የሚመጣው ትውልድ እንደ ትውፊታዊ የዜማ መሣሪያ ይቀበላቸዋል ብለው ነበር:: ሁለተኛም ጥንታዊ እና፣ ምሥጢራዊ የቤተክርስቲያናችን መለያ የሆኑትን የዜማ መሣሪያዎች ለማረሳሳት እና ኦርቶዶክሳዊ ማንነትን ለማሳጣት አንዱ ዘዴ ነው በማለት ነበር::

/የማኅበሩ መልእክት ገጽ 2/



*በራሴ በኩል በብዙ መከራ ተፈትኛለሁ:: ገና በተማሪነት ሕይወቴ ነቀርሳ በተባለው በሽታ ተይዤ ጉሮሮዬ ውሃ አያፈስስ ልብሴን አያበሰብስ ለሰባት ዓመታት ያህል በእጅጉ ተሰቃይቻለሁ:: በዚያ ጊዜ ተስፋ የማይደርገው ሞትን ስለነበር እጅግም አይሰማኝም ነበር:: የተሰማኝ በጣም በጣም አሁኑኑም በዓይኔ ተስሎ አያስቸግረኝ ያለ ጉዳይ የአባቶቼ አወዳደቅ ነው::*

*/ቃለ መጠይቅ.. ገጽ 14/*

*የዜና ማርቆስ ገዳምን ለማየት የሚጓዝ ሰው ሁለት ፈተናዎች ከፊቱ ይጠብቁታል:: ሜዳው አልቆ በረሃው ሲጀመር በአንድ ጊዜ አንድ ሰው ብቻ የምታሳልፍ ከዘጠኝ ሜትር የማትበልጥ ሠርጥ አለች:: ተዳፋቷ በአፍጢም የም ትተከል ነው የምትመስለው:: መያዣ መጨበጫ ያላት ሳመለ ያህል ነው:: ከግራ አለት ከቀኝ አለት ከላይ ሰማይ ከመሐል እኛ::*

*/እናስተዋውቃችሁ ገጽ 23/*

የግእዝ ቅኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መገልገያ ከሆኑት መንፈሳውያን ድርሰቶች አንዱ ነው:: በመሆኑም በቤተክርቲያናችን ውስጥ ሰፊ የሆነ የአገልግሎት ቦታ (ስፍራ) አለው::

/ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ ገጽ 30/

ዋና አዘጋጅ– ግርማ ወ/ሩፋኤል
ም/ዋና አዘጋጅ– መርሻ አለኸኝ
ስልክ 556328
ፖስታ 80078
E-mail-HamTsidk @Yahoo•com
አዲስ አበባ

# ሐመር

7ኛ ዓመት ቁጥር 3

ሰኔ/ሐምሌ 1991 ዓ.ም

## *ይዘት*

*የማኅበሩ መልእክት*
*መሆንና መምሰል ሁለቱ ለየቅል............2*

*ደብዳቤዎች........................................6*

*ከሰሞኑ በረከት*
- ክርስቲያንነት..............................8

*ትምህርተ ሃይማኖት*
- *ነገረ ማርያም በቅዱስ ያሬድ.......9*
- *ነገረ ድኅነት .........................10*

*ቃለ መጠይቅ*
- በቅርብ የማውቃቸውና የምወዳቸው
የወንጌል መልእክተኞች ................14

*የጥያቄዎቻችሁ መልሶች ..........................18*

ኪነ ጥበብ
- ከታሪክ አንድ ገጽ........................20

እናስተዋውቃችሁ
- አባ አኖሬዎስ..............................22
- ከደብረ ብርሃን እስከ ሕዝብናኝ
ቤተመንግሥት............................ 23

*ዓምደ ወራዙት*
*ኑሯችን «እንዲጣፍጥ»..........................25*

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
- *ጭንቀት መንስኤውና*
*መፍትሔው...........................26*
- *ምንተ ንግበር...........................29*

ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ
- የግእዝ ቅኔ...............................30

*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክ ርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓ ትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::*

# መሆንና መምሰል - ሁለቱ ለየቅል

*«ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር»ማን ነው?*

ማንኛውም ፍጥረት የራሱ ማንነት አለው:: ይሁን እንጂ የቻለ ማንነቱን አስከብሮ ሲኖር ሌላው ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ማንነቱን ሊያጣ ይችላል:: በሌላ መልኩ ደግሞ ማንነቱን በውስጥ ቀብሮ የተለወጠ የሚመስልበት ጊዜም አለ:: ይኸም የተለያየ ዓላማ ሲኖረው እና ዓላማውን እስኪያሳካ ድረስ ብቻ የሚላበሰው የማስመሰል ገጽታ ነው:: ሰይጣን የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣል የሚለው የመጽሐፋችን ቃል ማለት የፈለግነውን የበለጠ ያብራራዋል:: ሰይጣን የብርሃን መልአክነት የለውም:: ሰዎችን ለማሳሳት ግን መስሎ ይቀርባል:: በራሱ ማንነት ቢመጣ ይታወቅበታልና:: ዛሬም አንዲቷን ቤተክርስቲያን ለመፈታተን ብዙ መስለው የቀረቡ እና ሊቀርቡ የሚሹ ጠላቶች አሉ:: ከእነዚህም መካከል አንዱ በማኅበር የተደራጀ ቡድን የዚህ መልእክት መነሻ ነው::

«ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» በሚል መጠሪያ ይታወቅ የነበረ አንድ ማኅበር በተለያዩ ጊዜያት ብቅ እያለ ወዲያው ደግሞ «ሲጠፋ» ይታያል:: ለመሆኑ እርሱ ማን ነው?

ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በ1951 ዓ.ም ተመሠረተ:: በወቅቱ ሚስዮናውያን በዩኒቨርስቲ ኰሌጅ አካባቢ ያካሂዱት የነበረውን የመናፍቅነት ሴራ ለመቃወም ቀናያን በሆኑ የቤተክርስቲያን ልጆች እንቅስቃሴውን ጀመረ:: በዚህም መነሻ የቤተክርስቲያን ልጆች በተለይም የተማረውን ክፍል በማቀፍ ትምህርተ ሃይማኖትን ማስተማር ቀጠለ:: በጊዜው የማኅበሩ አባላት የሆኑት ታማኝ የቤተክርስቲያን ልጆች በቆሙለት ዓላማ መሠረት የሚቻላቸውን ተጋድሎ አድርገዋል:: ማኅበሩም እያደገና እየተስፋፋ በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎች መንቀሳቀሱን ገፋበት::

ይህ ጥሩ ጅምር ግን ወደኋላ መልኩን እየቀየረ መጣ:: በ1963 ዓ.ም «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን (World Christian Students Federation) አባል ሆነ:: ይህ ፌዴሬሽን ደግሞ የራሱ የሆነ የተለየ ዓላማ ያለው ነው:: በተለይም በዓለም ያሉትን ክርስቲያኖች አንድ ለማድረግ በሚል ሰበብ የተሐድሶ (Reformation ) እንቅስቃሴን የሚያራምድ ነው:: በመቀጠል በተጨማሪም እያንዳንዱን የእምነት ድርጅት ወደ አንድ የሚያመጣው ሁሉን አቀፍ የሆነ የእምነት መግለጫ (Universalism) ሊኖር ይገባል ባይ ነው:: ይህ እስኪሆን ድረስ አንድነት በልዩነት ( Unity with Diversity) የሚል አቋም ያነገበ ፌዴሬሽን ነው:: ሃይማኖተ አበውም አባል የሆነው በእነዚህ ነጥቦች ተስማምቶ ነበር::

«ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን አባል ሲሆን መሠረታዊ ለውጥ ማድረግ ነበረበት:: ፌዴሬሽኑ በዓላማው ላይ አንዳንድ ለውጦችን ካላደረገ እንደማይቀበለው በማስታወቁ ጉዳዩን በውስጥ ሆነው ያቀጣጥሉ በነበሩት አንዳንድ ሰዎች ግፊት ለውጡን ተቀበለ:: ይህም «ተባባሪ አባላት» በሚል ሰበብ መናፍቃን የማኅበሩ አባላት እንዲሆኑ ማድረግ የሚለው ነው:: ከእነዚህም መካከል የፕሮቴስታንት በተለይም «ሙሉ ወንጌል» እየተባለ የሚጠራው የመናፍቃን ድርጅት አባላት በብዛት ወደ «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» እንዲቀላቀሉ ሆነ::

በዚህም ምክንያት «ማናቸውም የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አባል <u>ያልሆነ</u> ለክርስትና እምነትና ሕይወት ደንታ ያለው ከሆነ በተባባሪ አባልነት ከማኅበሩ (ከሃይማኖተ አበው) ሊገባ ይችላል::» የሚል አንቀጽ በሕገ ደንቡ ውስጥ አስገባ:: ስለሆነም ብዙ መናፍቃን ወደዚህ ማኅበር ሰርገው ገቡ:: ደንቡም ሆነ ዓላማው ተለወጠ:: መናፍቃንም የወደዱትን ለማድረግ በር ተከፈተላቸው::

ይህ በመሆኑም «ተባባሪዎቹ አባሎች (መናፍቃን) በልዩ ልዩ እምነት ተከታዮችና በክርስትና ወገኖች መካከል አንድነትንና መግባባትን ያጠናክራሉ ያስፋፋሉ» የሚል አንጉል ፈሊጥ ያዙ:: በቀጥታ የ« Universalism» አስተሳሰብ እየጐላ መጣ:: እንደዚህ ያለው የዓላማ ለውጥ የማኅበሩን የጉዞ አቅጣጫ ለወጠው:: ይህንን ለውጡን በወቅቱ ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲያውቅ አልተደረገም:: ሥራው ሁሉ ውስጥ ለውስጥ በስውር የሚከናወን መሆን ስለነበረበት መደበቁ ተመረጠ:: ብዙዎች የቀሃንም የቀደመውን ዓላማ ያልለቀቀ እየመሰላቸው ሳያውቁት የመናፍቃን ሰለባ ሆኑ:: በተባባሪ አባልነት ስም የገቡት መናፍቃን ለምድ ለብሰው ምእመናንን እንዴት ከእናት ቤተክርስቲያናቸው እንደሚለዩ ከፍተኛ ጥናት ያደርጉ ጀመር:: በሚያገኙት መድረክ ሁሉ «ከወጣቱ ፍላጐት አንፃር ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች አሉ:: እምነቱ ካልተነካ ሥርዓት ቢሻሻል ምንም የለበትም ለሚለው አስተሳሰብ ማኅበራቸው (ሃይማኖተ አበው) ቅድሚያ ይሰጣል» በማለት መለፈፍ ቀጠሉ:: ሥርዓት

ቤተክርስቲያንን ለመለወጥም ከቅዱስ ሲኖዶስ በላይ የሆነ ሥልጣን እንዳላቸው አድርገው ተነሡ። ለነገሩ ቅዱስ ሲኖዶስ ማለት ለእነርሱ ምንም ማለት አይደለም።

በዚህም እንቅስቃሴ «የቅዳሴ ሰዓት ረዘመ ማጠር አለበት፣ በያሬዳዊ ዜማ መዘመር አንጉል ፈሪሳዊነት ነው፣ የቤተክርስቲያን የዜማ መሣሪያዎች ወደ ጊታር፣ ፒያኖ፣ ኦርጋን፣ ሲንቲሳይዘር፣ ሳክስፎን... ወዘተ መለወጥ አለበት» እያሉ ብዙዎችን አሳሳቱ። በወቅቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ በመኖራቸው የዋሁ ምእመን ሊጠረጥራቸው አልቻለም። አንዳንድ ሴራው የገባቸው ሰዎች ቢኖሩም በጊዜው የሚችሉትን ያህል ተቃወሙ እንጂ መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጡ አልቻሉም።

ለምልክትም ያኔ ያስገቧቸው አንዳንድ የዘፈን መሣሪያዎች ዛሬ ድረስ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ተቀምጠው ይገኛሉ። እንደ እነርሱ አስተሳሰብማ እነዚህ የዘፈን መሣሪያዎች ገብተው ብዙ ዕድሜ ካስቆጠሩ የሚመጣው ትውልድ እንደ ትውፊታዊ የዜማ መሣሪያ ይቀበላቸዋል ብለው ነበር። ሁለተኛም ጥንታዊ እና፣ ምሥጢራዊ የቤተክርስቲያናችን መለያ የሆኑትን የዜማ መሣሪያዎች ለማረሳሳት እና ኦርቶዶክሳዊ ማንነትን ለማሳጣት አንዱ ዘዴ ነው በማለት ነበር። ሦስተኛም በወቅቱ እንደ አሸን ከፈሉት መናፍቃን ጋር ለማመሳሰል እና ነገ ምእመኑ «እዚህም እዚያም ያው ነው። ልዩነቱ ምኑ ላይ ነው?» ብሎ እንዲሰናከል አስቀድመው መንገድ ለማመቻቸት የወጠኑት ሴራ ነበር።

የጉዞ መጀመሪያቸው በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ላይ ዘመናዊ ለውጥ ማምጣት ወይም ትውፊት አበውን ትቶ በአዲስ የመናፍቃን የግርግር መስመር መጓዝ ይሁን እንጂ የዓላማቸው ፍጻሜ «የክርስቲያንን እምነት (የመናፍቃኑን ሁሉ) ፍጹምነትና ርቱዕነት ሳያዛቡና ሳያፋልሱ የክርስቲያኖችን ሁሉ (መናፍቃንን ይጨምራል) <u>አንድነት</u> ለማሳወቅ» የሚል ነው። ይህም ቀደም ሲል «አንድነት በልዩነት» ከዚያም «Universalism» የሚለው አመለካከት መዳረሻ ነው።

በመጨረሻም «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በጸጉር ስንጠቃ ከመናፍቃን ተለየች እንጂ ከመናፍቃን ጋር የሚያራርቅ መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት (Dogma) ልዩነት የለም። ስለሆነም ልዩነታችን እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ እንሁን» ወደሚል ድምዳሜ ደረሱ። ይህንንም ለመፈጸም ያስችል ዘንድም በተለያየ ጊዜ በተለያየ ስልት (Strategy) እየቀየሱ ጉዟቸውን ቀጠሉ። ይህ ሁሉ የሚሆነው በተባባሪ አባልነት ስም ባስገቧቸውና እነርሱ ከዚያ ውስጥ በመለመሏቸው ሰዎች ነው። ቀጥሎም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ «ነገረ ድኅነትን ባጠቃላይም ትምህርተ ሃይማኖትን የሚቃወም ፍልስፍናቸውን» ማሠራጨት የዕለት ተዕለት ሥራቸው ሆነ።

በመካከልም «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» በ1975 ዓ.ም እንዲዘጋ ከቤተክርስቲያን ትእዛዝ ተላለፈ። በዚህም መሠረት ጥቅምት 1976 ዓ.ም በግልጽ መመሪያ ተዘጋ። እስከ 1980 ዓ.ም ድረስ ያንኑ አቋሙን ከቤተክርስቲያን ውጭ፣ ከመናፍቃን ጐራ ተሰልፎ ቆየ።

በ1980 ዓ.ም እንደገና እንዲከፈት ጥያቄ አቀረበ። በጥያቄውም መሠረት ሦስት ሊቃነ ጳጳሳት እና አራት ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ያሉበት አንድ አጥኚ ቡድን ተቋቋመ። አጥኚ ቡድኑም ባጠናው መሠረት «ማኅበሩ መጀመሪያ በዩኒቨርስቲ ኰሌጅ አካባቢ ከነበረው ዓላማ ፈጽሞ የተለየ ዓላማ ይዞ ይንቀሳቀስ እንደነበረ» አረጋገጠ።

በተለይም በሚያካሂዳቸው መርሐ ግብሮች ውስጥ እንዲሳተፉ ያደርጉ የነበሩት መናፍቃን መሆናቸው ታወቀ። ከእነዚህም መካከል «የመካነ ኢየሱስ መዘምራን»፣ «የሌዊ ሐርምስ መዘምራን»፣ «የሙሉ ወንጌል መዘምራን»፣ «የብርሃነ ወንጌል ወጣቶች»፣ እና የመናፍቃኑ «ሰባክያን» ይገኙበታል። ከዚህም በተጨማሪ የሚያካሂዱት ጉባኤ ወይም መርሐ ግብር «ይባረክ» የነበረው በመናፍቃን ነበር። ይህም በአጥኚ ቡድኑ ተረጋግጧል።

ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ተቀምጠው የመናፍቃን «ሰባኪዎች» ወንጌልን እያጣመሙ እንዲያስተምሩ መደረጉ በቀጥታ ቤተክርስቲያኗን ለማጥፋት የተቃጣ መሆኑ አይካድም። በያሬዳዊ ዜማ በጣዕመ ዝማሬ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ መዘምራን ላላት ቤተክርስቲያን የመናፍቃኑ ቸበርቻቻ ምን ያደርግላታል? ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቀሳውስት ያሏት ቅድስት ቤተክርስቲያን ከፕሮቴስታንት «ፓስተር» «ቡራኬ» የምትቀበለው እንዴት ነው ?

አጥኚ ቡድኑ በሚያጠናበት ወቅት እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች በወቅቱ ማኅበሩን እንወክላለን ብለው ለቀረቡት ሰዎች አንሥቶ ነበር። ሆኖም «እንታረማለን» የሚል የማስመሰያ አቋማቸውን በመግለጣቸው ለጊዜው እንደገና እንዲከፈት ተደረገ። የተከፈተው በ1984 ዓ.ም ሲሆን ወቅቱ በቤተክርስቲያን አካባቢ ፈተና የበዛበት ጊዜ ነበር። ሲከፈትም «ወደፊት በምትሠሩት ሥራ ትታያላችሁ» በሚል እንጂ ሙሉ በሙሉ ታርመዋል በሚል አልነበረም።

በቤተክርስቲያን መዋቅር ሥር ነን ይበሉ እንጂ በዚያ ወቅትም ከመናፍቃኑ ጐራ የሚያሰልፋቸው ሌላ መዋቅር ዘርግተው ነበር። ዛሬ በየአደባባዩ የክህደት ትምህርት የሚያስተምሩ ከዚሁ ማኅበር ተመልምለው የወጡ መናፍቃን ናቸው። ሳይገባቸው የቤተክርስቲያናችንን ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፣ የማያምኑበትን መስቀል ጨብጠው በየመድረኩ እናት ቤተክርስቲያንን «የሚያወግዙት» እነማን ናቸው? ይህ ማኅበር አሠልጥኖ ያወጣቸው አይደሉምን? መስቀሉን የሚይዙት፣ በሥልጣነ ክህነቱ የሚጠሩት፣ ቆቡን የሚደፉት ለማስመሰል እንጂ እነርሱ የቤተክርስቲያን አካል ሆነው አይደለም።

ዛሬ «ኢየሱስ አማላጅ ነው፣ ድንግል ማርያም አታማልድም፣ ታቦትም፣ ሥዕልም፣ ድርሳንም፣ ገድልም አያስፈልግም» እያሉ የሚለፍፉት ከየት የተገኙ ናቸው? ማኅበሩን እንመራለን እንወክላለን የሚሉትስ ሰዎች

መስቀልን «ግንዲላ» ብለው የተቃወሙ አይደሉምን? የተሐድሶ አርቶዶክስ መነኩሳት ኅብረት ነን ባዮቹስ ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር መልምሎ ያሠለጠናቸው መሆኑ ይረሳልን?

ሥራውንም ለማከናወን ይረዳው ዘንድ ከዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን (WCSF) እስከሁን ድረስ በጀት ያገኛል:: ይህም የሚያመለክተው ፌዴሬሽኑ ያለመውን ዓላማ በማሳካት ላይ መሆኑን ነው:: በጀቱን ለማግኘት በየጊዜው የሠራቸውን ሥራዎች በዝርዝር ማቅረብ ይጠበቅበታል:: ስለሆነም ይህ ማኅበር የፈለገውን ያህል እታረማለሁ እያለ ለማስመሰያ ይናገር እንጂ ከፌዴሬሽኑ ዓላማ ውጭ የሆነ ሥራ መሥራት እንዳይችል ሆኖ ተቀርጿል::

እንደዚህ ያለው የክህደት ጉዞ ስለተደረሰበት በ1986 ዓ.ም ለመጨረሻ ጊዜ ማኅበሩ እንዲዘጋ ቤተክርስቲያን ትእዛዝ አስተላለፈች:: በዚህም መሠረት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» የሚባል ቡድን ቤተክርስቲያን አታውቅም:: በወቅቱ እንዲዘጋ የተደረገውም ታላላቅ የቤተክርስቲያን አባቶች እና የጠቅላይ ቤተክህነት ከፍተኛ ኃላፊዎች ባካሄዱት ጥንቃቄ የተሞላበት ጥናት ነበረ::

ማኅበሩ በምሥራቁ የሃገራችን ክፍል ያካሄደው የነበረው የክህደት እንቅስቃሴ ከየትኛውም የሀገራችን ክፍሎች የላቀ ስለነበር በሐረር እና በድሬዳዋ ከተማ ማኅበሩ አስነሥቶት በነበረው ብጥብጥ የቤተክርስቲያን አባቶችን (ሊቃነ ጳጳሳትን እና ሌሎች አባቶችን) ደብድቧል:: የሰው ሕይወትንም እስከማጥፋት ደርሷል:: ከዚህም በተጨማሪ አባቶች እንዲታሠሩ አድርጓል:: ታዲያ ይህ ማኅበር ማን ነው? አባቶችን የሚደበድብ እና የሚያስር፣ የሰው ሕይወትም የሚያጠፋ እርሱ ምንድን ነው?

ይህንና ሌሎች እኩይ ሥራዎችን ያከናውን የነበረውን «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርን» ቤተክርስቲያን በወቅቱ ማገዷ አግባብነት ያለው ነበረ:: ሲከፈትም «ሥራህ ይገልጥሃል» በሚል ነበረና ሥራው ገለጠው:: ከሰው መሰወር ይቻል ይሆናል ከመንፈስ ቅዱስ ግን መሰወር በጭራሽ አይቻልም::

«ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርን» ቤተክርስቲያን በሕጋዊ እርምጃ ያገደችው መሆኑ ቢታወቅም ከተዘጋበት ጊዜ አንሥቶ እስካሁን ድረስ ያለ ቤተክርስቲያኗ ዕውቅና በየአዳራሹ የተለያዩ የክህደት መርሐ ግብሮችን በቀደመ ስሙ እያካሄደ ይገኛል:: ለዚህም አብነት የሚሆነን በተለያዩ ጊዜያት በሚበትነው በራሪ ወረቀት (Tract) ነው:: እንዳይንቀሳቀስ ታግዶ ሳለ «አልታገድሁም» እያለ ሰዎችን በማታለል ላይ ይገኛል:: እውነተኛ የቤተክርስቲያን አካል ቢሆን ኖሮ እንዲህ ያለ የማስመሰያ ጉዞን ባልመረጠ ነበር:: ቤተክርስቲያንንም ምን ያኽል እንደተዳፈራት ከዚህ መረዳት ይቻላል::

በአሁኑ ወቅት በተለያየ ሁኔታ «እንደገና ሊከፈትልን ነው» የሚል አዲስ ዘመቻ በመያዝ ምእመናንን በማወክ ላይ መሆኑ ተደርሶበታል:: በተለያዩ ጊዜያት እያዘናጋ የሚመጣውስ ለምንድን ነው? ምን ያልተሠራ ሥራ ለመሥራት ነው? አንድ ነገር ለማስታወስ እንወዳለን:: በ1984 ዓ.ም እንዲከፈት ሲደረግ «እንታረማለን» የሚል ማስመሰያ አቅርቦ ነበር:: ነገር ግን በቀጣዮቹ ጊዜያት በዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን የተጣለበትን አደራ ለመወጣት (ምዕመናንን ለማስበርገግ) ተጣጣረ:: በበለጠ ሁኔታ የመናፍቅነት ባሕርዩን፣ እያሳየ ስልቶችን እያረቀቀ መጣ እንጂ ቤተክርስቲያንን አልሰማትም:: በዚህም ምክንያት ቅድስት ቤተክርስቲያን አገደችው::

አሁንም ቢሆን «እንመለሳለን» ሲሉ «የድሮውን ደንብ ትተነዋል አዲስ ደንብ አውጥተናል» ማለታቸው አይቀርም:: የሚፈለገው የወረቀቱ ለውጥ ሳይሆን የሰዎቹ ማንነት ነው:: ለእነዚህ ሰዎች እንደገና መድረክ መስጠት ማለት ቤተክርስቲያንን ለጥፋት አሳልፎ መስጠት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: መሆንና መምሰል ሁለቱ ለየቅል ነውና:: እየመሰሉ ይምጡ እንጂ የቤተክርስቲያን አይደሉም:: ባለፈው ላጠፋነው ጥፋት ንስሐ እንገባለን ሊሉም ይችላሉ:: ንስሐ አይግቡ የሚል አመለካከት ባይኖረንም ንስሐ መግባት ያለባቸው ማኅበሩ እንዲከፈትላቸው መሆን ግን የለበትም:: እንደዚህ ከሆነ ነገ ተመልሰው ወደ ትፋታቸው እንደሚሄዱ እርግጥ ነው:: አልቅሶ መናገር መስቀል መትቶ መግል እንደሆነ የዘወትር ሥራቸው ነው:: የአንገት ማስገቢያ እስኪያገኙ ድረስ መሬት ይሆናሉ:: ከዚያ በኋላ ግን ወደ ክህደት ሥራቸው መመማራታቸው አይቀርም:: ይህ ደግሞ የመናፍቃን ጠባያቸው ነው::

እኛም የበኩላችንን (እንደ ቤተክርስቲያን አካልነታችን) ለማለት ፈልገን እንጂ ይህ እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ከአባቶቻችን የተሠወሩ ሆነው አይደለም:: በቤተክርስቲያን ላይ ስለተቃጡ የተለያዩ ሴራዎች ማኅበረ ቅዱሳን በተደጋጋሚ ያነሣል:: እንደዚህ ያሉ ርእሰ ጉዳዮችን የሚያነሣው ግለሰቦችን ከመጥላት ወይም ከመቃወም ሳይሆን ከዚህ በፊት ለሚመለከታቸው በተደጋጋሚ በበቂ ማስረጃ እንዳረጋገጠው ሁሉ ሁኔታዎችን በሚገባ አጢኖ ከአባቶች ጋር መክሮ ቤተክርስቲያንን ሊያጠፏት ከተነሡ ጠላቶች በእግዚአብሔር አጋዥነት ለመታደግ ነው::

ማኅበረ ቅዱሳን በ1985 ዓ.ም ራሱን «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር » እያለ ከሚጠራው ከዚህ ክፍል ጋር አሥራ ሦስት ጊዜ ያህል ተደጋጋሚ ውይይቶችን አካሂዷል:: ማኅበሩን እንዲሁ ከመጥላት ቢሆን ይህን ባላደረገ ነበር:: ይህንን ለማድረግ የተነሣሣውም ምናልባት ሰዎቹ ባላሰቡትና ባላጤኑት መንገድ በየዋህነት ገብተውበት ሊሆን ይችላል፤ የሚታይባቸውን ችግር ቢቀርፉ ለቤተክርስቲያኗ የሚጠቅም ሥራ ወደ መሥራት ይሄዳሉ በሚል ነበር::

ነገር ግን ዓላማው የተጠና እና በጭራሽ የማይለወጥ መሆኑን የማኅበሩ ተወካዮች አጠንክረው በተደጋጋሚ በመግለጣቸው ውይይቱ እንዲቋረጥ ሆኗል:: ማኅበረ ቅዱሳን እነዚህ ሰዎች ስህተታቸውን ቢያርሙ አብሯቸው ለመሥራት ፈቃደኛ ነበር:: ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ግን ከያዘው መስመር ፍንክች አልልም በማለቱ የሚፈለገው ሳይሆን ቀረ::

በወቅቱ በተካሄዱት ውይይቶች ውስጥ በርካታ ጥያቄዎች ለሃይማኖተ አበው ቀርበውለት ነበር:: ከእነዚህም መካከል ሥርዓተ ቤተክርስቲያን በፍጥነት መሻሻል አለበት የሚለው አቋም ትክክል ነውን?፣ በራሱ መንገድ ያለ ቤተክርስቲያን ዕውቅና የውጭ ግንኙነት ማድረጉ ይገባልን? ይህስ ለአደጋ የሚያጋልጥ አይደለምን?፣ ከመናፍቃን ጋር አንድ ሆኖ የቤተክርስቲያንን ሥራ መሥራት እንዴት ይቻላል? የሚታይባችሁን አንዳንድ የሃይማኖት ችግር ያመጣው ይህ አይደለም ወይ? የሚሉት ይገኙበታል:: ለእነዚህ ጥያቄዎች የሰጡት መልሶች «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» በጭራሽ የቤተክርስቲያን አካል አለመሆኑን የሚያረጋግጡ ነበሩ:: ልዩነቱ የሃይማኖት በመሆኑም አጠቃላይ ግንኙነቱ ተቋረጠ:: ማኅበረ ቅዱሳን ከዚህም በላይ በቤተክርስቲያን አባቶች ተመክረው ይመለሱ እንደሆነ በሚል ብዙ ጥሮ ነበር:: ነገር ግን አልተሳካም::

እኛ «ከእኛ ወዲያ ለአሣር» የሚል አቋም የለንም:: ቤተክርስቲያንን የሚያፈርሱት ግን የምንታገስበትን ኀሊና ፈጽሞ ሊኖረን አይችልም:: ማድረግ ያለብንን በወቅቱ አድርገናል:: እንደዚህ ላሉት የሃይማኖት ጠላቶች ቦታ የሚሰጡ ካሉም ማንነታቸው ሊጣራ ይገባዋል:: በማስመሰል የሚነግሯቸውን ብቻ በመቀበል «እነዚህማ ለቤተክርስቲያን ያስፈልጓታል» ማለትም የዋህነት ነው:: ሰይጣን በእባብ ገላ ተሰውሮ ሔዋንን ሲያስታት ለእርሷ ያሰበ በመምሰል እንጂ ሰይጣንነቱን ነግሯት አይደለም:: ማንነቱን ቢገልጥ ኖሮ ዓላማው ከወዲሁ ይደናቀፍበት ነበር::

ይህንን ሁሉ ያልነው ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርን በተመለከተ የሚከተሉት ጉዳዮች ሊጤኑ ይገባል ከሚል መነሻ ነው::

1. በተባባሪ አባልነት ስም መናፍቃንን ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያን እያስገባ የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን የሚያራምደውን ቤተክርስቲያንን የመለወጥ አቋም የሚያስፋፋ እና የቤተክርስቲያን አካል ያልሆነ መሆኑ
2. ደንቡን ለውጦ ቢቀርብም ውስጥ ለውስጥ የሚያከናውናቸው የጥፋት ሥራዎች እጅግ አደገኞች መሆናቸው ከዚህ ቀደምም ታይቷል:: «እንታረማለን» በሚል የማስመሰያ ፊሊጥ ተጥሎበት የነበረው እገዳ እንዲነሣለት ባደረገ ማግሥት እዚያው ከመናፍቃን ጐራ ተሰልፎ እንደተገኘ ሁሉ አሁንም በዚያው ስሜት ቢመጣ ምንም ዋስትና የሌለው መሆኑ፣ ለዚህም ትናንት በአበው ሊቃነ ጳጳሳት ፊት «እንመለሳለን» ብለው ነገር ግን በዚያው የውኃ ሽታ ሆነው የቀሩትን እነ ግርማ በቀለና ጽጌ ስጦታውን ማስታወሱ ይበቃል:: እነዚህም የዚሁ ማኅበር ውጤቶች መሆናቸው ይታወቃል:: የተያዘውም አቋም «ለጊዜው ቦታ እናግኝ እንጂ ኋላ የምንሠራውን እናውቃለን» ዓይነት አመጣጥ መሆኑ::
3. እንደ ዓላማ የያዘው «ቤተክርስቲያንን የመለወጥ» አቋም አደገኛ ነው:: በጐችን ለመናፍቃን የሚያቀብልበት ድልድይ አዘጋጅቶ ሲንቀሳቀስ የቆየ ማኅበር ለመሆኑ ከላይ ዘርዝረናል:: በተለይም የተሐድሶ እንቅስቃሴን ለማራመድ ብቃት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን በስውር አሰማርቶ የነበረ እና የተሐድሶ ድርጅትን በመመሥረት (ያላወቁ) የቤተክርስቲያን ልጆችን ለመናፍቃን ሲያቀብል የቆየ የውስጥ ጠላት መሆኑ
4. ወደ ቤተክርስቲያን ገብቶ ሥራውን እንዲሠራ ለማድረግ በጠቅላይ ቤተክህነት ውስጥ ሆነው ላይ ታች የሚሉ አንዳንድ መናፍቃንን በሥልጣናቸው ለመጠቀም በውስጥ አሰማርቷል:: በእነርሱ ስለማኅበሩ የሚነገሩ አንዳንድ ሐሳቦች ትክክል አለመሆናቸው እና ባለሥልጣኖችም በመናፍቅነት መጠየቅ ያለባቸው መሆናቸው
5. ቤተክርስቲያን በሕጋዊ ደብዳቤ ብታግደውም ውሳኔዋን ጥሶ ቤተክርስቲያንን የማይመስሉና የማይወክሉ በርካታ ጉባኤዎችን ሲያካሂድ እንዲሁም ጽሑፎችን ሲበትን መቆየቱ:: ብዙዎቹ አባላቱ ዛሬ በየመናፍቃኑ አዳራሽ ተበታትነው ይገኛሉ:: አሁን ልመለስ እንኳን ቢል አባላቱን የሚያመጣቸው ከየት እንደሆነ ሊታሰብበት የሚገባ ይሆናል:: «በጸጋው ድነናል፣ ኢየሱስ አማላጅ ነው» ሲል የቆየ ኅብረተሰብ ይዞ የሚመጣ መሆኑ እና ሌሎችም በሚገባ ሊጤኑ ያስፈልጋል::
6. ባለፈው ዓመት ቅድስት ቤተክርስቲያን አውግዛ የለየቻቸው «የተሐድሶ መነኩሳት ኅብረት» አባላት የሃይማኖተ አበው ማኅበር የመጨረሻ የዕድገት ደረጃዎች ናቸው:: ስለሆነም ቤተክርስቲያን የዚህን ማኅበር ጉዳይ ከእነዚያኞቹ ለይታ የምታይበት ዐይን የላትም::

ይህንን ጉዳይ የሚመለከታቸው ሁሉ በስከነ ልቦና አጢነውት ትክክለኛ መፍትሔ እንዲሰጡበት አደራው የጠበቀ ነው:: መፍትሔውም የማያዳግም እንዲሆን በቤተክህነት አካባቢ ወዲያ ወዲህ ከሚሉት መናፍቃን ጀምሮ ሊታይ ያስፈልጋል:: ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን ነገ በቤተክርስቲያን ላይ እጅግ አደገኛ ሁኔታ ይከሰታል:: በመጨረሻ ልናሳስብ የምንፈልገው ነገር ቢኖር «መሆንና መምሰል ሁለቱ ለየቅል» መሆናቸውን ነው:: ከአነሣሡ ጀምሮ አሁን እስካለበት ደረጃ ያሳየነውም በቂ ግንዛቤ ለመስጠት ነው:: ተገልጠው እያየናቸው አላያችሁንም በማለት መምጣታቸው አይቀርም:: ስለሆነም መላው የቤተክርስቲያናችን አባቶችና ምእመናን በዝምታ ሊያልፉት አይገባም::

«ሳይቃጠል በቅጠል» እንዲሉ ቅዱሳን የተጋደሉላትን ቤተክርስቲያን ከመዳፈራቸው አስቀድሞ ከወዲሁ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ በቤተክርስቲያን አምላክ ስም እናሳስባለን::

*ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን::*

# ደብዳቤዎቻችሁ

## በዚህ በኩል በርቱልን

በሐመር ሰባተኛ ዓመት ቁጥር አንድ እትም «መቅደሴን ፍሩ» በሚል ርዕስ በቀሲስ ስንታየሁ አባተ የቀረበው ጽሑፍ እጅግ አስደስቶኛል:: በእውነቱ ይህ ጉዳይ የወቅቱ የቤተክርስቲያናችን ችግር እንደመሆኑ ጽሑፉም ይህንን ውስጣዊ ችግር በሚገባ የዳሰሰ ነው:: ስለዚህ ውድ አዘጋጆች አምላካችን በዚህ ኃጢአታችን መቅሰፍቱን ሳያወርድብን መምህራን ተግ ተን ብናስተምር ምእመናንም በንቃት ብን ማር መልካም ነው እላለሁ::

*አዲሱ አራጋው*
*ምዕ/ሐረርጌ( መቻራ)*
*ተራመጅ ተስፋዬ*
*ተጉታ (ደ.ወሎ)*

## ገጽ ማባከናችሁ...?

ሐመር መጽሔት በእጄ እንደገ ባች ፈጠን ብዬ የማነበው የደብዳቤዎችን ዓምድ ነው:: ታዲያ እንደተለመደው ሐመር 7ኛ ዓመት ቁጥር አንድን ሳነብ አንድ የእናንተን ድር ጊት የማልደግፍበት ደብዳቤ አነበብኩ:: ይኸውም አንድ ወን ድሜ 'መጽሔታችሁ ያደክማል' ሲል የሰጠ ውን «አስተያየት» በቀጥታ አውጥታችሁ ታል:: ያ ወንድሜ በመጽሔቷ ስለሚወጡ ጽሑፎች ረጃጅም መሆን ከዚህም የተነሣ ለማንበብ እንደሚያደክሙ ጠቁሟል:: እን ደእኔ ይህ መባል አልነበረበትም:: የአርበ ኞች የቅዱሳን አባቶቻችን ልጆች ሆነን ሳለን እንዴት ማንበብ ያደክመናል? እነ ርሱ ተጋድሎው መጻፍ መደጉሱ አላደከማ ቸውምና:: የሆነው ይሁንና እናንተ ወንድ ሞቼ ይህንን አስተያየት ለሰጠው ወን ድማችሁ በትህትና ሆናችሁ ልታስረዱ ትና በዚያ ቦታ ላይ ሌላ ቁም ነገር ማስቀ መጥ ስትችሉ ገጽ ማባከናችሁ ለምንድን ነው?

*ዲ. ሰውነት ታዬ*
*/ደራ/*

## ለእነሱ ቢጨምርልን

ይድረስ ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል፤ ዕውቀቱን እንዲገልፅላ ችሁ የዕውቀት አባት የሆነውን ቤዛ ዓለም ክርስቶስን ሁሌም በጸሎቴ እጠይቃለሁኝ:: ውድ ወንድሞቼ ይህችን ደብዳቤ እንድጽ ፍላችሁ ያነሣሣኝ በቅርቡ በአስቃቂ ሁኔታ ለኀልፈተ ሕይወት ስለተዳረጉት ሁለቱ አባቶቻችን በተመለከተ ነው:: ይኸውም በጉባ ከተማ ለሚደረገው ትልቅ ጉባኤ ለመገኘት ሲመጡ በአርሲ ሜዳ የቀሩትን አባቶቼን ዜና ዕረፍት ስሰማ በጣም ጥልቅ ኃዘን ነው የተሰማኝ:: ሌሎች የቤተክርስ ቲያን ልጆችም እንደሚያዝኑ አልጠራጠ ርም:: ወገኖቼ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ብዙ አባቶችን እያጣን ነው:: ስለዚህ በመጽሔታችሁም ሆነ በጋዜ ጣችሁ ላይ ሕዝበ ክርስቲያን ለአባቶቻችን በዕድሜ መቆየት ጸሎት እንዲያደርግ ብታሳስቡ መልካም ነው እላለሁ::

*ተፈሪ መኮንን*
*(ከባሌ ደሎ መና)*
*መብራቱ( ሐረር)*

<u>ከአዘጋጁ</u>:-

ወንድሞቻችንን እናመሰግና ለን:: ቀደም ሲልም ሆነ አሁን በቅርቡ ያጣናቸ ውን አባቶቻችንን በሚመለከት የተሰማንን ኃዘን በመጽሔታችንም ሆነ በጋዜጣችን አስነብበናል:: ወንድሞቻችን እንዳሉት ብዙ ሊያስተምሩን፣ ሊመክሩንና ሊባርኩን የሚ ችሉ አባቶ ቻችንን በተመሳሳይ አደጋ እያ ጣን ነውና ምእመናን በጸሎታቸው እንዲ ተጉ አደራ እንላለን::

## በልጅነት አንደበት

ሐመሮች መጽሔታችሁ በጣም ጥሩ ዕውቀት እያስጨበጠኝ ነው:: በሰባ ተኛ ዓመት ቁጥር ሁለት እትማችሁ ከቅዱስነታቸው ጋር ካደረጋችሁት ቃለ ምልልስ በሀገርና በቤተክርስቲያን መከራ ትና መመካትን በአንጻሩም ቤተክርስቲያን ከችግሮቿ ሁሉ ትላቀቅ ዘንድ አብዝቶ መጸለይ እንደ ሚያስፈልግ ተምሬያለሁ:: ቅዱስነታቸው የቤተክርስቲያናችንንና የኢ ትዮጵያን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ነት በትክክል በማስቀመጣቸው በልጅነት አንደበት ላመስግናቸው እወዳለሁ:: እንደ ተባለው የቤተክርስቲያን ታሪክ የኢትዮ ጵያ ታሪክ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ የቤተክር ስቲያን ታሪክ በመሆኑ ዛሬ የመናፍቃኑ የማጥፋት እርምጃ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ካለ ፍላጐት የመጣ መሆኑን ተረድቶ ማንኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ሊነቃና ሊከላ ከል ይገባል:: አገሩ የሆነች አገራች ንንና በደሙ የዋጃትን ቅድስት ቤተክ ርስቲያንን የማይረሳ አምላክ አሁንም በሠ ይጣን ከሚመጣ ፈተና ሁሉ ይጠብቅልን::

*ቤካ - ምዕ/ወለጋ*

## አቅራቢውን አመስግኑልኝ

በሰባተኛ ዓመት ቁጥር ሁለት እትማችሁ በ«ኪነጥበብ» ዓምድ «እግዚአብ ሔርን ማየት እፈልጋለሁ» በሚል ርዕስ የቀረበው ጽሑፍ እጅግ አርክቶኛል:: በወ ጣቱና በአባ ከሚደረገው ጥያቄና መልስ እጅግ ጠቃሚ ቁም ነገሮችን ማግኘት ይቻ ላል:: በተለይ በእምነት ይኖር ዘንድ ምል ክትን አጥብቆ ለሚሻ ትውልዳችን ትክ ክለኛውን መልስ የሰጠ ይመስለኛል:: ስለ ዚህ አቅራቢውን አመስግኑልኝ:: ፍቅረ እግ ዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን::

*ከበቡሽ ዘለቀ*
*/ሞጆ/*

## ...ስለምወዳቸው በርቱልኝ

ይህን ደብዳቤ ኢሒዱ ብዬ ስልክ ላችሁ ተደስቼ ደስታዬን ይገፔ መቀመጥ ስላልቻልኩኝ ነው:: የምታዘጋጂቸው ዓም ዶች በጣም ደስ የሚሉና የሚያስደስቱ ናቸው:: ሌላው በ7ኛ ዓመት ቁጥር 2 የማኅበሩ መልእክት በሚለው ጽሑፍ በጣም ረክቻለሁ:: ይህ ለተዋሕዶ ልጆች ትምህርት ሲሆን ለመናፍቃን ዕፍረት ውርደት ነው:: በዚህ ቀጥሉ:: ለጥያቄዎች መልስ ዓምዳችሁ ከአሶሳ ታደሰ መርጊያ በዮሐንስ ራእይ 22÷18–20 የጠየቀው ጥያቄ የኔም የዘወትር ጥያቄዬ ስለሆነ መልሱን በማግኘቴ በጣም ደስ ብሎኛል:: ስለዚህ ከላይ የጠቀስኳቸውንና የተቀሩት ንም ዓምዶች በጣም ስለምወዳቸው በርቱ ልኝ:: ድንግል በጸሎቷ ትጠብቃችሁ::

*ወንዳፍራሽ ፋንታዬ*
*/አሶሳ/*

## ቢመቻችልን

የመጽሔታችሁ ደንበኛ የሆንኩት በ1985 ዓ.ም ሲሆን በመጽሔቷ ከሚወጡ ትምህርቶች ብዙ ቁም ነገሮችን ዐውቄአ ለሁ:: ይህንን እንድታደርጉ የጠራችሁ እግ ዚአብሔር ይክበር ይመስገን እያልኩ በ7ኛ ዓመት ቁጥር 2 ሚያዝያ/ግንቦት መጽ ሔት ላይ ከቅዱስ አባታችን ጋር ያደረጋ ችሁትን ቃለ መጠይቅ ተመልክቼው ተደ ስቼበታለሁ:: በመጨረሻው ጥያቄአችሁ ላይ በተሰጠው መልስ የማታ ትምህርት ፕሮግራም እንደሚጀመር ተገልጿል:: ነገር ግን በአቅራቢያው የሌለን የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን ስለማንችል ኮርሱ በክረምት ሆኖልን እንድንማር ሁኔታዎች ቢመቻቹልን ካልሆነም ኮሌጁ የተልእኮ

ትምህርት እንዲጀምር ቢሆን የበለጠ ለመሥራት እንችላለን:: ምክንያቱም በተለያየ የመንግሥት ሥራ ላይ እያለን ቤተክርስቲያንን የምናገለግልና የምንገለገል ስልጣነ ክህነት ያለን ብዙዎች ነንና:: ለሁሉም ፈቃደ እግዚአብሔር ይሁን::

*ቀሲስ ሃ/ሚካኤል ወ/ገብርኤል*
*/ሻኪሶ – ቀንጢቻ/*

## በተስፋ እንጠብቃለን

ግንቦት 12 ቀን 1991 ዓ.ም ከአዲስ አበባ በባሌ ሀገረ ስብከት ጐባ ከተማ በተዘጋጀው መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ለመገኘት ሐዋርያዊ ተልእኮ ይዘው በመጓዝ ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው የመኪና አደጋ ከዚች ከምታልፈው ዓለም ወደማታልፈውና የዘላለም ሕይወት ወዳለባት ዓለም የተሸጋገሩት ብፁዓን አባቶቻችንን ዜና ዕረፍት በሚመለከት የተሰማኝን ጥልቅ ኃዘን በመግለፅ እባካችሁ የእነዚህን የታላላቅ አባቶቻችንን የሕይወት ታሪክ በምታሳትሟቸው ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣና ሐመር መጽሔት እንድታስነብቡን ይሁን::

*ተፈራ መኩሪያ*
*/ባሌ ጐባ/*

## ይህ ለምን ሆነ?

ሐመሮች በ7ኛ ዓመት ቁጥር 2 እትማችሁ ላይ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተ/ሃይማኖት ጋር ያደረጋችሁት ቃለ ምልልስ በጣም አስደስቶኛል:: በተለይ ስለወቅታዊ ጥያቄዎች ለምሳሌ የኤድስ በሽታና የመቃብር ቦታ ሁኔታ ያደረጋችሁት ቃለ ምልልስ በጣም አርክቶኛል:: ነገር ግን በተቸገሩ የገጠር አድባራትና ገዳማት እርዳታ ላይ አንዳንድ የአዲስ አበባ አድባራት ተገቢውን አስተዋፅኦ ያላደረጉ ይመስለኛል:: እንደዚሁ አንዳንድ አድባራት አንድ ሰሞን አስቀምጠውት የነበረውን የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት መርጃ ሙዳየ ምፅዋት በአሁኑ ጊዜ አንሥተውታል:: ለምን ይሆን?

*ኤርምያስ – ከኮልፌ*

## ብርታቱን ይስጠን

ውድ አዘጋጆች፣ የመጽሔታችሁ ተከታታይ ነኝ:: በመሆኔም ዝግጅታችሁን እጅግ አደንቃለሁ:: ዛሬ ይህችን ደብዳቤ እንድጽፍ ያነሣሣኝ ግንቦት 12 ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩን አባቶቻችን ጉዳይ ነው:: ወንድሞቼ የእነዚህ ብፁዓን አባቶች ለኀልፈተ ሕይወት መዳረግ ለቤተክርስቲያናችን ታላቅ ጉዳት ነው:: ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ለመጨረሻ ጊዜ በማኅበራችሁ 7ኛ ዓመት የግንቦት ልደታ ክብረ በዓል ተገኝተው ያሰሙትን የመሰናበቻና የአደራ ቃል ከእኔ የበለጠ እናንተ የምትረሱት አይመስለኝም:: መርሳትም የለባችሁም:: ወንድሞቼ፣ አባቶቻችን እንደዚህ በየዓመቱና በየሁለት ዓመቱ ከመካከላችን እየተለዩን ነው:: ታዲያ እናንተም የጀመራችሁትን የአባቶችን የሕይወት ታሪክ በተከታታይ ማስነበብ አደራ እንዳታቋርጡ :: ለእኔ በተለይ አቡነ ኤልያስን ብታነጋግሯቸው ኖሮ ምንኛ በታደልን ነበር? ከአንደበታቸው የሚወጣው ቁም ነገር እኮ ለሕይወት መሠረት ነበር:: እንግዲህ ያለፈው አለፈ፣ ለአሁኑ ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ተርፈው የአባቶችን አስከሬን ይዘው የመጡትን ብፁዕ አቡነ ቀዉስጦስን የቀጣዩ መጽሔት እንግዳ ብታደርጓቸው ጥሩ ነው:: በሥርዓተ ቀብሩ ላይ ዘወትር እንባዬን የምታመጣ ቃል ተናግረዋልና:: «ወገኖቼ፣ እነዚህን ሁለት የቤተ ክርስቲያን ማሕቶተ ዕንቁዎች እንደቀላል ዕቃ በሁለት ሳጥን አሽጌ አምጥቼላችኋለሁ ተረከቡኝ» በማለት ዛሬም ቢሆን እንባ የሚያራጭ ንግግር ተናግረዋልና:: እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጠን::

*አሳምነው ውቤ አ/አ*

**ከአዘጋጁ:-**

በ«ቃለ መጠይቅ» ዓምዳችን አባቶችን መጠየቅን አናቋርጥም:: ብፁዕ አቡነ ኤልያስን ብትጠይቋቸው ኖሮ ላልከውም ብፁዕ አባታችን እንግዳችን እንዲሆኑ (የዚህ መጽሔት) ጠይቀናቸው መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ለእሳቸው ያልናቸውን ጥያቄዎች አዘጋጅተን በእሳቸውም ሆነ በእኛ የሥራ መብዛት ነገ ዛሬ ስንል ይህ አሰቃቂ አደጋ ደረሰባቸው:: ብፁዕ አቡነ ቀዉስጦስን ላልከው ደግሞ ይኸውና እንግዳችን ናቸው::

## ያንን ብትጠቀሙ

ሐመሮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የከፈታችሁት የቃለ መጠይቅ ዓምድ ይህቺን ደብዳቤ እንድጽፍ ምክንያት ሆነኝ:: በእውነቱ በዓምዱ የያዛችሁት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን የማስተዋወቁ ተግባር በጣም የሚያስመሰግናችሁ ነው:: የቤተክርስቲያን ልጆች አባቶቻቸው ከምን ተነሥተው እዚህ እንደደረሱ ሲያውቁ አባቶቻቸውን በማክበር አርአያቸውን ይከተላሉና:: በትዕቢት ተወጣጥሮ አባቶችን ለሚዘልፈው የእኔ ቢጤ ደካማም ወደ ልቡናው እንዲመለስ ያደርጋሉና:: በዚህም እኔ እጅግ ሳላመሰግናችሁ አላልፍም:: ነገር ግን አንድ ሀሳብ እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ:: ይኸውም ጥያቄዎቻችሁ የበለጠ ሰፋ እንዲሉና በርካታ ችግሮችን መመለስ እንዲችሉ ሊቃነ ጳጳሳቱ ከመጠየቃቸው በፊት «በሚቀጥለው ብፁዕ አቡነ እገሌን ልናነጋግር አስበናልና እንዲጠየቁላችሁ የምትፈልጉት ነገር ካለ በአድራሻችን ደውሉልን ወይም ጻፉልን »ብትሉ:: ምክንያቱም በአንዳንድ ቃለ መጠይቆቻችሁ መጠየቅ ያለባቸው ጥያቄዎች ሳይጠየቁ ሊያልፉ ይችላሉና:: ስለዚህ በተለይ ከየሀገረ ስብከታቸው ለሚነሡ ጥያቄዎች ያ ጥሩ መፍትሄ ነውና:: ስለዚህ ለጥያቄዎቻችሁ ብስለትና ጥንካሬ ያንን ብትጠቀሙ መልካም ነው እላለሁ::

*ዲ.ተፈራ አበራ*
*/ዲላ/*

## ዕፁብ

ሐመረ ኖኅ አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉትን ኖኅንና ቤተሰቦቹን ከጥፋት ውሃ እንደታደገቻቸው ሐመር መጽሔትም ብዙ ወጣቶችን ከጥፋት መንገድ መልሳ እውነተኛይቱን ሃይማኖት እያስተማረች ትገኛለች:: በተለይም በዓምደ ወራዙት ስር የሚወጡት ጽሑፎች ብዙ ያላወቅናቸውን ክርስቲያናዊ ምግባሮች አሳውቃናለችና ሥራችሁ ዕፁብ ነው ግሩበት እንላለን:: እግዚአብሔር አምላክ ሥራችሁን ይባርክ፣ እመቤታችን በምልጃዋ አትለያችሁ::

*ወልደገብርኤል*
*ምዕ/ሸዋ–ባንቱ*

## እውነታው ምን ያህል....

ውድ አዘጋጆች ዝግጅታችሁ በጣም አስተማሪ ነው:: ይህን ስል ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም:: በተለይ የተወሰኑትን ዓምዶች እጅግ አድርጌ እወዳቸዋለሁ:: ለምሳሌ እናስተዋውቃችሁ ዓምደ ወራዙትና ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ:: አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመጽሔቷ የኋላ ሽፋን ውስጥ ገጽ ላይ «ከመጻሕፍቶቻችን » በሚል ማውጣት የጀመራችሁት ነገር ያስደሰተኝ ገብቷል:: ሊቃውንት አባቶቻችን ትተውልን ያለፏቸው የዕውቀት ምንጭ የሆኑትን መጻህፍት ብዙዎቻችን አናውቅምና:: በዚሁ ቀጥሉ እያልኩ ባለፈው የሰባተኛ ዓመት ቁጥር ሁለት እትም ያስተዋወቃችሁትን «ትምህርተ መለኮት» መጽሐፍ እኔ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ባላውቅም በተለይ «እመቤታችንና ጥንተ አብሶ »በሚለው ላይ መጽሐፉ ችግር አለበት ይባላል:: እና እውነታው ምን ያህል ይሆን ?

*ታረቀኝ /ከአሦሳ/*

**ከአዘጋጁ:-**

ወንድማችን ታረቀኝ በመጽሔቱ ላይ እኛ ባስቀመጥነው መልኩ ከሆነ አባባልህ እውነታ አለው:: ይኸውም ከመግቢያው ላይ የሕትመት ዘመኑን ስናስቀምጥ 1983 ዓ.ም ብለናል:: በዚያ ጊዜ የታተመው መጽሐፍ አንተ ያልከው ሕፀፅ አለበት:: ነገር ግን ደራሲው የተሰጣቸውን አስተያየት ተቀብለው ለሁለተኛ ጊዜ ሲያሳትሙ አስተካክለዋል:: እኛም ልናስተዋውቅ የፈለግነው በ1991 ዓ.ም የታተመውን መጽሐፍ ነው:: በዚህ አጋጣሚ ለሌሎችም አንባብያን ይህንን ማስተካከያችንን ከይቅርታ ጋር እናስተላልፋለን::

# ክርስቲያንነት

መምህር ብርሃኑ ጎበና

«... በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ ብእኔ ባትኖሩ አትችሉም። እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።» *ዮሐ.15፥4–5*

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች አስቀድሞ ደቀመዛሙርት ይባሉ ነበር። ዮሐ. 4፥1፤ ማቴ.9፥10። የጌታም ደቀመዛሙርት ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ። የሐዋ. 11፥19–26።ስያሜውም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጥምቀት የክርስቶስ ወገኖች ለሆኑ ሁሉ መጠሪያ ሆነ።

የአንድ ነገር ስያሜ ሲጠራ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የነገሩን ምንነትና ማንነት ይገልጣል። ለምሳሌ፦ ሐኪም ሲባል ከአለባበሱ ጀምሮ ምን እንደሚመስል የሚታየንና በሕሊናችን ልንቀርጸው የምንችለው ነገር ይኖራል። ልክ እንደዚያው ሁሉ ክርስቲያን ሲባል የራሱ የሆነ መለያ አለው። «ስም ግብርን ይመራል» እንደሚባለው የክርስቶስ ደቀመዛሙርት የሆኑ ከሌላው የሚለዩበት መታወቂያ አላቸው። ግንዱ ክርስቶስ ነውና ቅርንጫፍ የሆኑ ክርስቲያኖች የሚያፈሩት ፍሬ የተለየ ነው። "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ" ያለውን ጌታ የሚከተሉ የቅድስናን ፍሬ ያፈራሉ። 1ጴጥ.1፥15።

ይሁን እንጂ ክርስቲያንነት የራሱ የሆነ መመዘኛና መለያ አለው። ስለዚህ እውነተኛውን ክርስቲያን ከሌላው መለየት ያስፈልጋል። ለመሆኑ ክርስቲያንነት በምን ይለካል? እውነተኛ ክርስቲያንስ ማነው? ቃለ እግዚአብሔርን መሠረት በማድረግ እነዚህን ጥያቄዎች አጠር አድርገን ለመመለስ እንሞክራለን። እውነተኛ ክርስቲያን፦

## ሀ. ኃጢአትን ወዶ ለምዶ የማይሠራ፦

ከእግዚአብሔር በጥምቀት የተወለደ ክርስቲያን የኃጢአት ሎሌ ከቶ አይሆንም። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በቀዳማዊ ክታቡ ላይ እንዳሰፈረው «በእርሱ (በክርስቶስ) የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፥ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አያውቀውምና። ልጆች ሆይ ማንም አያስታችሁ እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው። ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፤ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና። «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም። ዘሩ በእርሱ ይኖራልና። በእግዚአብሔር ተወልዷልና። ... ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም። ዘሩ በእርሱ ይኖራልና። በእግዚአብሔርም ተወልዷልና። ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም»/ ዮሐ.3፥4–10/።

ህብተ ወልድና ስመ ክርስትናን አግኝቶ ነገር ግን በኃጢአት ባሕር ጠልቆ የሚዋኝ ሰው ክርስቲያን ነኝ ቢል ስሙን ተሸክሞታል እንጂ አይድንበትም። ስለዚህ በንስሐ ከጠለቀበት የኃጢአት ባሕር ሊወጣና በንስሐ ሕይወት ሊኖር ይገባዋል።

## ለ. በቦታና በጊዜ የማይለወጥ

ለክርስትናችን ጊዜና ገደብ የምናበጅለት አይደለም። ክርስቲያን በማንኛውም ጊዜ በየትኛውም ቦታ ክርስቲያንነቱ የተጠበቀ ነው። ክርስቲያን ካለበትና ካየው ሁሉ ጋር እየተለዋወጠ ዘመን የወለደውን ጊዜ የወደደውን የሚከተል ሊሆን አይገባውም። መነሻውም ሆነ መድረሻው ሕገ እግዚአብሔር ነው። ጊዜ ሲለዋወጥ አብሮ የሚለዋወጥ አይደለም። «በጊዜውም አለጊዜውም ጽና... ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፣ ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ፣እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስማተሪዎችን ያከማቻሉ» 2ጢሞ 4፥2–4 ፤ እንዳለው ቅዱስ ጳውሎስ ህብት ሲያከማቹ የሥልጣን ኮርቻ ላይ ሲፈናጠጡ የቀደመ ሕይወታቸውን በመንቀፍ እንደ ሥጋ ፈቃዳቸው የሚጓዙላቸውን የሚከተሉና የቀደመውን እውነተኛ መንገድ የሚተው በስሙ ይጠሩበት እንጂ ከጸጋው የተራቆቱ የጥፋት ልጆች ናቸው።

እውነተኛ ክርስቲያን ግን በድህነትም ሆነ በብልጥግና፣ በተራ ሰውነትም ሆነ በሥልጣን ላይ እያለ የቀደመ እሱነቱን አይዘነጋም። በሚያገኘው ነገር ሁሉ ፈጣሪውን የሚያመሰግንና ሰውነቱን የማይረሳ ነው።

## ሐ. የራሱን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚቀበል

የሥጋ ስሜታችን በውስጣችን የሚፈጥራቸው ብዙ ፍላጎቶች አሉ። መልካም መስለው የሚታዩ የኋላ ኋላ ግን ግባቸው ከዘላለማዊ ሕይወት የሚያወጡ ለጊዜው ስሜታችንን ወጥረው ሕሊናችን እንዲቀበለው የሚያስገድዱ ነገሮች ፈታኝ ሆነው ይቀርባሉ።

እውነተኛ ክርስቲያን ግን በስሜት ብቻ ተመርቶ ለውሳኔ አይቸኩልም። ጊዜያዊ ጥቅም ለማግኘትም አይፋጠንም። ረጋ ብሎ ግራ ቀኙን ይመለከታል፣ በጥልቀት ይመረምረዋል፤ በሕይወቱ ላይ ሳንካ የሚያመጣበት ከሆነ ጥቅም የሚገኝበትንም እንኳ ቢሆን ይተወዋል። «ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደ ጉዳት ቆጥሬዋለሁ» የሚለውን የሐዋርያውን ትምህርት ያጤናል። ፊል.3፥8

## መ. የራሱን ክብር የማያስቀድም

ክርስቲያን እንደ ዓለሙ ጠባይ የሚወደስበትንና ስሙ የሚገንበትን ለመሥራት የሚሯሯጥ አይደለም። በሚያገለግለው አገልግሎት ሁሉ ሊከበርና ሊመሰገን የሚገባው ሁሉን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ስለሚያምን ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር እንዲቀርብ ያደረጋል።

መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» እንዳለው ሁሉ የእውነተኛ ክርስቲያን ፍላጎትም የእግዚአብሔር ታላቅነት የእርሱ ታናሽነት እንዲታወቅ ማድረግ ነው።/ዮሐ.3፥30/

የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት በሚያደርገው ጉዞ ትችት፣ ንቀት የመሳሰሉት ከሌሎቹ ቢሰነዘርበት ይህ የሥራው ፍሬ መሆኑን በመገንዘብ በፍጹም ደስታ ሊገፋበት እንጂ የይሉኝታ ገመድ ጠፍሮ ሊይዘውና ከዓላማው እንዲያፈገፍግ ሊያደርገው አይገባም።

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትን እዚህ ምዕራፍ ላይ ማስታወስ ያስፈልጋል። የእግዚአብሔርን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ ባገባ ጊዜ ንጉሥ ዳዊት ከካህናቱ ጋር አብሮ በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ሲዘል ሲዘምር በመስኮት ሆና የምትመለከተው ሜልኮል ናቀችው። እግዚአብሔርን በማመስገኑ፣ በተመስጦ ሲዘምር ልብሱ ስለወለቀበት «ምናምንቴዎች እርቃናቸውን እንደሚገልጡ የእስራኤል ንጉሥ በባሪያዎቹ ቈነጃጅት ፊት እርቃኑን በመግለጡ ምንኛ የተከበረ ነው!» አለችው።

ያ ታላቅ ሰው፣ ያ ቅዱስ ሰው ግን « በእግዚአብሔር ፊት ዘምሬያለሁ በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ላይ አለቃ እሆን ዘንድ ከአባትሽና ከቤቱ ሁሉ ይልቅ የመረጠኝ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፤ ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት እዘምራለሁ» የሚል አስተዋይነቱንና እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን የሚገልጥ መልስ ነበር የመለሰላት::

ትሑቱ ንጉሥ ከትቢያ አንሥቶ ለዚህ ክብር ያበቃውን አምላክ አልዘነጋም:: ትናንትን በዛሬ እሱነቱ አይቶ አልተኩራራም:: የዛሬው ክብር የትናንት ማንነቱን እንዲዘነጋ አላደረገውም:: የክብር ባለቤት፣ የምስጋና ጌታ ዘላለም ሊመሰገን የሚገባውን ቢቻለው ከዚህ የበለጠ እራሱን እንደ ትቢያ ቆጥሮ ሊያከብረው እንደሚገባው በአጽንኦት ትዕቢት ዙፋኑን ለዘረጋባት ለሜልኮል ሲያሳውቃት «አሁንም ከሆንሁት ይልቅ የተናቅሁ እሆናለሁ÷በዓይንሽም እዋረዳለሁ ነገር ግን በተናገርሽው ቈነጃጅት ዘንድ እከብራለሁ» 2ሳሙ. 6÷10 – 23:: ብሏል::

ራሱን ዝቅ አድርጎ ፈጣሪውን ያከበረው ዳዊት ዘመኑን ሁሉ የክብርን ሸማ ተጎናጽፎ እንደኖረ ትዕቢት የነገሠባት ሜልኮል ደግሞ መካን ሆና እንደሞተች የታወቀ ነው::

እናም በምድራውያን ዘንድ የተቸረን የከበሬታ ወንበር እንዳይነሣብን እየፈራንና እየተባን አዩኝ አላዩኝ በማለት የምንኖርበት ሳይሆን በነፃነት በፍጹም ደስታ የምንመላለስበት ሕይወት ነው ክርስትና::

## ረ. ታዛዥ የሆነ

«መታዘዝ ከመስዋዕት ይበልጣል» የሚለው የነቢዩ ሳሙኤል አነጋገር መሠረታዊ የክርስቲያኖች መርህ ነው:: 1ሳሙ.15÷22:: ገና በጥንተ ፍጥረት የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት የተቋረጠውና የጸብ መጋረጃ በሁለቱ መካከል የተጋረደው ባለመታዘዝ ነው:: «ይህን አትብላ» የሚለውን ትእዛዝ መጣስ መላው የሰው ዘር ለ5,500 ዘመናት በእግረ አጋንንት እንዲቀጠቀጥና ከጸጋ እግዚአብሔር ተራቁቶ እንዲኖር አድርጎታል::

ዛሬ ያ የቀድሞ ጸጋችን በጌታችን ተመልሶልናል:: በማይታዘዙ ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚወርድባቸውም ተነግሯል:: /ኢሳ.1÷19–20/ :: ስለዚህ ክርስቲያን ታዛዥ ሆኖ የሚኖር ነው:: የታዛዥነት ባሕርይ የእውነተኛ ክርስቲያን አንዱ መለያ ነው::

ቅንነት ስብእና ካለው ክርስቲያን ሁሉ ታዛዥነት አይጠፋም:: በታዛዥነታቸው ከቅዱሳት አንስት እነ ሣራ፣ ከቅዱሳን አበው እነ ይስሐቅ ተመስግነውበታል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና» በማለት አሳስቧል:: ኤፌ. 6÷1::

ዳሩ ግን ታዛዥነታችን በጌታ ቃልና ሕግ ላይ ተመስርቶ ለሚመጣ እንጂ ከእግዚአብሔር ሕግ በሚያ ስወጣን መንገድ አይደለም::

## ሰ. ታማኝ የሆነ

የተሰጠውን አደራ በብቃት የተወጣን አገልጋይ « አንተ በጎ ታማኝ አገልጋይ በጥቂት ታምነሃል፤ በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» በማለት ጌታ በታማኝነቱ ጸንቶ ለተገኘው አገልጋይ መናገሩ በወንጌል ተዘግቧል:: ማቴ.25÷23 ::

ታማኝነት አንዱ የክርስቲያንነት መስፈርት ነው:: ክርስቲያን በሥጋዊም ይሁን በመንፈሳዊ ረገድ ታምኖ በተሰማራበት የሥራ መስክ ሁሉ ታማኝነቱን ሊያስመሰክር ይገባል:: ታማኝነቱ ዘር፣ ጎሳ፤ ዝምድናና፣ ጓደኝነት መርጦ ሳይሆን ክርስቲያንነቱ አስገድዶት የሚያደርገው ሊሆን ይገባል::

ለትዳር ጓደኛው፣ ለተጣለበት ኃላፊነት፣ ለተሰጠው አደራ ባጠቃላይ ለሁሉ ነገር ታማኝ ይሆን ዘንድ የክርስትናው ሕይወት ያስገድደዋል:: « በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ÷ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» መባል የሚቻለውም በተሰጠን ነገር ታማኝ መሆን ስንችል ነው::

## ሸ. ከቅድሳት መጻሕፍትና ከመንፈሳውያን አበው ጋር ግንኙነት ያለው

የክርስቲያን የዕለት ኑሮ ስኬታማ እንዲሆን ከእግዚአብሔር ቃል ሊርቅ አይገባም:: « የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ÷ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፤» በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስገነዘበንም ለዚህ ነው:: 2ጢሞ.3÷16::

በጥሬ ምንባብ ብቻ በመመራት ስተን እንዳናስት ምሥጢሩንና የተሰወረውን የሚገልጡ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ከጎናችን ሊኖሩ ይገባል:: ስለዚህ የመጻሕፍትን ምሥጢር ለመረዳት አባቶችን መጠየቅ ያስፈልጋል:: «አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል::»

እንግዲህ «አብርሃም አባት አለኝ» እንደሚሉት ፈሪሳውያን ክርስቲያንነት በስም ብቻ የምንኩራራበት አይደለም:: «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» እንደ ተባልነው ብርሃናችን በሰው ፊት ሊያበራ፤ ማንነታችንም በኑሮአችን ሊገለጥ ይገባል:: ማቴ.5÷14–16:: ያን ጊዜ ነው ጽድቃችን ጌታ ዘወትር ሲወቅሳቸውና ሲገስፃቸው ከነበሩትና ጉዞአቸው ሁሉ የታይታና የግብዝነት ከነበሩት ፈሪሳውያን በልጦ መንግሥተ ሰማያት የምንገባው:: ማቴ.5÷20:: ስለዚህ ሀብተወልድና ስመ ክርስትናን ያገኘን ወገኖች ሁሉ ከዚህ አንፃር ራሳችንን ልንመረምር ያስፈልጋል:: ለመሆኑ ስማችንና ግብራችን ተገናኝቷል?

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## አንደበት

*ልጓም ከሌለው ሁሉን የሚበላ
እሳት ነው
*ሸንጋይ ከሆነ እግዚአብሔር ይጠየፈዋል
* በጻድቅ ዘንድ የጥበብ ሁሉ
ምንጭ ነውና
ብዙ ሰዎችን ይመግባል
* በሰነፎች ዘንድ ግን የሀሜት
ጐተራ ነውና
ብዙዎቹን ያሰናክላል
* ትሑት ከሆነ የእግዚአብሔርን
ምሕረት ያገኛል
* በምሥጋና ከተጋ በእግዚአሔር
ይጐበኛል
* ለጽድቅም ሆነ ለኩነኔ ምክንያት
ነውና
አልገራ ካለህ ጠባቂ
እንዲያኖርለት
ለፈጣሪህ አደራ ስጠው ::

# ነገረ ማርያም በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ

(*ካለፈው የቀጠለ*)

•

*ከመሪጌታ ዓምደወርቅ እስጢፋኖስ*

ባለፈው እትማችን «ያሬድ» ስለሚለው ስም አሰያየምና ትርጓሜ በሰ ጠነው ማብራሪያ ጀምረን ቅድስተ ቅዱ ሳን ድንግል ማርያም ከዓለም መፈጠር በፊት በአምላክ ኅሊና ስለመኖሯ ኢት ዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በድጓው እንዴት እንደተናገረ አይተ ናል:: እንዲሁም ይኸው አባት እመቤ ታችን ቅድመ ዓለም በአምላክ ኅሊና ከመታሰብ እንዴት ሰው ሆና እንደ ተፈጠረች በጸዋትዎ ዜማው ያመሰጠ ረውን ተመልክተናል፤ ዛሬም ካቆምንበት እንቀጥላለን::

*ድጓ 4. ይቤ ዳዊት በመዝሙር «መሠ ረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን፣ ወካ ዕበ ይቤ ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል ወይቤ ዝየ አኀድር፣ እስመ ኀረይክዋ እግዚአ ለሰንበት በከርሣ ተጸውረ ሰማየ ወም ድረ ዘውእቱ ፈጠረ::»*

<u>ትርጉም:</u>– ዳዊት በመዝሙር እንዲህ ብሎ ተናገረ «የቤተመቅደስ መሠረቶቿ ለእግዚአብሔር የቅድስናው ቦታ በተ ለዩ ተራሮች ውስጥ የጸኑ ናቸው::» ዳግመኛም ልዑል ማደሪያውን ለየ ሲል ተናገረ መርጫታለሁና በእሷ አድራለሁ አለ» ለማደሪያነት የመረጣት ሰማይንና ምድርን የፈጠረ የሰንበት ጌታዋ በማ ኅፀኗ አደረ::

- *መሠረታት /መሠረቶች/ አልዓዛር ቅስራና ኢያቄም*
- *ማኀደር /ማደሪያ/ ማኅፀንዋ ነው::*

ልዑል ራሱ መረጣት የተባለው የአብ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን ሲሆን በዚህም መሠረት ለማደሪያነት መረ ጣት የሚለውን «ሰማይና ምድርን እርሱ ቅሉ ፈጠረ በማኅፀኗ አደረ ብሎ ገጥሞ ያነበዋል»

ይህ ምሳሌ ነው:: ቤተመቅደስ የድን ግል ማርያም ሁለንተና አድባር ቅዱሳን /የቅዱሳን ተራሮች/ ከአብርሃም እስከ ኤልዩድ ያለው ሐረግ ትውልድ ማቴ.1÷1–16 አልዓዛር፣ ቅስራና ኢያ ቄም፤ ማኅደር የማኅፀንዋ፤ ልዑል ራሱ የአብ አካላዊ ቃል ምሳሌ ሲሆን ለማደ ሪያነት የመረጣት «ሰማይና ምድርን እርሱ ቅሉ ፈጠረ በማኅፀኗ አደረብሎ ገጥሞ ያነበዋል::

*3.አዳም በልጅ ልጁ እንደሚ ድን የተሰጠው የ5,500 ዘመን ተስፋ ድኅነት::*

*«ምስሌከ ቀዳማዊ በዕለተ ኃይል በብርሃናሙ ለቅዱሳን ወለድኩከ እምከ ርሥ እምቅድመ ኮከበ ፅባሕ ጸረቶ በከ ርሣ ውእቱኒ ቀደሳ ወይቤሎ ለአቡነ አዳም እትወለድ እም ወለትከ ወእጽ ሕከ ውስተ መርሕብከ፣ ወእከውን ሕፃነ በእንቲአከ» መዝ.109÷*

<u>ትርጉም:</u>– ቀዳማዊ ቃል ሆይ ካንተ ጋር በዕለተ ፍጥረት (በኃይል ቀን) በቅ ዱሳን ብርሃን ከአጥቢያ ኮከብ መው ጣት በፊት ከባህርዩ ወለድኩህ፣ በማሕ ፀንዋ ተሸከመችው እርሱም ለይቶ መረ ጣት፤ አባታችን አዳምን ተናገረው፣ ከልጅህ እወለዳለሁ በሜዳህም እድሃለሁ (እመላለሳለሁ) ስለአንተም ሕፃንን እሆ ናለሁ «ወድቆ ቢነሡ በእጅ ደህይቶ ቢከብሩ በልጅ» እንዲሉ አዳም በጥንተ በደል ምክንያት ከገነት ተሰዶ ወደ ምድረ ፋይድ ወርዶ 5,500 ዘመን እስከ ሚፈፀም ከድኅነት ተቆራምዶ ከኖረ በኋላ የአብ አካላዊ ቃል የሰው ፍቅር ቢያገብረው ልዑል ዙፋኑን ዝቅ አድርጎ ልጁ ከሆነችው ከቅድስት ድን ግል ማርያም ተወልዶ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ከነልጅ ልጁ ከዲያ ብሎስ የባርነት ቀንበር ነፃ አደረገው::

ቀሌምንጦስም ለመምህሩ ለቅ ዱስ ጴጥሮስ ጌታ የገለጠለትን የዚህን ኃይለ ቃል መሠረት እንዲህ ፅፎታል *«ወእምድኅረ ሐሙስ መዋዕል መንፈቀ መዐልት እምሕረከ ወእሠህለከ በብዝኀ ሣህልየ ወምህረትየ እወርድ ውስተ ቤትከ ወአኀድር ውስተ ከርሥከ ኦ አዳም እትወለድ ከመህፃን በእንቲአከ»*

<u>ትርጉም:</u>– አምስትቀን ተኩል ከሆነ በኋላ እንደ ቸርነቴና ይቅርታዬ ብዛት እምርሀለሁ ይቅርም እልሃለሁ ወደ ቤትህ ወርጄ በባህርይህ አድራለሁ አዳም ሆይ! ስለ አንተ እንደ ህፃን እወ ለዳለሁ::

አንድ ሺህ ዘመን በጌታ ዘንድ እንደ አንዲት ቀን ናትና በአምስት ቀን ተኩል ይቅር እልሃለሁ የሚል ቃል ኪዳን ለአዳም ገባለት አንድ ሺህ ዘመን በጌታ ዘንድ እንደ አንዲት ቀን መሆንዋን ሲያስረዳ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም «የሰው ልጆች ተመለሱ ትላለህ»

ሺህ ዓመት:– በአንተ ፊት ትናንት እንዳለፈች ዕለት ናትና መዝ.89÷4 ብሏል አሁንም ወደ ቅዱስ ያሬድ ዜማ ስንመለስ እንዲህ ይላል

*በከመ ይቤ በነቢይ ይመጽእ መድኅን እምፅዮን ወያአትት ኃጢአት እም ያዕቆብ መፅአ ከመ ይሥዐር ጣዖተ መጽአ*

<u>ትርጉም:</u>– መድኅን ከፅዮን ይመጣል ኃጢአትንም ከቤተ ያዕቆብ ያስወግዳል ተብሎ በነቢይ አድሮ እንደተናገረ ጣኦትን ያጠፋ ዘንድ መጣ

* *መጽአ ከመ ይሚጥ ልበ አበው ኀበ ውሉድ ወኀሊና ከሃድያን ውስተ ፍኖተ ጻድቃን ለሐከ ለአዳም መሬ ታዊ ወአርአየ በኅዕሌሁ ማርያምሃ መሬተ ሠናይተ*

የከሀድያንን ሐሳብ ወደ ጻድቃን ጎዳና የአበውን ልቡና ወደ ልጆች ይመልስ ዘንድ መጣ መሬታዊ አዳ ምን ፈጠረ በላዩ ላይም ያማረች በጎነት ያላት መሬት ማርያምን አሳየ

* *ወእምዝ አርአየ እግዚአብሔር በኅ ዕሌሁ ዐሠርተ ወኃምስተ ነቢያተ ዐሠርተ ወክልኤተ ሐዋርያተ* ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር ዐሥራ አምስ ቱን ነቢያትና ዐሥራ ሁለቱን ሐዋ ርያት አሳየ

* *ወእምዝ አርአየ እግዚአብሔር ካልዐ ሰብዓ ወክልኤተ አርድእት ሠልስተ ምዕት ወስሙንተ እለ ኀብሩ ሃይ ማኖተ*

ከዚህ በኋላም ሌሎች ሰዎችን ሰባ ሁለት አርድእትንና በሃይማኖት የተባበሩትን ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንትን አሳየ

* *አርአዮ ለሙሴ ደብተራ ፍጽምተ ወለአብርሃም አርአዮ ቀዳሚተ ሕግ ወሥርዓተ ወአኮቴተ ሴሞሙ ጳጳ ሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ እለ ያዐርጉ መሥዋዕተ ንጹሐ*

ለሙሴም ፍፅምት የሆነች ድንኳን /ደብተራ ኦሪትን/ አሳየው ለአብ ርሃም «በካህኑ በመልከ ጼዴቅ አማ ካይነት ኅብስተ አኮቴትን ጽዋዐ በረ ከትን/ በወይን በስንዴ አስታኩቶ የአማናዊ መሥዋዕት ሥርዓትንና ቀዳማዊት ሕግን አሳየው ንጹሕ መሥዋዕትን የሚያሳርጉ ዲያቆናት

ቀሳውስት ጳጳሳት አድርጎ ሾማቸው::

* *ነሥአ ኅብስተ አእኰተ ባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ሥጋሁ ቅዱስ ለሐዲስ ሥርዓት ኢየሱስ መርሐ ኮነ*

ኅብስቱን አንሥቶ /በምሴተ ሐሙስ/ አመሰገነ ባረከ ፈተተ ለደቀመዛሙርቱ ቅዱስ ሥጋውን ሰጣቸው:: ለሐዲስ ሥርዓትም አብነት ሆነ::

እግዚአብሔር አዳምን ከአራቱ ባህርያተ ሥጋና ከሦስቱ ባህርያተ ነፍስ:- ማለት:- 1. ባህርያተ ሥጋ:- (መሬት፣ ውኃ፣ ነፋስ፣ እሳት)

2. ባህርያተ ነፋስ:- (ነባቢት፣ ለባዊት ሕያዊት) ከፈጠረ በኋላ በጎንት ያላት መሬት እመቤታችንን በላዩ አሳየ ሲል የተናገረው «ማርያምስ ከጥንት ጀምሮ በአዳም ባህርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ታበራለች» ተብሎ በስ ውር የተነበየውን አጉልቶ ለማሳየት ሲሆን አንዲት ሐረግ ለመምዘዝ ብዙ አሥራውንና አዕፁቅ መበዝበዝ የነበረ ያለ የሚኖር በመሆኑ ሌሎችንም በእግዚአብሔር ብርዐ-ቅድስና አምላካዊ ሕግን በሚፈፅሙ ምእመናን ስሌዳ ልቡና ስሞቻቸው የተመዘገቡ ቅዱሳንን በሥነ ተፈጥሮ ቅንጣትነት በአዳም ሥርወ ባህርይ ውስጥ አቆጥቁጠው እንዲታዩ ያስተምረናል::

## 4. የነቢያት ትንቢት

*«አይ ይእቲ ዛቲ መድኃኒት እንተ ኀሠሥዋ ወያጽዋ ነቢያት ወይቤሉ ለኖኅ አመ አይኅ ግበር ታቦተ በዘትድኅን፣ እትአመን ባቲ እስመ አርአያ መስቀል ይእቲ አክሊለ ተቀጺላ ታንሰሱ»*

<u>ትርጉም</u>:- ነቢያት በእግረ-ትንቢት ዞረው የሿት (የፈለጓት) ይህች መድኃኒት ምንድን ናት? ኖኅንም እንዲህ አለው በጥፋት ውኃ ጊዜ ማደሪያ መርከብን ሥራ በምትድንበት ገንዘብ፣ እኔም አምንባታለሁ የመስቀል ምልክት ናትና የክብር አክሊልን ተቀዳጅታ ትመላለሳለች ይህች መርከብ ነቢያት በእግረ ትንቢት ዞረው የፈለጓት መድኃኒት እመቤታችን ናት:: በመድኃኒት ድውያነ ሥጋ ከፅኑ ደዌ ሥጋቸው እንዲድኑ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተገኘው አማናዊ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስም በጥንተ በደል ምክንያት ድውያነ ነፍስ ቁሱላነ ነፍስ ሆነው ወደ ሲኦል ወርደው የነበሩ የአዳም ልጆች በሙሉ ከቁስለ ነፍስ ከደዌ ነፍስ ድነው ወደ መጀመሪያይቱ የአዳም ቦታ ተመልሰው ገብተዋልና::

ኖኅም በሠራው መርከብ የዳኑ ነፍሳት ምድርን እንደመሏት፣ ሊቃውንት በየድርሳናቸው ሐመረ ኖኅ ብለው ከሰየሟት ከድንግል ማርያም በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የተወለደው አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ትርክዛ እየቀዘፈ ከባህረ እሳት ነፃ ያወጣቸው ነፍሳት ገነትን መልተዋታል::

ነፍሳት የዳኑባት መርከብ ምሳሌዋ መስቀል እንደሆነ፤ የአብ አካላዊ ቃል ዓለሙን ሁሉ ያዳነው የእመቤታችንን ሥጋ ለብሶ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ነው::

ቀጥሎ የምንመለከተው ቅዱስ ያሬድ በኋላ ዘመን ስለ እመቤታችን መገኘት ነቢያት የተናገሩትን ትንቢት መሠረት አድርጎ የዘመረውን ነው::

*ትወፅእ በትር እም ሥርወ ዕሴይ ወየዐርግ ጽጌ ይእቲ በትር አምሳለ ማርያም ቅድስት ይእቲ ወጽጌ ዘወፅአ እምኔሃ አምሳሉ ለወልድ ኅደረ ላዕሌሃ ቃል ሥጋ ኮነ ወተወልደ እምኔሃ::*

<u>ትርጉም</u>:- ከነገደ ዕሴይ በትር ትወጣለች አበባም ከእሷ ይወጣል ይህችውም በትር የማርያም አምሳያ ናት ከእሷ የሚወጣው አበባም የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው:: «በትሯ የእመቤታችን ጽጌ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ሆነው ቢገኙ ዘመኑ ወሩ ዕለቱ በደረሰ ጊዜ» «የአብ አካላዊ ቃል ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ» በማኅፀኗ አድሮ ሰው ሆኖ ከእሷ ተወለደ::

*ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ «ወትወፅእ በትር እም ሥርወ እሴይ ወየአርግ ጽጌ እምኔሃ»* ማለት «በትር ከእሴይ ሥር ትወጣለች አበባም ከእርሷ ይወጣል» ብሎ የተናገረውን ደረቅ ንባብ ትንቢት፣ ቅዱስ ያሬድ በሙሉ ምሳሌውን ከነምሥጢሩ አመጣው የብሉይ ኪዳን መተርጉማንም ይህንኑ ተከትለው «በትር እመቤታችን ከነገደ እሴይ ከባህርይ እሴይ ትወለዳለች ፅጌ ክርስቶስም ከእርሷ ይወለዳል» ሲሉ አመስጥረውና አራቀው ስለተረጐሙት

የነቢዩ አስከሬናዊ ደረቅ ትንቢት ትርጓሜያዊ ሰብእናን ነሥቶ ምሥጢራዊ ነፍስን ዘርቶ ሰማዊ ርቀቱ ጎልቶ ወርቃዊ አካል ንባብን ገዝቶ ከተቀበረበት አዘቅተ ንባብ በእውን እንዲነሣ አድርጎታል:: ኢሳ.11÷1 ዳግመኛም *«... መንክር ተአምሪሁ ለመድኃኒነ በከመ ወጽአት በትር እምሥርወ ዕሴይ፣ በአምሳለ በትረ ያዕቆብ::*

*በዘይርዒ አባግዒሁ ይእቲኬ ማርያም ይእቲ፤ ወበ እንተ ዘይቤ ትወጽእ በትር ወየዐርግ ጽጌ ውእቱኬ ዋህድ ውእቱኬ ወልደ አምላክ ውእቱ»*

<u>ትርጉም</u>:- «...በጎቹን በሚጠብቅበት ገንዘብ በያዕቆብ በትር አምሳል ከዕሴይ ባህርይ በትር እንደወጣች የመድኃኒታችን ተዓምሩ ድንቅ ነው፤ ይህችውም በትር እርሷ ድንግል ማርያም ናት:: በትር ትወጣለች አበባም ከእርሷ ይወጣል» ብሎ ስለተናገረው ያው አንዱ ወልደ አምላክ ነው:: ይህም ምሳሌ በትር የእመቤታችን፣ ያዕቆብ የጌታ አባግዕ (በግ) የምእመናን::

ያዕቆብ ሦስት ኅብረ መልክ ባላት በትሩ በጎቹን እንዲጠብቅ፣ ጌታም ንፅሐ ነፍስን፣ ንፅሐ ሕሊናን፣ ንፅሐ ሥጋን አስተባብራ በያዘች በእመቤታችን ጸሎት የተማፀኑትን የሠላሴ ያመኑትን ይጠብቃል ያስጠብቃል::

ዳግመኛም ይህንን ቃል ከፍ ብሎ በሙሴና በአሮን ዝቅ ብሎ በዕሴይ ቅጂ በሆነው በዳዊት አንፀባርቆ ተናግሮታል::

*«ማርያምስ እምነ ሥርው ለዳዊት እንተ ሠርፀት ለሕይወት እምሙላሙሴ ወለአሮን ካህናት ሰመያ ማኅደረ መለኮት»*

<u>ትርጉም</u>:- ደብተራ አሪት ካህናት የሚሆኑ የሙሴና የአሮን እናታቸው የምትሆን ማርያምስ ለድኅነተ ዓለም ከዳዊት ባህርይ የተገኘች ናት፣ መለኮትም ማደርያው አደረጋት::

የእመቤታችን የዘር ቅጂዋ ከዕሴይ ወደ ዳዊት፣ ወደ ሰሎሞን ከዚያም ሲወርድ ሲዋረድ እስከ አልዓዛር፣ ከአልዓዛር ሴት ልጁ ወደምትሆን ወደ ቅሥራ፣ ከቅሥራ ኢያቄም የደረሰ ጠቋሚ ቀስታችን ወንጌላዊ ማቴዎስ የፃፈው የዘር ሐረግ ነው:: በሌላ አቅጣጫ ለሙሴና ለአሮን እናታቸው መባሏ ቅድመ ዓለም በኀሊና አምላክ መኖሯ እናት ለመሰኘት የመብቃት ዓይነተኛ መለኪያ ከመሆኑም በላይ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ነፍሳትን ከዲያብሎስ ቁራኝነት ያወጣ የእርሷን ሥጋ ከለበሰ በኋላ መሪር ሞተ ሥጋን በፈቃዱ ቀምሶ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ስለሆነ እናት መባል ቢያንሳት እንጂ አይበዛባትም::

ሰሎሞንም ከአድባረ ሊባኖስ እንደምትገኝ የተናገረውን ሊቁ እንደሚከተለው ገልጦታል::

*«እምርእሰ ሳኔር ወኤርሞን እምግበበ አናብስት ወእም አድባረ አናምርት ወፃእኪ፣ »*

<u>ትርጉም</u>:- ከሳኔርና ከኤርሞን ጫፍ ከሚገኙት ከአናብስት ጉድጓዶችና ከአናምርት ተራሮች ወጣሽ፤ መልካሚቱ ርግቤ ሆይ፣ ፍፅምቲቱ ርግቤ በፍፁም አደስትብሻለሁ::

አሁንም ከሊባኖስ ሳይወጣ በሌላ ስፍራ ስለ እመቤታችን እንዲህ ይላል:: *«እምሊባኖስ ትወፅዕ መርዓት ወትወፅዕ እምግበበ አናብስት እምታዕካ ዘነገሥት»*

<u>ትርጉም</u>:- ሙሽራ ከሊባኖስ ትወጣለች ከአናብስትም /ወደ ገጽ 13 ዞሯል/

# ነገረ ድኅነት

ሁለተኛ ክፍል

(ከባስልዮስ ዘቂሳርያ)

## ለአዳምን ሊያድነው የሚችለው ማነው?

ባለፈው እትማችን

የድኅነትን ትርጉም፣ የአዳም ውድቀት ማለት ምን እንደሆነ፣ ዕፀ በለስ የተፈጠረችበትን ምክንያት፣ ለአዳም መውደቅ ተጠያቂው ማን እንደሆነ፣ በዝርዝር ተመልክተናል።

አዳም አባታችን ጸጋው ተገፏል፣ [ራቁቱን ሆኗል፣ ኃይሉን አጥቷል፣ እንግዳ ሆኗል] ባሕርይው ጐስቁሏል [ሰላሙን አጥቷል፣ ነጻነቱን አጥቷል፣ ሕያውነትን አጥቷል፣ እግዚአብሔርን መምሰልን አጥቷል፣ ባለዕዳ ሆኗል፣ ገነትን አጥቷል]

ታዲያ አዳምን ከዚህ ሁሉ ዕዳ አውጥቶ ሞትን አሸንፎ፣

በሐዲስ ተፈጥሮ ሊፈጥረው የሚችል፣ ወደ ወጣበት ርስት የሚመልሰው በለጸጋ የሚያደርገው ማነው?

### ነቢይ ነውን?

ነቢያት ወደ ሕዝቡ ይላኩ የነበሩት ለሁለት ምክንያቶች ነበር። የመጀመሪያው ለትምህርት ለተግሳጽ ነው። ሙሴና ሳሙኤል ሕዝቡን ይመሩ÷ ይመክሩ ይገሰጹ እንደነበረው ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ ከሚመጣው ቁጣ ይተርፍ ዘንድ መፃኢያቱን እየነገሩ ይመክራሉ ይገስፃሉ ያስጠነቅቃሉ። ዳንኤልና ኤርምያስ ኢሳይያስና ሕዝቅኤል በሕዝበ እሥራኤል ላይ ከሚደርሰው ጉዳይ አንሥቶ በዓለም ላይ እስከሚፈጸመው ድረስ በትንቢት መጽሐፋቸው እንደገለጡት።

ነቢያት በየዘመናቱ ከደረሰውና ከሚደርሰው መከራ በምክራቸውና በትምህርታቸው በጸሎታቸውና በምልጃቸው ሕዝቡን ከመዓት ከቁጣ ከሞት አድነዋል። መዝ.105÷23።

ይህ ሁሉ የነቢያት ተጋድሎ አዳምን ከሲኦል ወደገነት ሊመልሰው፣ ከጥንተ አብሶ (ከውርስ ኃጢአት) አላቅቆ ነፃነት ሊሰጠው፣ ዕዳ ሞትን ሊከፍልለት አልቻለም።

እነርሱ ከአዳም ዕዳ ነፃ ስላልነበሩ ባለዕዳ ባለዕዳን ሊያድነው አልቻለም። መዝ.63÷5። በመሆኑም ለአዳም ከነቢያት የሚበልጥ አስፈለገው።

### መልአክ ነውን?

መላእክት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሚላላኩ (ሉቃ.1÷8–19) የሰዎችን ጸሎት የሚያሳርጉ (ራእ 8÷1–5)፣ ስለ ሰዎች ኃጢአት የሚያማልዱ (ዘካ.1÷12–17)፣ ሰዎችን ከክፉ መከራ የሚያድኑ (ዘፍ.48÷16)፣ ከታናሽነት እስከ ዐዋቂነት የሚመግቡ (ዘፍ.48÷15)፣ በሰዎች ንስሐ መግባት የሚደሰቱ (ሉቃ.15÷7፣10) ናቸው። በዚህ ሁሉ ተልእኮዋቸው የሰውን ልጅ በገነት ሳለ ከገነት ከተባረረም በኋላ ሲራዱት፣ ሲማልዱለት፣ መንገዱን ሲመሩት ኑረዋል።

ይህ ሁሉ ቢሆንም መላእክት አዳምን ከሲዖል ሊያወጡት፣ ገነትን ሊከፍቱለት፣ ሞትን ሊደመስሱለት አልቻሉም። ምክንያቱም:–

1. ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ሲጣላ የእግዚአብሔር ከሆነው ጋር ሁሉ ተጣልቷል። የእግዚአብሔር መላእክት ወደ አዳም ይመጡ ነበር እንጂ አዳም ወደነርሱ መሄድ አልቻለም።
2. በአዳም የሞት ፍርድ የፈረደው እግዚአብሔር በመሆኑ እግዚአብሔር የፈረደውን ፍርድ መላእክት ማንሣት አልቻሉም።
3. ከገነት አዳምን ያስወጣው በመልአኩ ሰይፍ ገነትን ያስጠበቀ፣ እግዚአብሔር በመሆኑ እግዚአብሔር ያስወጣው አዳም መላእክት ሊመልሱት አልቻሉም።

በመሆኑም ለአዳም ከመላእክት የበለጠ ያሻው ነበር

### መሥዋዕተ ኦሪት ነውን?

ከዘመነ አበው እስከ ዘመነ ካህናት በተራራዎችና በቤተመቅደስ መሥዋዕተ አበውና መሥዋዕተ ኦሪት ቀርበዋል። የበግና የላም የፍየል መሥዋዕት ግን አዳምን ሊያድነው አልቻለም።

1. የሚሠዋው መሥዋዕት የፍጡር በመሆኑ ፍጡርን ፍጡር ማዳን አይችልምና ሊያድነው አይችልም። ፍጡርን ፍጡር ሊያድነው ቢችል ኖሮ ፍጡርን ፍጡር ሊፈጥረው በቻለም ነበር። ከየት እንዳመጣው፣ ምን እንደሰጠው ከሚያውቅ በቀር አዳምን ወዴት እንደሚወስደው ምንስ እንደሚመልስለት ሊያውቅ የማይችል አንዳች የለምና። በመሆኑም የፍጡር መሥዋዕት ፍጡርን ሊያድነው አልቻለም። (ዕብራ. 10÷1–5)
2. የሚሠዋው መሥዋዕት ሞት የሚያሸንፈው በመሆኑ ሞትን ድል አድርጎ አዳምን ከሞት ባርነት ሊያወጣው አልቻለም። በጉም ሆነ ፍየሉ ሟች ሙቶ በስብሶ የሚቀር የሞትን መውጊያ፣ የመቃብርን መዝጊያ ማሸነፍ የሚችል በመሆኑ ባለዕዳውን አዳም ትንሣኤን ሰጥቶ ከሞት ሊያወጣው አልቻለም።

በመሆኑም ከበግና ከላም ከፍየልም የበለጠ መሥዋዕት ያስፈልገው ነበር።

### እግዚአብሔር ነውን?

አዳምን ከምድር አፈር ያበጀው የሕይወት እስትንፋስንም የሰጠው እግዚአብሔር ነው። «አዳም ሆይ መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ» ብሎ የፈረደበትም እግዚአብሔር ነው። ሕያው አዳምን ሞት እንዲያሸንፈው ፍርድ የሰጠበትም እግዚአብሔር ነው። ስለዚህም ከመሬት ያበጀውን ወደ መሬት የመለሰውን መልሶ ከመሬት ለማንሣት ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሕይወት ለሰጠው ሰው ሞት የፈረደበት መልሶም ከሞት ቀንበር አላቅቆ ሕይወት መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

የቀደመው ሰው አዳም በእግዚአብሔር ተፈጥሮ በእግዚአብሔር የከበረ ነበር። የዳነው አዳም ግን «በፍጡር የተፈጠረ» በፍጡር «የዳነ» በፍጡር «የከበረ» በሆን አዳም ወደ ጥንተ ክብሩ ተመለሰ፣ ፍጹም ድኅነትን አገኘ ማለት ባልተቻለ ነበር። ምክንያቱም የቀደመው አዳም በእግዚአብሔር ተፈጥሮ በእግዚአብሔር ከብሮ የሚኖር በመሆኑ ከኋለኛው አዳም ይበልጣል ያሰኛልና ነው።

እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥር ማንንም አላማከረም፤ ሲፈርድበትም የማንንም ሃሳብ አልጠየቀም። በመሆኑም እንዴት እንደፈጠረውም እንዴት እንደፈረደበትም ምሥጢሩን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሊያድነው ወደ ጥንት ክብሩ ሊመልሰው ዕውቀቱም ጥበቡም ሥልጣኑም ያለው እርሱ ብቻ ነው።

ለአዳም ቀዳሚቷን ሕግ የሰጠ እግዚአብሔር ነው። አዳም ሕጉን በጣሰ ጊዜ የቀጣው እግዚአብሔር ነው። ሁለተኛዋን ሕግ የመስጠት ሥልጣን ያለውም እግዚአብሔር ነው።

ስለዚህም አዳምን ሊያድነው ከወደቀበት ሊያነሣው ወደ ጥንት ርስቱ ሊመልሰው «አ አዳም አይቴ ሀሎከ» እያለ የመጣው መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው ፍጡር – አይደለም፣ መልአክ – አይደለም ነቢይ – አይደለም፣ [ምንም እንኳ ነቢይነት ገንዘቡ ቢሆን ለነቢያትም ሀብተ ትንቢትን የሚሰጠው እርሱ ቢሆን]

### እግዚአብሔር ለምን ሰው ሆነ?

ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው። ከፍጥረት መካከል አሚልቶ አጠናቆ

ያውቀው ይመረምረው ዘንድ የሚቻለው የለም:: መንፈስ ቅዱስ የገለጠላቸው አበው የነገሩንን እነሆ::

- እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር «ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳልነ» ብሎ ከምድር አፈር አበጀው:: ይህ በአብ ልብነት አስበው፣ በወልድ ቃልነት ተናግረው፣በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት የፈጠሩት ሰው ቢወድቅ «ንግበር ሰብአ» ብሎ የተናገረው ቃል ወደ አዳም መጣ:: ከመሬት ያበጀው እጅ (ክንድ) ተዘረጋ::
- «አ አዳም መሬት አንተ ወትገብአ ውስተ መሬት» ብለው ሥላሴ በአብ ልብነት አስበው በወልድ ቃልነት ፈርደው፣ በመንፈስ ቅዱስ ሕያውነት፣ አጽንተውት የኖሩትን ፍርድ ሊያነሣ የፈረደበት ቃል ወደ አዳም መጣ::
- ዓለም በኃጢአቱ ምክንያት የእግዚአብሔርን ድምፅ ፈርቶ ይኖር ነበር:: ዘፍ.3÷10–13:: እሥራኤል እግዚአብሔር በሲና ተራራ በተናገራቸው ጊዜ ሙሴን «አንተ ተናገረን፤ እኛም እንሰማለን፤ እንዳንሞት ግን እግዚአብሔር አይናገረን» ዘጸ.20÷18 እንዳሉት:: ይህን የኃጢአት ፍርኃት ከሰዎች ያርቅ ዘንድ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ከእኛ ጋር ተገኘ:: (አማኑኤል) የሰው ቋንቋ እየተናገረ በሰው ሥርዓት ተመላለሰ:: ድምፁን አሰምቶ በበለስ ሥር የተደበቀውን አዳም ፈለገው:: አገኘውም::
- የሰው ልጅ በትእዛዛት የተሰጠውን ሕግ ይፈጽም ዘንድ አልቻለም፤ ሠርቶ ፍጹም አድርጎ ያሳየው የለምና:: በመሆኑም እግዚአብሔር ወደኛ መጥቶ ሠርቶ አዲሲቷን ሕገ ወንጌልን ሰጠን::

*[የቀረውን መንፈስ ቅዱስ ይግለጥልን]*

## *እግዚአብሔር ሰውን እንዴት አዳነው?*

አበው እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል ይላሉ:: ምክንያቱም ባሰቡት ቁጥር ኀሊናን የሚያስደንቅ ምሥጢር ተፈጽሟልና::

- የአዳምን ዕዳ ፍጡራን ሊከፍሉት አልቻሉም:: እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ዕዳችንን ከፈለልን:: አዳም ሊቀበለው ይገባው የነበረውን ሁሉ ተቀብሎ አዳምን ነፃ አወጣው፤
- አዳም በበደሉ ከገነት ወደ ሲዖል ቢሰደድ÷ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ያለበደሉ የገነት ምሳሌ ከሆነች ከነዓን የሲዖል ምሳሌ ወደሆነች ግብጽ ተሰደደ፤
- አዳም ከዓለመ መላእክት ተሰድዶ በእንስሳት መካከል ቢገኝ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በከብቶች በረት ተወለደ፤
- አዳም ቈኀቱም መሬት ተገኝቶ ቢሳሳት መድኃኔዓለም ክርስቶስ ከኀቱም ድንግል ከእመቤታችን ተወልዶ አዳነው፤
- አዳም ከንጹሕ ምድር (መርገም ካልደረሰባት) ተገኝቶ ቢሳሳት መድኃኔዓለም ክርስቶስ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ከሌለባት ከንጽሕት እመቤታችን ተወልዶ አዳነው፤
- አዳም በተፈጠረ በሠላሳ ዘመኑ ልጅነቱን ቢያጣ፤ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በሠላሳ ዓመቱ ተጠምቆ አዳነው፤
- አዳም በመብል ድል ተነሥቶ ከገነት ቢወጣ፤ መድኃኔዓለም ክርስቶስ «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም በእግዚአብሔር ቃል ጭምር እንጂ:: ብሎ ፈቃደ ሥጋን ስስትን ድል ነሣበት»
- ዲያብሎስ አዳምን ከምድር ተለይታ በምትገኝ ገነት ለብቻው በመብል ድል ቢያደርገው ጌታም ዲያብሎስን ከከተማ ርቃ በምትገኝ ገዳመ ቆሮንቶስ በጾም ድል ነሣው፤
- አዳም ሕግ ጥሶ ከጸጋ ቢራቆት መድኃኔዓለም ክርስቶስ ራቁቱን በመልዕልተ መስቀል ተሰቀለለት፤
- የአዳም እጅና እግር ወደ ዕፀበለስ ቢያመሩ መድኃኔዓለም እጅና እግር በቅንዋት ተቸነከሩ::
- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አምላክ፣ ወልደ እግዚአብሔር ፍጹም ካሣን ካሠልን:: የአዳም ዐጽም ካረፈበት በጐልጐታ (ትርጓሜው የራስ ቅል ነው) ተሰቅሎ ሞትን መውጊያ አሳጣው፤ የመቃብርም ኃይል ተሻረ:: ርቀን የነበርነውን ልጆቼ አለን::

የተዘጋች ገነት ተከፈተች፤ ዕድሜውን በሙሉ በኃጢአት ሲናውዝ ለነበረው ለፈያታዊ ዘየማን ታላቅ ብሥራት ተነገረው «ከኔ ጋር በገነት ዛሬ ትሆናለህ» (ሉቃ. 23÷43) ገነት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ተመልሰው በቀኙ ለሚቆሙ መከፈቷን አበሠረን:: ሞት በሞት ሞተ::

*«እግዚአብሔር ሰው ሆነ» ስንል እንዴት ነው?*

ይቀጥላል

---

## ነገረ ማርያም...

ጉድጓዶች ትወጣለች ከነገሥታትም አዳራሹ:: ይህ ቃል እመቤታችን በአድ ባረ ሊባኖስ እንደም ትወልድ የተነገረ ሲሆን ሌላ ሐረገ ትውልዷ ከይሁዳ ከተወለዱ ነገሥታት ከዳዊት ከሰሎሞን መሆኑን ያስረዳናል፤ ከዚህም ጋር በማያያዝ የላቀ ምሥጢር እንዳለው በዘፍ.49 ላይ ስለ ክርስቶስ ከቤተ ይሁዳ መገኘት ሙሴ የፃፈውን መሠረት በማድረግ ሊቁ እንዲህ ሲል ተርጉሞታል::

*«ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ እምነ ሥርው ለዳዊት አንበሳ ዘይቤ ወልደ አምላክ ተንሥአ»*

ትርጉም:-ከዳዊት ባህርይ ከነገደ ይሁዳ የተገኘ አንበሳ አሸነፈ (ሞትን ድል አደ ረገ) አንበሳ ያለውም ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን ወልደ አምላክ ክርስቶስን ነው፤ እመቤታችንም ከግበበ አናብስት ትወጣለች ያለበት ምክንያት የሥርዓተ ንግሥ አርማቸው አንበሳ ክርስቶስ ከነበረ አናብስት ከሚመስሉ ነገሥታት ከዳዊት ከሰሎሞን ባህርይ ለመገኘቷ ምሳሌ ነው::

የእመቤታችን ጥንተ ግኝት ኀሠሣራ እይ ሰንሰለታዊነት:-

ቴክታ በጥሪቃ የሚባሉ የወርቅ የዕንቁ የወንድ፣ የሴት አገልጋይ የላም የፍየል፣ የፈረስ፣ የበቅሎ መንጋ ባለጠጎች ነበሩ፤ ዳሩ ግን ዓይናቸውን የሚያሳርፉበት ከአብራካቸው የተገኘ ልጅ አልነበራቸውም:: ከዕለታት አንድ ቀን በጥሪቃ ወደ ዕቃ ቤት ገብቶ የኑሮ ሥርዓት የተሟላላቸው ከመሆኑ የተነሣ ዕቃውን ቁሳቁሱን ተመልክቶ ቴክታ ከአንቺ በቀር የምወደው እንደሌለ አምላክ ያውቃል ነገር ግን ልጅ የለንም አላት:: እሷም ለልጅማ ምንድን ነኝ ወደ እግዚአብሔር እናመልክት እንጂ አለችው:: አመለከቱ::በራ ዕይ እሷም ከማኅፀንዋ ነጭ እንቦሳ ስትወጣ፣ እንቦሳዋ እንቦሳን ስትወልድ እስከ 6 ደረሱ:: ስድስተኛይቱ ጨረቃ ጨረቃይቱም ፀሐይን ስትወልድ አይታ ነገረችው:: በዘመናቸው መተርጉመ ህልም አለና ሄደህ አስተርጉመህ ና አለችው:: ሄዶ ለፈቺው ቢነግረው ደግ ልጅ ትወልዱ ይሆናል አለው:: ተመልሶ መጣ ምን አለህ? አለችው «ደግ ልጅ ትወልዱ ይሆናል» አለኝ አላት:: የጨረቃይቱንና የፀሐይቱንስ ጊዜ ይተርጉመው እንጂ አልተረጎምልህም አለው:: እንዲህ ሲኖሩ ፀንሳ ወለደች፣ ስምዋንም ሔኤሜን ብላ ሰየመቻት:: ምኞቴን ልመናዬ አገኘሁ ማለት ነው:: ሔኤሜን ደርዱዕን፣ ደርዱዕ ቶናሕን፣ ቶናሕ ሲካርን፣ ሲካር ሔርሜላን፣ ሔርሜላ ሐናን፣ ሐና ከነገደ ይሁዳ የተወለደ ኢያቄምን አግብታ ስትኖር መካንነት በዘር ወርዶ መካን ሆነች:: ሐና መካንነቷን ተከትለው በተከሰቱ በተፈፀሙ ጧይት ነገሮች አዝናለች::

1. ወዳጅ ባልንጀራ ጎረቤት ነበረቻት ከዕለታት አንድ ቀን ዛሬ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሄጄ እጅ ልነሣ ወድጄ ነበር:: ነገር ግን ልብስ የለኝም አለ ቻት፣ ልብስማ የኔ ብዙ ልብስ አለ ልሽ አንዱን ለብሰሽ አትሄጅም? አለቻት፤ ምን አልባት በዝሙት በዐለበ ደነስ ያመጣሽው እንዳይሆን እግዚአብሔር ንፁሐ ባህርይ ነው:: ስለዚህ ንፁህ የሆነ ነገር ይወዳልና::

ይህንን ለብሼ ብለምነው ይሰማኛል ብዬ ነው አለቻት፤ ሐና እግዚአብሔር በምን ምክንያት ልጅ ነሣት እያልኩ ሳዝንልሽ እኖር ነበር፣ ለካ እንደ ደንጊያ አድርቆ ያስቀረሽ ትዕቢትሽና ክፋትሽ ነው ብላ ስለተናገረቻት አዝናለች:: ነገሩም አልቀረ ተውሳ ለብሳ ሄደች::

ይቀጥላል

# «በቅርብ የማውቃቸውና የምወዳቸው የወንጌል መልእክተኞች አባቶቼ በዚያ ሁኔታ አሰቃቂ መከራ ሲደርስባቸው በማየቴ እጅግ አዝኛለሁ»

ብፁዕ አቡነ ቀዉስጦስ

በሰሜን ሸዋ በሰሳሴ አውራጃ በስሚ ወረዳ ልዩ ስሙ የትናሪ ቅዱስ ሚካኤል በተባለው ቦታ ከአባታቸው ከመ/ር ኃይለ ማርያም ድብቀ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ስናፍቅሽ ወልደማርያም በ1929 ዓ.ም ተወለዱ:: ከመምህሩ ወሰጃቸው ፊደል በመ ቁጠር የጀመሩትን የትምህርት ዓለም ቀጥ ሰው ወደ ደብረ ሊባኖስ በመሄድ ንባብና ዳዊትን ተማሩ:: በወቅቱ በጽኑ ሁኔታ ተጠ ናውቷቸው በነበረው የነቀርሳ በሽታ የተነሣ ወደሚጣቅ አማኑኤል በመ ሄድ ስስድስት ወራት ከተጠመቁ በኋላ ተፈወሱ::



በዚያው እንደወጡ አንኮበር ቅዱስ ሚካኤል ወደ ሚገኙት የቅኔ መም ህር (መ/ር ወልደጊዮርጊስ ፈቄ) ዘንድ በመሄድ ለአራት ዓመታት ቅኔን በሚገባ ተማሩ:: ከዚያም ወደ ደብረ ሊባኖስ በመ መለስ መ/ር ገብረ ጊዮርጊስ መታሰቢያ ት/ቤት በመግባት ሐዲሳትን ከተማሩ በኋላ የመምህርነት ፈቃድ አገኙ:: ብፁዕነታቸው በ1960 ዓ.ም ሰሜን ሸዋ ሰቃ መድኃ ኔዓለም ገዳም ቅኔውንም ሐዲሳቱንም እንዲያስተምሩ በመመደብ እስከ 1966 ዓ.ም፣ ከዚያም ወደ መተሀራ መድኃኔዓለም ደብረሰላም በመዘዋወር በአስተዳዳሪነት እስከ 1971 ዓ.ም ድረስ አገለገሉ:: በተጨማሪም በአዲስ አበባ ደብረ አሚን ተክለሃይማኖት በአስተዳዳሪነት ለ8 ዓመታት አገልግለዋል::

በመጨረሻም በ1979 ዓ.ም ግንቦት 30 ቀን በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ተመረጡ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በልዩ ልዩ አኅጉረ ስብከት በመዘዋወር በማገልገል ላይ ናቸው::

ብፁዕነታቸው ስላገለገሉባቸው አኅጉረ ስብከትና አጠቃላይ የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ እንዲሁም በቅርብ ሁለት ሊቃነ ጳጳሳት በአካለ ሥጋ እንዲለዩን ምክንያት የሆነው የመኪና አደጋ ከመከሰቱ በፊት ከአባቶች ጋር አብረው ስለነበሩና ከአደጋውም በኋላ በቦታው ተገኝተው ስለነበር ስለአደጋው ጠቅላላ ሁኔታ ከመርሻ አሰኸኝ ጋር ተወያይተዋል:: ለአንባብያን መልካም ንባብ እንላለን::

*ሐመር፡- ለዚህ ከፍተኛ ማዕረግ ከበቁበት ጊዜ ጀምሮ ካገለገሉባቸው አኅጉረ ስብከት ውስጥ የበለጠ ሥራ የሠሩበት ከዚሁም ጋር ለሥራዎ ዕንቅፋት ተፈጥሮብዎት የነበረው በየት ነው?*

*ብፁዕነታቸው፡-* በመጀመሪያ በኤጲስ ቆጶስነት ተቀብቼ የተሾምሁበት ወላይታ ደብረ መንክር ተ/ሃይማኖት ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት ቅዱስነታቸው (ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት) የእኔን የአስተዳደግ ሁኔታ በማጥናታቸውና ከተ/ሃይማኖት ወደ ተ/ሃይማኖት በሚል ይመስለኛል:::

በትምህርትም ሆነ በሥራ በርከት ያለውን ዕድሜዬን ያሳለፍኩት በአቡነ ተ/ሃይማኖት በተገደመው ገዳምና በስማቸው በተሰየመው ቤተክርስቲያን በመሆኑ በኤጲስ ቆጶስነትም ወደዚያ እንድሄድ የሆነ ይመስለኛል:: ለማንኛውም በዚያ እስከ 1981 ዓ.ም ሠራሁ:: ከዚያም ወደ ትግራይ ሀገረ ስብከት እንድሄድ ታዘዝኩ:: ነገር ግን በተለያዩ ችግሮች የተነሣ ወደዚያ ሳልሄድ ወደ ምዕራብ ሐረርጌ ተዛውሬ እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በዚያ አገለገልኩ::

ከዚያም በ1983 መጨረሻ ወደ ወለጋና አሶሳ አኅጉረ ስብከት ተዛውሬ ለሁለት ዓመታት ካገለገልኩ በኋላ በ1986 ዓ.ም ወደ ሰሜን አሞ ሀገረ ስብከት በመዛወር እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ አገለገልኩ:: አሁን ደግሞ ይኸውና በምስራቅ ሐረርጌና ኦጋዴን አህጉረ ስብከት እያገለገልኩ ነው:: ታዲያ አገልግሎቴን በሚመለከት አንዱን ከሌላው የማበ ላልጠው የለም:: በሁሉም ሠርቼአለሁ:: ነገር ግን ምናልባት ጥያቄውን ለመመለስ እኔ ጥሩ ሥራ የምለው ምእመናን በመናፍቃን እንዳይነጠቁ መጠበቅ፣ ሃይማኖትን ጠብቆ ማስጠበቅ ነው:: በመሆኑም ከዚህ አንፃር በሰሜን አሞ ሀገረ ስብከት የመናፍቃን እንቅስቃሴ ጠንከር ይል ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን ምእመናን አልተነጠቁብኝም:: ምእመናኑ የመናፍቃኑን ዘመቻ ተከላክለው አሸንፈዋል፣ የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴም አልተዳከመብኝም:: ምእመናኑ መንፈስ ጠንካሮች ናቸው:: ሃይማኖታቸውን ነቅተው ይጠብቃሉ:: ለዚህ ምክንያቱ እኔ ልሁን እንጂ እነሱው ናቸው የሚመሰገኑት:: «ከአባታችን በፊት እኛ ነን፣ ሃይማኖታችን አይዳከምም፣ የሃይማኖት ሥርዓታችን መፈጸሚያ የሆነው ቦታችን (ባሕረ ጥምቀቱ) አይወሰድብንም» ብለው ትልቁን ተጋድሎ የተጋደሉት ራሳቸው ምእመናን ናቸው:: እንደመናፍቃኑ አነሣስ ሁሉ ንም ለመቆጣጠር የተነሡበት ወቅት ነበር:: በተለይ የሃይ ማኖት ቦታችንን ለመውሰድ ባደረጉት እንቅስቃሴ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሃይማኖታቸውን ለማስከበር የቤተ ክርስቲያንን መብት ለማስጠበቅ ባደረጉት ተጋድሎ ብዙ እንግልት ደርሶባቸዋል:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ይዞ ታችንን አስከብረዋል::

*ሐመር፡- አሁን ያሉበትን አኅጉረ ስብከት ቀድሞ ከነበሩባቸው አኅጉረ ስብከት ጋር እንዴት ያነፃፅሩታል? በምእ መናን ብዛት? በአብያተ ክርስቲያናት ቁጥር? በቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ?...ወዘተ*

*ብፁዕነታቸው፡-* አሁን ያለንበት አኅጉረ ስብከት ምሥራቅ ሐረርጌንና ኦጋዴንን በአንድ ያጠቃለለ ነው። ምሥራቅ ሐረርጌ ብቻ 96,201 ምእመናን፣ 499 ካህናትና 36 አብ ያተ ክርስቲያናት ያሉበት ነው።

እንግዲህ ቀድሞ የነበርኩባቸውን አኅጉረ ስብከት ከላይ ጠቅሼልሃለሁ። በምእመናኑ በኩል ከቀድሞዎቹ አኅጉረ ስብከቶቼ ጋር ሳነጻጽረው ልዩነት አላይም። በእውነቱ አሁን ያለሁበት አህ ጉረ ስብከት ምእመናን ታዛዦችና ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚወዱ ናቸው። አንድ ጉባኤ ባደረግን ጊዜ ጉባኤው የእነሱ መሆኑን ተገንዝበው በትጋትና በሚያስደስት ሁኔታ ተባብረው ያቀናጃሉ። ያዘጋጃሉ። በእው ነቱ ይኸንን የትም ቦታ የምናገረው ነው። አክ ብረውን ነው የሚሠሩት። ካለእነሱ ድጋፍና ትብብር ቤተክርስ ቲያን ሥራዋ አገልግሎቷ ሁሉ የተቃና እንደ ማይሆን በሚገባ ተገንዝበው እኛን መስለውን እኛን ሆነው ይሠራሉ። በዚህ አጋ ጣሚ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። አሁንም የሥራ ቅንጅታችንን የበለጠ ብናጠናክር ያሉብንን ችግሮች ሁሉ በማስወገድ የቤተክርስቲያናችንን የሐዋርያነት እንቅስቃሴ እንደምናፋጥን በመተማመን ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

በአሁኑ ወቅት ለቤተክርስቲያናችን ክብር መጠበቅ ወጣቱ ያለበትን ከፍተኛ ኃላፊነት ተገንዝቦ በአንድነት በመንቀ ሳቀስ ላይ ነው። ነገር ግን ይህንን ጉዳይ በሚመለከት በአኅጉረ ስብከቴ ከፍተኛ ችግር አለ። እዚህ ላይ እንደ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና ትውፊት ከእኛው ጋር በመሆን ቤተክርስቲያናቸውን የሚያገለግሉ ወጣቶች እንዳሉ ለመግለጽ እፈልጋለሁ።

በእውነቱ አኅጉረ ስብከቱ የተወሰኑ ልጆች ወላጆችን ግራ የሚያጋቡበት ውስብስብ ችግር ያለበት ነው። እንግዲህ መስሎ በመታየት ሥርዓቱን ከኦርቶዶ ክስም ከፕሮቴስታንትም አደባልቀው እየሠሩ «እኛ ኦርቶዶክስ ነን» ይላሉ። በተግባር ስና ያቸው ግን የፕሮቴስታንቶች ሥራ አስፈጻሚዎች ናቸው። በዚህ የተነሣም ወላጆች ግራ ተጋብተዋል። «እኛ ያሳደግናቸው ናቸው አብረውን የኖሩ ናቸው» ይላሉ። ነገር ግን ልጆቹ ከቤተክር ስቲያን ተለይተው የራሳቸውን ቤት ተከራይተው ያው የተደበ ላለቀ ሥርዓታቸውን በማካሄድ ላይ ናቸው። እግዚአብሔር ወደ ፊት ሁሉንም ያስተ ካክለው።

ልማትንም በሚመለከት ከነበርኩባቸው አኅጉረ ስብከት ሁሉ የበለጠ በዚህኛው ችግር አለ።

እንግዲህ ይህ ሁሉ ችግር ቢኖርም የቆምንበት ዓላማ በመሆኑ ሥራዎችን በተቻለ መጠን ከመሥራት ወደ ኋላ አላልንም። ችግር አለ በተባለበት ቦታ ሁሉ እየተዟዟርን እናስተ ምራለን፣ የተበላሸውን ለማስተካከል እንሞክራለን።

*ሐመር፡- ወደዚህ አኅጉረ ስብከት ከመጡ ያጋጠመዎት ለየት ያለ ነገር ካለ ቢነግሩን?*

*ብፁዕነታቸው፡-* እንግዲህ አካባቢው በዛ ያለው ሕዝብ እንደመ ዝናኛ ወይም እንደማምለኪያ ሊሆን ይችላል ጫት የተባለውን ቅጠል የሚያዘወትርበት ቦታ ነው። እና ገና ወደዚያ እንደሄድኩ በመንበረ ጵጵስናው በር አካባቢ ሰው ሞቶ ድንኳን ተዘርግቶ ሰዎች ለኃዘን ተቀምጠው ነበር። ኃዘኑ የደረሰባቸው የእኛው ቤተክርስቲያን ልጆች መሆናቸውን በመስማቴ እንሂድና እናጽና ናቸው በማለት ከአንድ ሰባኬ ወንጌል ጋር ሄድን። ከሰዓት በኋላ ነበር። በዚያ ተገኝተን መምህሩ «ሁሉም ይሞታል ነገር ግን ይነ ሣል» በሚል መነሻ ሰፋ ያለ ትምህርት ሲሰጡ በተመስጦ የሚያ ዳምጡት ሰዎች ግማሾቹ ብቻ ነበሩ። ግማሾቹ ግን በጫቱ የሰከ ሩት በጣም ጸንቶባቸው ካርታ የተባለውን ወረቀት እያነሡ እየ ጣሉ ይወትካሉ። በዚያ ጊዜ እኔ አላ ወኩም ነበርና «እናንተ እን ኳን ባታምኑ ያመኑትን አት ረብሹ» በማለት ተቆጣሁኝ። በኋላ ግን ምክንያቱ ገባኝና በሉ ጥፋቱ የእኛ ነው በማለት ትምህርቱ እንዲቆም አደረኩ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በእንደዚያ ዓይነት ቦታ እስከቀኑ ስድስት ሰዓት ካልሆነ በስተቀር ከዚያ በኋላ ትምህርት አንሰጥም።

*ሐመር፡- የጠቀሱትን ችግሮች በተለይ የተሐድሶዎቹን ችግር ለማቃለል እየወሰዱት ያለ እርምጃ ካለ ቢገልጹልን?*

*ብፁዕነታቸው፡-* እንደተባለው በአኅጉረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስናው በሚገኝበት በሐረር ከተማ ራሳቸውን ከቤተ ክርስቲያን አግልለው በግላቸው የሚንቀሳቀሱ ወጣቶች አሉ። ማንነታቸው በሚገባ ስለታወቀም ከቤተክርስቲያን ተገልለዋል።ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ከቤተክርስቲያን ውጭ ቢሆኑም በማንኛውም ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን ገብተው ኑፋቄያቸውን እንዳያስራጩ ከእኛ የበ ለጠ ምእመናንና በየአጥቢያው ያሉ የሰንበት ተማሪዎች ይከታተ ሏቸዋል። እነሱ ማንነታቸውን በሚገባ አውቀዋቸዋልና። በእኛም በኩል ማንኛውንም እንቅስቃሴያቸውን ከመከታተል ጐን ጠርተን እናነጋግራቸዋለን፣ እንመክራቸዋለን። ይህ አካሄዳቸው ጥሩ እንዳልሆነ ደግመን ደጋግመን እንነግራቸዋለን። የሚሠሩት ስህ ተት እንደሆነ አምነው በንስሃ እንዲመለሱ (ነገር ግን እውነ ተኛውን መመለስ) እንመክራ ቸዋለን።

እንግዲህ ለማንኛውም የቤተክርስቲያን ችግር መፍት ሄውን የሚያመጣው እግዚአብሔር በመሆኑ እሱን ከማሳሰብ ጋር እኛም ሆን ምእመናን የሚጠበቅብንን እያደረግን ነው።

*ሐመር፡- በአሁኑ ወቅት ያለውን አጠቃላይ የቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎት እንዴት ይመለከቱታል?*

*ብፁዕነታቸው፡-* በአሁኑ ሰዓት ያለው እንቅስቃሴ የሚደነቅ አይደለም። ከዚህ የበለጠ ቤተክርስቲያናችን መንቀሳቀስ ነበረባት። ችግሩ በጣም የከበደ ነው። መናፍቃኑ ከውጭ ሆነው የዕንቅፋትነት ሥራቸውን ይሠራሉ። ዛሬ መናፍቃን በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የበለጠ ተጠናክረው የተነሡበት ጊዜ ነው። በእርግጥ መሠረቷ ክርስቶስ ስለሆነ ምንም ልትሆን አትችልም። ሌላው ውስጣዊ ችግርም አለ። ይኸውም ቤተክርስቲያኗ ካለባት የኢኮኖሚ ችግር ጋር በውስጧ ያሉ ሠራተኞች በአጠቃላይ የቤተክርስቲያን ልጆች ነን የምንለው እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን የመገኘት ችግር እንዳለ ይሰማኛል። ይኸውም ለያዝነው ዓላማ በአንድነት ከልብ የመሰለፋችን ጉዳይ ነው። ይህን ስል ግን በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ዕንቅፋት ሆነናል ወይም ችግር ፈጣሪዎች ነን ማለት አይደለም። የተወሰኑ ሰዎች ለሥራ ዕንቅፋት ሲሆኑ ይታያሉ።

የሆነው ሆኖ ይህችን ቤተክርስቲያን የማይረሳ አምላክ ይህንን ችግር አቃልሎ ቤተክርስቲያናችን ክብሯን ጠብቃ የሐዋርያነት እርምጃዋን እንድትቀጥል እንዲደረግ የሁላችንም ጸሎት ነው። ይህንን መሻታችንን እንደሚሰማንም እናምናለን።

*ሐመር፡- በዘመናችን የካህናት ተልእኮ ምን መምሰል አለበት ይላሉ?*

*ብፁዕነታቸው፡-* ሕግን የሚፈጽመው እየጠፋ ነው እንጂ የካህናት ተልእኮ ምን እንደሆነ እኔ ከምናገረው የበለጠ በመጽሐፉ በግል ጽና በስፋት ተቀምጧል። ካህናት ከሥርዓተ ፃሎት አንጻር የሚ ጠበቅባቸው በሥጋዊ ጥቅም እንጠቀምባቸዋለን ሳይሉ የእግዚአብ ሔርን መንጋዎች ምእመናኑን በትምህርተ ወንጌል መጠበቅ ነው። ይህንንም አባታችን ቅዱስ ጴጥሮስ በአንደኛ መልእክቱ ምእራፍ አምስት ቁጥር ሁለትና ሦስት በጥሩ ሁኔታ አስረድቶናል። « በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን÷በበጐ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን

በቅርብ የማውቃቸውና የምወዳቸው የወንጌል መልእክተኞች የእግዚአብሔር አገልጋዮች/ በፊቴ በዚያ ሁኔታ አሰቃቂ መከራ ሲደርስባቸው፣ አወዳደቃቸውንም በማየቴ እጅግ አዝኛለሁ። በራሴ በኩል በብዙ መከራ ተፈትኛለሁ። ገና በተማሪነት ሕይወቴ ነቀርሳ በተባለው በሽታ ተይዤ ጉሮሮዬ ውሃ እያፈሰሰ ልብሴን እያበሰበሰ ለሰባት ዓመታት ያህል በእጅጉ ተሰቃይቻለሁ። በዚያ ጊዜ ተስፋ የማደርገው ሞትን ስለነበር እጅግም አይሰማኝም ነበር። የተሰማኝ በጣም በጣም አሁኑኑም በዓይኔ ተስሎ እያስቸገረኝ ያለ ጉዳይ የአባቶቼ አወዳደቅ ነው።

ጉብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ» በማለት አዝዟል።

የእውነተኛ ካህን መመዘኛው የታወቀ ነገር ነው። ምሥጢረ ሃይማኖትን ለማስተማር መብቃት፣ ራስን መግዛት፣ እንግዳ የመቀበልን ጠባይ ልማድ ማድረግ፣ ከስካር መራቅ። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ለቅዱስ ጢ ሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ ምዕራፍ ሦስት ከቁጥር ሁለት እስከ አምስት ዘርዝሮታል። ሌላው ቀርቶ የቤቱን ሥርዓት በሚገባ አቃንቶ የሚመራ፤ የራሱን ቤት በሚገባ ማስተዳደርና መምራት አይችልምና። ስለዚህ አንድ ካህን የነፍስ ልጆቹ አባት፣ ጠባቂና እረኛ መሆኑን ተረድቶ ዕለት በዕለት መከታተል፣ ምግባሩ የተመሰገነ የቤተክርስቲያኑን ማንኛውም ሐዋርያዊ እንቅስቃሴ በንቃት የሚከታተል፣ በዕውቀቱ ከሌላው የቀደመ መሆን ይኖርበታል።

*ሐመር፡—* ካህናት ተልእኮአቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ቤተክርስቲያን ምን ማድረግ አለባት ይላሉ?



*ብፁዕነታቸው፡—* ማድረግ ያለባትን እያደረገች ነው። በየአኅጉረ ስብከቱ ካህናትን እየሰበሰበች፣ ልዩ ልዩ ሴሚናሮችን እየሰጠች፣ ከሥርዓቱ ውጭ ሆኖ የተገኘውን ሥልጣኑን እየያዘች ከሥራም እያስወገደች ነው ያለችው። በመሆኑም የአንዳንድ ካህናት ችግር ቤተክርስቲያንን ክፉኛ እየጐዳ ያለ ነገር መሆኑን ተገንዝባ ማስተማሯንና እንቢ ባሉት ላይም እርምጃ የመውሰዷን ጉዳይ አጠናክራ እየቀጠለች ነው። በየአኅጉረ ስብከቱ ያሉ ሥራ አስኪያጆችም በዚህ ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነትና አደራ ተሰጥቷቸዋል። እናም ጥሩ ነገር እየታየ ነው ያለው።

*ሐመር፡—* በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሰዎች የወጣቱን በወንጌል አገልግሎት መሰማራት በበጐ ጐኑ አያዩትም። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?

*ብፁዕነታቸው፡—* በእውነቱ ወደቤተክርስቲያን መምጣት፣ በአገልግሎት ላይ መቀመጥ የሚያስደስት እንጂ የሚያስከፋ አይደለም። ነገር ግን ክትትል ያስፈልጋል። አባት ሰባክያን የልጆቻቸውን ለስብከተ ወንጌል መፋጠን በበጐ ጐኑ ተመልክተው ይልቁንም ከጐናቸው በመሆን በማስተማር በመምከር በመገሰጽ ሊያበረቷቸው ይገባል እንጂ መቃወም የለባቸውም። ደግሞም ወጣቶቹ በሚገባ የቤተክርስቲያንን ትምህርት ከተማሩ፤ ዛሬ በተለያዩ ዘዴዎች ቤተክርስቲያንን ለማጥቃት የተነሡትን መናፍቃን አካሄዳቸውን ከእኛ ይልቅ እነሱ ስለሚያውቁት ከፍጥነት ጋር ድል ያደርጓቸዋል። ስለዚህ እነዚህ « አእመሪ» ያላሉ እንዴት በወንጌል አገልግሎት ሊሰለፉ ቻሉ? ብሎ ማለት አይገባም። ደግሞ ካስተማሯቸው የሊቃውንቱን መርህ (ፈለግ) የማይከተሉበት ጉዳይ የለም። ከዘመኑ ዕውቀት ጋር ስለተራመዱ በቤተክርስቲያን በኩል የሚያስተምራቸው ካገኙ እጅግ ብዙ ጠቃሚ ሥራ ያበረክታሉ። በእርግጥ ሰይጣን መጥፎውን ያመለከታቸው ከእናት ቤተክርስቲያናቸው ጉያ ወጥተው የሚንቀሳቀሱ ወጣቶች አሉ። ዐወቅን፣ ተራቀቅን፣ ምክር አንሰማም የሚሉም አሉ። እና ምናልባት አንጋፋ ሰባክያን ሊያጠራጥራቸው የቻለው በዚያ የተነሣ ሊሆን ይችላል። ግን 'አባት ያልተከለው ይነቀላል' እንደሚባለው እግዚአብሔር ያልጠራው ወጣትም ካለ እየተለየ ይሄዳል። ነገር ግን እግዚአብሔር የጠራቸው ለአገልግሎትም የመረጣቸው«ከአባቶቻችን ጐን ተሰልፈን እንሠራለን» ያሉትን ተስፋ ማስቆረጥ እናንተ እንዲህናችሁ ብሎ ማባረር ቤተክርስቲያንን መጉዳት ነው። ለእነሱ ሞራል እየሰጡ፣ ነገረ ሃይማኖትን እያስተማሩ ማሠራት እንጂ እንዲያው ገና ለገና ወደፊት ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ በሚል ግምት ሰው ማጣት፣ ቤተክርስቲያንንም ሰው ማሳጣት አይገባም።

ወጣቶቹም ሃይማኖት ፍልስፍና የሚሻ ጉዳይ ባለመሆኑ ፍልስፍናን ትተው ከአባቶቻቸው እግር ሥር በመቀመጥ መማር አለባቸው። ከዚህም ጋር ወቅቱ መጻሕፍትን አጣመው የሚተረጉሙ ሰዎች የበዙበት ነውና ለእኒህ ሰዎች ጆሮአቸውን መስጠት የለባቸውም እላለሁ።

እኔ ጥሩ ሥራ የምለው ምእመናን በመናፍቃን እንዳይነጠቁ መጠበቅ፣ ሃይማኖትን ጠብቆ ማስጠበቅ ነው። በመሆኑም ከዚህ አንፃር በሰሜን ኦሞ ሀገረ ስብከት የመናፍቃን እንቅስቃሴ ጠንከር ይል ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን ምእመናን አልተነጠቁብኝም። ምእመናኑ የመናፍቃኑን ዘመቻ ተከላክለው አሸንፈዋል፤ የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴም አልተዳከመ ብኝም። ምእመናኑ መንፈሰ ጠንካሮች ናቸው። ሃይማኖታቸውን ነቅተው ይጠብቃሉ። ስለዚህ ምክንያቱ እኔ ልሁን እንጂ እነሱው ናቸው የሚመሰገኑት።

*ሐመር፡— በአሁኑ ወቅት ለቤተክርስቲያን ያስፈልጓታል ብለው የሚሏቸው ነገሮች ካሉ ቢገልጹልን?*

*ብፁዕነታቸው፡—* በአሁኑ ወቅት ለቤተክርስቲያን ያስፈልጓታል የምላቸው በቤተክርስቲያኗ ሥልጣን ላይ ያለነው ሁሉ ቤተክርስቲያናችን ከእኛ ብዙ የምትጠብቅ መሆኗን ተገንዝበን በአንድነት በመመካከር በመደማመጥ እንድንሠራ፣ በመንግሥቱ ሥልጣን ያለው ሁሉም አቤቱታዋን የሚያዳምጥ ይዞታዋንና ክብሯን የሚያስጠብቅ እንደሚሆን፣ በውስጥ የእኛ ሳይሆኑ የእኛ መስለው የሥራ መሰናክል እየፈጠሩ ያሉ ጠላቶቿ በሙሉ እንዲወጡ፣ የራሷ ሀብት በራሷ ልጆች እንዲጠበቁ ይህንንም ስል ቤተክርስቲያናችን ባዕለፀጋ እንደመሆኗ ሀብቶቿ ሁሉ በስሯ ባደጉ ትምህርቷን፣ ባህሏን ሁሉ ጠንቅቀው ባወቁ ልጆቿ እንዲጠበቁ፣ ከላይ እስከታች ያለው ሠራተኛ ሁሉ ለስብከተ ወንጌል እንዲሰለፍ፣ ከዚህም ጋር ለወንጌሉ ተልእኮ የሚያስፈልገው ሁሉ እንዲሟላ አጥብቄ እሻለሁ።

*ሐመር፡— በቅርቡ በድንገተኛ አደጋ በአካለ ሥጋ ስለተለዩን ሁለት ጳጳሳት ( ብፁዕ አቡነ ዮሴፍና ብፁዕ አቡነ ኤልያስ) ከሚያውቋቸው ጥቂቱን ቢነግሩን።*

*ብፁዕነታቸው፡—* እነዚህን ሁለት አባቶች በቅርብ ነው የማውቃቸው። ከብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ጋር ከሁለት ዓመት በላይ በአንድ ቤት ኑረናል። ምን ዓይነት ሰው እንደሆኑ ምን ዓይነትም ባሕርይ እንዳላቸው በጥሩ ሁኔታ አውቃለሁ። ሽማግሌ ሆነው ስለቤተክርስቲያን ያላቸው ትጋት ይህ ነው ተብሎ የማይገመት ታታሪ ተጠያቂ ምሁር አባት ነበሩ። አሁን እንኳ እስከ ዕረፍታቸው ጊዜ የነበረውን ስናይ ዕድሜያቸው ሰማንያ ዓመት ነው። ነገር ግን

በዚህ በሰማንያ ዓመታቸው አቀበቱን ወጥተው ቁልቁለቱን ወርደው ልክ እንደ ሠላሳ ዓመት ጐልማሳ ሆነው ነበር የሚሠሩት:: እና እኒህ ብፁዕ አባት ለሀገርም ለቤተክርስቲያንም ተቆርቋሪ ነበሩ፡ ባላቸው ዐቅም ቤተክርስቲያንን ለማገልገል የነበራቸው ፍቅርና ትጋት ይህ ነው ተብሎ አይነገርም::

ብፁዕ አቡነ ኤልያስንም ቢሆን ወደ አዲስ አበባ ከመጣሁ ጊዜ ጀምሮ ነው የማውቃቸው:: ብፁዕነታቸው በወንጌል መድረክ የተጉ ሊቅ አባት ነበሩ፡ ሌሊት ማኅሌት አድረው ጠት ቀድሰው በዚያው አስተምረው እንደገናም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን ሄደው ሲያስተምሩ ይውላሉ ያመሻሉ:: ይህንንም አሟሟታቸው ይመሰክራል:: ብፁዕነታቸው ይህ አደጋ የደረሰባቸው አዲስ አበባ ደብረ አሚን ተክለሃይማኖት ቀድሰው ብፁዕ አቡነ ዮሴፍም አስተምረው ለቀጣይ አገልግሎት ወደ ባሌ ስንሄድ ነው::

በእውነቱ ሁለቱም አባቶች ተመሳሳይ ባሕርይ አላቸው:: ሁለቱም በእውነት ስለእውነት ሲመሰክሩ ጊዜ አይሰጡም:: ምንም ነገር በይሉኝታ ሸፍነው ለማለፍ አይፈልጉም:: በአንድ ቀን መጓዛቸው በእውነቱ እጅግ ይገርመኛል:: በጠባያቸው ተመሳሳይነት፣ በሥራቸው ተመሳሳይነት፣ በትጋታቸው ተመሳሳይነት ያላቸው አባቶች በአንድ ቀን ወደላይኛው ዓለም መጓዛቸው ይደንቀኛል:: እንግዲህ መቼም የእግዚአብሔር ምሥጢር አይመረመርም፤ ሁለቱም ለቤተክርስቲያናችን መጠበቅ ከፍተኛ ተጋድሎ እያደረጉ የነበሩ አባቶች በመሆናቸው በእውነቱ ታላቅ ጉዳት ነው::

*ሐመር፦ አደጋው ከመከሰቱ በፊት ከሊቃ ጳጳሳቱ ጋር አብረው እንደነበሩ ይታወቃል:: እነዚህ አባቶች ከእርስዎ እንዴት ተለይተው ይህ አደጋ ሊደርስባቸው ቻለ? አደጋውንስ እንዴት ሰሙ? በአጠቃላይ ስለነበረው ሁኔታ ሰፋ አድርገው ቢያወያዩን?*

*ብፁዕነታቸው፦* የጉዞአችን ዓላማ በብፁዕ አቡነ ሰላማ ጥሪና ግብዣ በባሌ ሀገረ ስብከት ጐባ ከተማ ተዘጋጅቶ በነበረው ታላቅ ጉባኤ ተገኝተን የወንጌል ትምህርት ለመስጠትና በዚያ ያሉ ልጆቻችንንም ለመባረክ ነበር:: በመሆኑም በዚያ ጉባኤ ለመገኘት ሐሙስ እንደምንሄድ ተነጋግረን ተቀምጠን ሳለ ከብፁዕ አቡነ ኤልያስ እዚህ አዲስ አበባ በሚገኘው ደብረ አሚን ተክለሃይማኖት አገልግለን እንሂድ የሚል ሀሳብ መጣ:: እኔ ግን «አይ፣ እንደዚህ ባናደርግ:: መንገዳችን ሩቅ ነው:: እዚህ አዲስ አበባ አንግሠን ለመሄድ ያዳግተን ይሆናል:: ጊዜው ይመሽብናልና:: ባይሆን ናዝሬት ቅድስት ማርያም አስቀድሰን ብንሄድ ይሻላል» የሚል ሀሳብ አቀረብኩ:: ነገር ግን ብፁዕ አቡነ ኤልያስ «ደብረ አሚን ተክለሃይማኖት ያደግንበት ቦታ ነው:: እርስዎም ዘጠኝ ዓመት ያገለገሉበት ቦታ ነው:: እዚህ አገልግሎት በስፋው ማበርከት ስንችል ይህንን ተራምደን መሄድ የለብንም:: ቢያቆየን እስከስድስት ሰዓት ነው:: ስለዚህ እዚሁ አገልግለን መሄድ አለብን:: ሾፌሩ ሊቀ ጉባኤ አበራ በቀለ ናቸው፤ ፈቃደኛ ናቸው:: እርስዎ አያሳንፉ» አሉኝ:: እኔም «አይ፤ እኔ መሽ ብለን ከምንርጥ ብዬ እንጂ አገልግሎቱን ጠልቼው አይደለም:: እሺ መልካም» ብዬ ሀሳባቸውን ተቀበልኩ:: እናም ከንጋቱ 11:00 ሰዓት ወደ ደብረ አሚን ተክለሃይማኖት ሄድን:: እንደገለጽኩት እሳቸው ቀደሱ፣ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ አስተማሩ፡ ለስድስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ወደ ባሌ ጉዞ ጀመርን::

ጉዞውን ስንጀምርም ሊቀ ጉባኤ በሚያሽከረክሯት ፒክአፕ መኪና ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ከፊት፤ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ፣ እኔና መልአከሰላም ዳኛቸው ከኋላ ወንበር ተቀምጠን ነበር የምንጓዘው:: ነገር ግን ገና ብዙም ከአዲስ አበባ ሳንርቅ መልአከሰላም ዳኛቸው «አባታችን አሟቸዋል:: እኔ ከላያቸው ወድቄ ነው የምንጓዘው:: እና በኋለኛው መኪና ቢገቡ ይሻላል» አሉ:: እኔም «እውነት ነው፤ እግሬም አልታጠፍ አልዘረጋ እያለ ያስቸግረኛል:: እናንተም ተጣባችኋል:: እንዳሉት እኔ እዚያ ብሄድ ይሻላል» አልኩኝ:: በዚያ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ «የእኔም እግርኮ ያመኛል፤ አይታጠፍም አይዘረጋም» አሉ:: 'አይ ከእኔ ሳይሻሉ አይቀርም' እየተባባልን ስንነጋገር ሊቀጉባኤ «እንግዲያውስ ቦታ ፈልጌ አቆማለሁ:: እና እንደተባለው መሪጌታ ታምር እዚያኛው መኪና ጋቢናውን ይዟል:: እርስዎ ወደዚያ ይሄዳሉ፤ እርሱ ወደ ዚህ ይመጣል» አሉኝ:: እና ደብረ ዘይትን አልፈን ሞጆ መግቢያ ላይ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን አለ፤ እዚያ ስንደርስ «ሽማግሌውም (አቡነ ዮሴፍ) ደክሟቸዋል:: እና ወደቤተክርስቲያኑ ገባ ብለን ብናርፍ» በሚል ሊቀ ጉባኤ መኪናዋን አቆሙ:: እኔ ግን «አይ ለማረፍ እንኳን አንድ ልጅ አሉኝ እሳቸው ቤት ብንሄድ ይሻላል» አልኩኝ:: መኪናዋ ቆማ በዚያ እየተነጋገርን ሳለ ቀሳውስቱ ሲመጡ በማየቴ እነሱን ሰላም ልል ወደዚያ ሄድኩኝ::

ከቀሳውስቱ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥኩ በኋላ ወደመኪኖቹ በመመለስ ያው በተነጋገርነው መሠረት በቀጥታ ወደሁለተኛዋ መኪና ሄጄ ገባሁ:: በኋላ እንደነገሩኝ ከሆነ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ እኔ ከገባሁበት ማለትም ሁለተኛው መኪና ገብተው ተቀምጠው ኖሯል:: ነገር ግን አስኬማቸውን (የጽጽስናቆባቸውን) እዚያችኛዋ መኪና ረስተው ያንን ሊያመጡ ወጥተው ወደዚያ እንደሄዱ እኔ ገባሁ:: ብፁዕነታቸውም የእኔን መግባት በርቀት ሲያዩ በመጀመሪያይቱ መኪና ብፁዕ አቡነ ዮሴፍን ከኋላ እንዲቀመጡ አድርገው እሳቸው ጋቤና በመቀመጥ እነሱ ፊት ፊት እኛ ኋላ ኋላ ጉዟችንን ወዳልነው ቤት ቀጠልን::

እኒያ ትሁት ምእመን ቤት ስንደርስም «ዛሬ ቅዱስ ሚካኤል በዕለተ ቀኑ በረከት ወደቤቴ እንዲገባ አደረገልኝ» በማለት እጅግ ተደስተው አስተናገዱን:: ከዚያም በቆየንበት ሁኔታ ጉዞአችንን ቀጠልን:: አሰላን አልፈን ጫካ አለ:: እዚያ ዐርፈው አገኘናቸው:: እኛም ትንሽ ዕረፍት አደረግን:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ አሁንም እንደቀድሞው ፊትና ኋላ ሆነን ጉዞ ጀመርን:: አሳሳ የሚባል ወረዳ ውስጥ ስንደርስ ነጠቅ ብለው ከዓይናችን ተሰውረዋል:: ግን መጀመሪያ አርፈው ያገኘናቸው ጊዜ ሊቀ ጉባኤ «ለምንድን ነው ወደእኛ እየተጠጋችሁ ከእኛ የሚቀረውን አቧራ የምትለብሱት?» አሉን:: እኔ ያለሁበት ሾፌር ደግሞ «ጊዜው እየመሸ ስለሆነ ቶሎ ቶሎ እንዲሄዱ ብዬ ነው» ብሏቸው ነበር:: በዚያ የተነሣ ይመስለኛል ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ፈጠን ማለት ጀምረዋል::

እና በግምት ዶዶላ ልንደርስ ሠላሳ ኪ.ሜ የቀረን ይመስለኛል ስንደርስ እዚያ ላይ መኪናው ተገልብጦ አባቶቼ ወድቀው ሰዎች ተሰብስበው ሲጐትቷቸው ደረስን:: እኔ እንደደረስኩ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በጀርባቸው ነው የወደቁት፤ አንዱ ዐይናቸው ፈርጧል፣ በአፍንጫቸውና በአፉቸው ደም ይፈሳል (ይህንን የሚነግሩኝ እያነቡ ነበር) ብፁዕ አቡነ ኤልያስ እጅግ ተዝለፍልፈው ሴቶች ደግፈው ይዘዋቸዋል፣ ሊቀ ጉባኤ ደግሞ ከመኪናው ወጥተው ቆባቸው ወልቆ ደም ከራሳቸው እየወረደ « አባቶቼን ፈጀሁ፣ አባቶቼን ፈጀሁ» እያሉ እንደ ዕብድ ሲራወጡ፣ መልአከሰላም ዳኛቸውም የግማሽ አናታቸው ቆዳ ተነሥቷል እንደዚያው ወድቀው አገኘናቸው:: በወቅቱ በሆነው ነገር በእውነቱ እኔ የተረዳሁት ሰው በድንጋጤ እንደማይሞት ነው:: ለተቀደሰ ዓላማ በመጓዝ ላይ የነበሩት አባቶቼ እንደዚያ ወድቀው በማየቴ የሚጮህ የሚራመድ ድንጋይ ነበር የሆንኩት::

የሆነው ሆኖ እነሱን አፋፍሰን አባቶችን እኛ በነበርንበት መኪና መሪጌታ ታምሬንና መልአከሰላም ዳኛቸውን በጭነት መኪና አሳፍረን ወደዶዶላ ክሊኒክ ላክን:: እኔ፣ ሊቀ ብርሃናት መርቆርዮስና መሪጌታ ኤፍሬም ቀረን:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ አንድ መኪና ሲመጣ እኔን በአሰላ ከተማ ወደሚገኝ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አደረሱኝ:: የቀሩትን ሰባክያነ ወንጌል ደግሞ በዚያ ያሉ አንድ መነኩሴ መኪና ልከው ወዲያውኑ ከነጓዙ አስመጡልኝ:: ቆይቶም አባቶችን ወደዚያ የወሰደው መኪና መጣና ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ጣቢያ ሳይደርሱ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ግን ከደረሱ ከአምስት ደቂቃ በኋላ እንዳረፉ ዘማርያቱ ወ/ት ማርታና ወ/ሮ ፋንቱ ነገሩኝ:: ከዚያ በኋላ በሕይወት የተረፉትን ወደ ይርጋዓለም እንዲሄዱ ካደረግን በኋላ ወደዚህደወልን:: በአስቸኳይ መኪኖቹ ተላኩልን:: ከዚያ በእውነቱ የደረሰው ጉዳት እጅግ ያስደነገጠው ያዘነውንም የዶዶላን ሕዝብ አመስግነን ወደዚህ መጣን::

እንግዲህ ከእነሱ ተለይቼ የእኔን መዳን እግዚአብሔር ብቻ እንጂ እኔ የማውቀው ነገር የለም:: መቼም ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ካልወጣ በቀር ሰው አይሞትምና ለነገ ለዛሬ ብሎ ለትንሽ ቀን የንስሃ ዕድሜ ሊሰጠኝ እንደሆነ አላውቅም:: ያ ምሥጢር በእግዚአብሔር ብቻ ያለ ነው:: የሆነው ሆኖ ከአባቶቼ ጋር ከመጀመሪያው ጀምሮ አብረን ስለነበርን አወዳደቃቸውንም ስላየሁ እጅግ አዝኛለሁ:: በእውነቱ ሁኔታቸውም በተለይ አወዳደቃቸው ፈጽሞ ከዓይኔ ሊጠፋልኝ አልቻለም:: ወደፊትም አይመስለኝም::

*ሐመር፦ አባቶች ለዚህ የበቁበት ጉባኤስ መጨረሻው ምን ሆነ?*

*ብፁዕነታቸው፦* ጉባኤው ምንም እንኳን አባቶችን ብናጣበትም መከናወኑ አልቀረም:: ብፁዕ አቡነ ሰላማ (የአባቶች የኅልፈተ ሕይወት መርዶ አስደንግጦአቸው ቢታመሙም) ብፁዓን አባቶች

*(ወደ ገጽ 28 ዞሯል)*

## ተፎካካሪ ሆነ

**ጥያቄ:-**

ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ ስለ መልከ ጸዴቅ ሲናገር «እናት አባት የትውልድም ቁጥር የሉትም፤ ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም ብሏል» ዕብ.7÷3 ሰመሆኑ ሰብዓዊ ፍጡር ሆኖ እንዴት እናትና አባት ሳይኖረው ቻለ? ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱ ፍጻሜ ከሌለው ከእግዚአ ብሔር ጋር ተፎ ካካሪ ሆነ አይደለም ወይ?

*(ያሬድ አሸናፊ ከአምቦ)*

መልስ:- በቅድሚያ መልስ ከመስጠታችን በፊት ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራው ያን በጻፈው መልእክቱ ምዕራፍ 7 ከቁ ጥር 1–5 የጻፈውን እናስነብባለን:: «የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከ ጸዴቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው:: ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አሥራትን አካፈለው:: የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው ኋላም ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው:: አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም:: ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱ ፍጻ ሜ የለውም፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል »

*ዕብ.7÷1–3*

ቅ.ጳውሎስ ለዕብራውያን ማስ ተላለፍ የፈለገውን መገንዘብ እንድንችል ስለ መልከ ጼዴቅ የሚከተለውን ታሪክ እናቀርባለን::

ኖኅ ከጥፋት ውኃ በኋላ ለሦ ስት ልጆቹ ሴም፣ ካምና ያፌት ዓለምን አከፋ ፍሎ ሰጥቷቸው ነበር:: በዚህም ጊዜ ለካም የደረሰው ምሥራቃዊው የዓለም ክፍል ነበር:: ካምም ምሥራቃዊ የዓለምን ክፍል አቅንቷል፤ የካም ዘር ሲወልድ ሲዋለድ የመልከ ጸዴቅ ጥንት አባቱን ሴዱን ይወል ዳል:: ይህም ሴዱ ከምሥራቅ ተነሥቶ ግብ ጽን ተሻግሮ ከነዓናውያንን ድል ነሥቶ በአገ ራቸው ላይ ነግሶባቸው ስለነበር የኖባ እና የምስር ንጉሥ ልጅ ተብሏል:: የያዛትንም ቦታ በስሙ ጠርቷት ቤተሳይዳ ብሏታል:: ትርጉሙም የይ ቅርታና የጸጋ ቤት ማለት ነው:: ሴዱ ሳሌምን ይወልዳል፤ ሳሌም ደግሞ ሜልክንና መልከ ጼዴቅን ይወልዳል:: ሜልክ ታናሽ መልኬ ጼዴቅ ታላቅ ነበሩ:: አንድ ወቅት አባታቸው በአምልኮተ ጣዖት ቢወድቅ መልከ ጼዴቅን መሥዋዕት ላቅርበው ብሎ ተነሣ፤ የመልከ ጼዴቅ እናት ግን ተቃወመች በኋላም እጣ ቢወጣ ለታናሽ ወንድሙ ለሜልካ ወጣበት:: በዚህ ጊዜ መልከ ጼዴቅ ከአባቱ ቤት ወጣ:: የእግዚአብሔርም መንፈስ አጽመ አበውን እያጠነ እንዲቀመጥ ወደ ቀራንዮ መራው:: እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠውን ሲወርድ ሲዋረድ ለመልከ ጼዴቅ አባት የደረሰውን ወርቅ እጣን ከርቤ ይዞ ሄደ:: ለረጅም ዘመንም አጽመ አበውን እያጠነ በቀራንዮ ኖረው በነበረበት አገር ሰዎች ተከራክረው እውነት ይፈር ድላቸው ስለ ነበረ ንጉሠ ጽድቅ ብለው ጠርተውታል:: ተጣልተው ሲሄዱ ያስ ታርቃቸው ነበርና ንጉሠ ሰላም ብለው ጠርተውታል:: ይህም መልከ ጼዴቅ ከሌዊ የሚበልጥ ደገኛ ካህን ስለነበር በቀራንዮ ቤተመቅደስ ሠርቶ በኅብስት (ከስንዴ) እና ወይን መሥዋዕት ሲያቀርብ ኖሯል:: ዛሬም ጭምር ይህ የነበረበት ቦታ መካነ መልከ ጼዴቅ ተብሎ ይጠራል::

አምስቱ ነገሥተ ሰዶም 12 ዓመት ሙሉ ለነገሥተ ኮሎደጐሞር ሲገ ብሩ ቆይተው በ13ኛው አንገብርም በማለታቸው በተፈጠረው ግጭት የሰ ዶም ነገሥታት ድል ተነሥተው ሎጥም ተማ ረከ:: አብርሃምም ይህንን ወሬ ሲሰማ በቤቱ የነበሩትን 318 ሰዎች አስከትሎ የተማረከ ወንድሙን ሎጥን ነጻ አውጥቷል:: ዘፍ. 14÷1–16 በዚህን ጊዜ አብርሃም የረዳውን እግዚአብሔርን በዓይነሥጋ ለማየት ቢናፍቅ የእግዚአብሔር መንፈስ እሱን ለማየት አትችልም ዕድሜ ይገታሃል ብሎ ነገ ረው:: ነገር ግን ምሳሌውን እንድታይ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረህ ሂድ አለው:: አብርሃም የዮርዳኖስን ወንዝ ሲሻገር አይቶ የማያውቀውን መልከ ጼዴቅን ሲያይ በልቡ ናው ደነገጠ:: መልከ ጼዴቅም አብርሃም አትፍራ ብሎት አንተን ወደ ዮርዳኖስ እንድ ትሻገር ያዘዘህ አምላክ እኔንም ኅብ ስተ አኰቴት እና ጽዋ በረከት ይዤ ወደ ዮርዳኖስ እንድመጣና ለአንተ እንድ ሰጥህ አዞኝ ነው አለው:: ከያዘውም ኅብስትና ወይን ለአብርሃም ሰጠው፤ አብርሃምም ከያ ዘው ሁሉ አሥራትን ሰጠው:: ስለዚህ አብር ሃም ለክርስቶስ ምሳሌ የሚሆነውን አየ:: የዮርዳኖስን ወንዝ በምሳሌነት አቅርቦለት ጥምቀትና መልከ ጼዴቅ የሰጠውን ኅብስ ትና ወይን ደግሞ የክርስቶስ ሥጋና ደም በምሳሌነት አሳየው::

ቅ.ጳውሎስ ይህንን ታሪክ ሳያ ውቅ ቀርቶ አልነበረም እናትና አባት የሉትም ያለው:: ሕዝበ እሥራኤል ክህነት ከሌዊ ወገን ንጉሥነት ከነገደ ይሁዳ እንደማይወጣ ያውቅ ስለነበረ በመጽሐፉ የተቀመጠ ከሌዊ ወገን የሆነ አባትና እናት የሉትም ለማለት ነው እንጂ ያለ እናትና ያለ አባት ያለ ዘር የተገኘ ነው ለማለት አይደለም:: ነገር ግን ሕዝበ እሥራኤል በትውፊት ስለ መልከ ጼዴቅ ያውቁ ስለ ነበር መልከ ጼዴቅ ከእሥራኤላውያን አለመሆኑንና በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በጽሑፍ የተቀመጠ የትውልድ ሀገሩን የሚገልጥ አለመገኘቱን ለማስረዳት ነው::

ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱ ፍጻሜ የለ ውም ብሎ ሲናገርም ምንም እንኳን እግዚ አብሔር ለቅዱሳኑ የተሰወረ የመልከ ጼዴቅን ምሥጢር ቢገልጥላቸውም በሕዝቡ ዘንድ ግን የመልከ ጼዴቅ የሕይወቱ ጅማሬ (ልደቱ) እና ፍጻሜውም በእግዚአብሔር ስለተሰወረ ጅማሬው ይህ ነው ፍጻሜው ይህ ነው ብለው መናገር እንዳይችሉ አድር ጓቸው ነው:: ይህም ምሳሌ ሊያደርገው በመፍቀዱ ነው:: የመልከ ጼዴቅን ጅማሬ ሰዎች እንደተሰወረባቸው ሁሉ የጌታችን የኢየ ሱስ ክርስቶስም መጀመሪያው ይህ ነው የማይባል መሆኑን ለማሳየት፣ የመልከ ጼዴቅ ፍጻሜው እንደተሰወረ ሁሉ የጌ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ፍጻሜ የሌለው መሆኑን በምሳሌነት ጠቋሚ አመልካች ስላደረገው ነው:: በዘመናትና በዓመታት መልከ ጼዴቅ የኖረበት ዘመንና አሁንም ፍጻሜውም ምን እንደ ሆነ አይታወቅምና::

በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል ሲልም መልከ ጼዴቅ ለክርስቶስ ምሳሌ መባሉን መገንዘብ ያስፈልገናል:: ምሳሌ ደግሞ ከሚመስለው ነገር እጅግ በብዙ ነገር ይለያል፤ በብዙ ነገር ያንሳል:: መልከ ጼዴቅ ለክርስቶስ ምሳሌ ነው ሲባል ክርስቶስ ማን እንደሆነ እንደ ቀስት ጠቁሞ የሚያሳይ ነው ለማለት ነው:: ስለዚህ መልከ ጼዴቅ ፍጡር ክር ስቶስ ደግሞ ፈጣሪ መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል ሲባልም መልከ ጼዴቅ ያለው ክህነቱ እንደሌሎች ካህናት በሞት የሚቀር አይ ደለም ለማለት ሳይሆን በካህንነቱ በምሳ ሌነቱ የኖረበት ዘመን የሚኖርበትም ጊዜ ተቆጥሮ የማይታወቅ መሆኑን ለማሳየት ለዘላለም ብሎ ተናገ ረው::

ዘላለም የሚለው ቃል እንደ አገ ባቡ ሁለት ዓይነት ትርጉም ያዝላል:: ዘላለም የሚለውን ቃል ለእግዚአብሔር በምንጠቀምበት ጊዜ ፍጻሜ የሌለው በጊዜ ያትና በዘመናት የማይሻር መሆኑን ሲገልጥ በሌላ ጊዜም ዘላለም የሚለው ቃል ፍጻሜ ያለውን ነገር ግን ረጅም ጊዜያት ለማሳየት በመጽሐፍ ቅዱስ ገብቶ እናገኘዋለን:: ለም ሳሌ ያህል ዘሌዋ23÷21 ላይ እንደተገለፀው እግዚአብሔርን እሥራኤላውያን የበግ ጠ ቦት መስዋዕት አድርገው እንዲያቀርቡ ሲያዛቸው «በዚያን ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ይሆንላችሁ ዘንድ ታውጃላችሁ የተግባር ሥራ ሁሉ አታድርጉበት÷ በምትቀመጡ በት አገር ሁሉ ለልጅ ልጃችሁ የዘላለም ሥርዓት ነው» ብሏል:: ይህ ማለት ለረጅም ዘመናት ይህንን ሥርዓት ትፈጽማላችሁ ማለቱ እንጂ ማቆሚያ የለውም ማለቱ አይደለም:: ምክንያቱም ይህ የበግ ጠቦት ለመሥዋዕት የማቅረብ ሥርዓት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከተገለጠ በኋላ ቀርቷልና:: እንደዚሁም ሁሉ መልከ ጼዴቅ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል ማለት እንጂ ክህነቱ ፍጻሜ የለውም ማለት አይደለም::

መልከ ጼዴቅ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደሙን በስንዴ ኅብስትና በወይን ፈት ቶ እንደሰጠ ን ሁሉ (ማቴ. 24÷26–29) መልከ ጼዴቅም በኅብስት (በስንዴ) እና በወይን ያስታኩት ነበ ርና:: (ዘፍ.14÷17–20):: ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ ክህነቱን ከማንም እንዳ ልተሰጠው ሁሉ የመልከ ጼዴቅም ክህ ነት እንደሌዋውያን በዘር ያገኘው አይደለምና::

የመልከ ጼዴቅ ክህነቱ ለሌላ እን ዳልተላለፈች ሁሉ የጌታም ክህነቱ ለማንም አልተሰጠምና:: የመልከ ጼዴቅ ክህነቱ ከሌዊ ክህነት የሚበልጥ አማናዊ (እውነ ተኛ) ክህነት ነበር፤ ነውም::

## ሊመጣልኝ አልቻለም

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የትው ልድ ሐረግ ወንጌላዊ ማቴዎስና ሉቃስ ጽፈዋል:: ነገር ግን ሁለቱ ልዩነት አላቸው:: ሁለቱም ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገሩ ሆነው ለምን ተለያዩ?

*(አበበ ታሪኩ ከአ/አ)*

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ ስለ ዘር ሐረግ በሚናገረው አንቀጽ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ 14 ይላል:: ነገር ግን ስሄ 14 ሊመጣልኝ ስላልቻለ ብታብራሩልኝ?

*(ነጋ ፍቅሬ ከአ/አ)*

መልስ:- በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስን ወንጌል በተብራራ መልኩ የጻፉት

ወንጌላዊ ሉቃስና ማቴዎስ ናቸው:: ሁለቱም የሚናገሩት በሀሳብ ደረጃ ልዩነት ባይኖረውም የተጠቀሙበት የአቆጣጠር ዘይቤ ከመለያየቱ የተነሣ በአንዳንድ ቦታ የገቡት ስሞች ተለያይተዋል:: ይህንንም ለመረዳት የእሥራኤላውያንን የትውልድ አቆጣጠር ዘይቤ መረዳት ያስፈልጋል:: ቅ.ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው ለእሥራኤላውያን ሲሆን፤ ሉቃስ የጻፈው ደግሞ ለግሪኰች (ለአሕዛብ) ነው:: ለአቆጣጠሩ ልዩነት የሚሰጠውን ማብራሪያ እንደሚከተለው እንመልከት::

1ኛ ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈላቸው ለእሥራኤላውያን ሲሆን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባረገ በ8 ዓመቱ ላይ እንደ ተጻፈም ይነገራል:: በጌታችንና በመድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ እንደተሰ በከላቸው ያመኑ አይሁድ እንደነበሩ ሁሉ በእርሱ የማያምኑና ያመኑትንም ዘወትር የሚጠይቋቸው ነበሩ:: ያላመኑ አይሁድ ያመኑትን ክርስቶስ የዳዊት ልጅ የዳዊት ወገን መሆኑን አስረዱን፣ ትውልዱን ቁጠሩልን፣ ባሏቸው ጊዜ እነርሱም መምህራቸውን ወንጌላዊ ማቴዎስ ሲጠይቁት፣ አስተምሯቸው በአፍ ያለ ይረሳል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል ብሎ የአብርሃም የዳዊት ወገን መሆኑን ቆጥሮ ጽፎ ሰጣቸው:: እሥራኤላውያን አባታችን አብርሃም ነው ንጉሣችን ዳዊት ነው እያሉ ፍቅራቸውን ይገልጡ ነበርና በሚወዷቸው አባቶች የአብርሃም ልጅ የዳዊት ልጅ ብሎ ነገራቸው:: ሉቃስ ደግሞ ልደተ ሕጋዌን ተጠቅሞ ቆጠረ:: ልደተ ሕጋዌና ልደተ ሥጋዌ ማለት ሁለቱ ወንጌላውያን የተጠቀሙበት የትውልድ ሐረግ አቆጣጠር ናቸው::

ልደተ ሕጋዌ ማለት ሕጋዊ የሆነ የትውልድ አቆጣጠር ማለት ነው:: ይህም የአቆጣጠር ዘይቤ በእሥ ራኤላውያን ዘንድ ይጠቀሙበት የነበረ አቆጣጠር ነው:: እግዚአብሔር በባሪያው በሙሴ ላይ አድሮ ለእሥራኤላውያን እንደነገራቸው ሁለት ወንድማማቾች ቢኖሩ ታላቅ ወንድም በቅድሚያ ያገባ ነበር:: ታላቁ እያለ ታናሹ ቀድሞ አያ ገባም ነበርና:: ታላቅ ወንድሙ ላገባት ሚስቱ ምንም ልጅ ሳይወልድላት ቢሞት ታናሽ ወንድሙ የሟች (የወንድሙን) ሚስት አግብቶ ልጅ ይወልድ የተወለደውም ልጅ በሟች ወንድሙ የአባት ስም ይጠራ፤ ዘር ያቁምለት ተብሎ ታዞ ስለነበር ነው:: (ዘዳ.25÷5 -10, ማቴ. 22÷23–28:: ሉቃስ ይህንን ዘይቤ በመጠቀም የትውልድ ሐረጉን ቆጥሮ ተናገረ::

ልደተ ሥጋዌ ማለት ደግሞ በሥጋ ደረጃ ልጅ፤ የወለደው በአባ ትነት የሚጠራበት የትውልድ አቆጣጠር ነው:: ማቴዎስ የተጠቀመው ይህን ዘይቤ ነው::

ሀ. በበለጠ ግልጽ ለማድረግ በምሳሌ እንመልከት ወንጌላዊ ማቴዎስ ሲጽፍ « ማታን ያዕቆብን ወለደ ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ» ሲል ሉቃስ ደግሞ ሲጽፍ «ዮሴፍ የኤሊ ልጅ ነው፤ ኤሊ የማታን ልጅ ነው» ብሏል::

ያዕቆብ

ማታን ዮሴፍ

ኤሊ

እንደ ማቴዎስ አቆጣጠር የዮሴፍ አባት ያዕቆብ ሲሆን፤ እንደ ሉቃስ አቆጣጠር የዮሴፍ አባት ኤሊ ነው:: ዮሴፍ ከሁለት አባት በሥጋ የተወለደ ሳይሆን የአቆጣጠሩ ዘይቤ ሁለት አባት እንዳለው መስሎ ቀረበ:: ይህም ተጠራጣሪዎች እንደሚሉት ሁለቱም ወንጌላውያን ጉዳዩን በሚገባ የማያውቁ ሆነው ሳይሆን የአቆጣጠራቸው ዘይቤ ልዩነት ነው:: ታሪኩም እንደዚህ ነው:: ማታን ሹሻን የተባለችውን ሴት አግብቶ ያዕቆብንና ኤሊን ይወልዳል:: ኤሊ ታላቅ ያዕቆብ ደግሞ ታናሽ ነበሩ:: ኤሊ ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ይሞታል:: ታናሽ ወንድሙ የኤሊ ሚስት የነበረችውን አግብቶ ዮሴፍን ይወልዳል:: ስለዚህ ዮሴፍን በሥጋ የወለደው አባቱ ያዕቆብ ሲሆን በኦሪቱ እንደተቀመጠው ሕጋዊ የልደት አቆጣጠር ከሆነ ደግሞ ዮሴፍ የኤሊ ልጅ ሊባል ይችላል:: ስለዚህ ወንጌላዊ ሉቃስ ልደተ ሕጋዌን ተጠቅሞ የዮሴፍ አባት ኤሊ ነው ሲል ወንጌላዊ ማቴዎስ ደግሞ ልደተ ሥጋዌን ተጠቅሞ የዮሴፍ አባት ያዕቆብ ነው አለ::

ለ. ወንጌላዊ ማቴዎስ ሰላትያን የአኮንያን ልጅ እንደሆነ ሲገልጽ ሉቃስ ደግሞ ሰላትያን የኔሪ ልጅ እንደሆነ ገልጿል:: ይህም የሆነበት የአቆጣጠሩ ዘይቤ በመለያየቱ ነው:: ሚልክ የኤልትማልን ልጅ አግብቶ ኔሪን ወልዶ ይሞታል:: የኔሪን እናት ኤልያቄም አግብቶ አኮንያንን ይወልዳል:: ይህም ማለት ኔሪና አኮንያን ወንድማማቾች ሆኑ:: ኔሪ ታላቅ አኮንያን ደግሞ ታናሽ:: ታላቅ እያለ ታናሽ አያገባም ነበርና ኔሪ ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ይሞታል:: አኮንያን የኔሪን ሚስት አግብቶ ሰላትያንን ይወልዳል:: ስለዚህ ሰላትያን በሥጋ የወለደው አባቱ አኮንያን ሲሆን እስራ ኤላውያን በሙሴ ሕግ በተነገራቸው መሰረት ሲቆጠር ደግሞ ኔሪ የሰላ ትያን አባት ተብሎ ይጠራል:: ሉቃስ በልደተ ሕጋዌ ሰላትያን የኔሪ ልጅ ነው ብሎ ሲቆጥር ማቴዎስ ደግሞ በልደተ ሥጋዌ ሰላትያን የአኮንያን ልጅ ነው ብሎ ቆጠረ::

2. ማቴዎስ የቆጠረው በአጠቃላይ 42 ትውልድ ብቻ ነው:: እስራኤላውያን አብርሃም አባታችን ዳዊት ንጉሣችን ይሉ ስለነበረ በሚወዱት በሚያፈቅሩት ልንገራቸው ብሎ ከአብርሃም ጀምሮ ተስፋ የተነገረላቸውን ዋና ዋናዎቹን አንሥቶ ቆጠረ:: አብርሃም ስርወ ሃይማኖት ዳዊት ስርወ መንግሥት ተብሏልና:: ሉቃስ ደግሞ በአጠቃላይ 77ቱን ትውልድ ዘርዝሮ ለአ ሕዛብ (ለግሪኮች) ነገራቸው፤ በሚገባ ሁሉን እንዲያውቁት ብሎ::

3. ወንጌላዊ ማቴዎስ የትውልድ ሐረጉን ሲዘረዝር ከላይ ወደታች ተናገረ (ከአባት ወደ ልጅ) ለምን ቢሉ እሥራኤላውያን እግዚአብሔር ይወርዳል ይወለዳል ተብለው በነቢያት እንደተነገራቸው፣ ይህም የተስፋ ቃሉ አምላክ ሰው ሆነ በመወለዱ እን ደተፈፀመ ሊነግራቸው ርደቱን (ከሰማየ ሰማያት መውረዱን) ሊያስረዳቸው፤ ሉቃስ ደግሞ የጻፈላቸው አስቀድሞ ሃይማኖት ያልተሰበከላቸው ተስፋ ያልተነገረላቸው አሕዛብ ስለ ነበሩ ከታች ወደ ላይ (ከልጅ ወደ አባት) ቆጥሮ ነገራቸው ሥጋ አምላክ ሊላቸው ዕርገቱንም ሊያሳስባቸው ፈልጎ::

4. ወንጌላዊ ማቴዎስ ሲጽፍ የነገደ ይሁዳን ትውልድ ዘርዝሮ ጻፈ:: እስራ ኤላውያን ንጉሥነት ከነገደ ይሁዳ እንደማይወጣ በሕጋቸው ያውቁ ነበርና ምንም እንኳ የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በሥጋዌ ወይም በሕጋዌ የማይቆጠር ያለ ዘርዓ ብእሲ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ በመንሣት በኅቱም ድንግልና ወለደችው ብሎ ቢነግራቸውም እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ እውነተኛ ንጉሥ ነውና:: የአይሁድ ንጉሥ ብለውት ነበርና አቅርቦ ለመንገር የነገሥታቱን ትውልድ ይዞ በነገደ ይሁዳ ቆጥሮ ነገራቸው:: እውነተኛው ንጉሥ ይወርዳል ይወለዳል ተብሎ በነቢያት የተነገረው እርሱ ነው ሊላቸው፣ ሉቃስ ደግሞ የካህናቱን ወገን ይዞ ቆጠረ:: ምንም እንኳ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ከሌዊ ክህነት ፈጽሞ የተለየ ቢሆንም ከሌዊ ወገን ሳይሆን እንዴት የክህነቱን ሥራ ይሠራል እንዳይሉት አቅርቦ ለመንገር ፈልጎ ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ አባት ከድንግል ማርያም በድንግልና ተወለደ:: ድንግል ማርያም ደግሞ በአባቷ ከነገደ ይሁዳ በእናቷ ደግሞ ከነገደ ሌዊ ናትና፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከነገደ ይሁዳ ከነገደ ሌዊ ነው ሊባል ይችላልና ነው::

ወንጌላዊ ማቴዎስ እንደገለፀው ከባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ ያለው ትውልድ 14 ነው:: ነገር ግን እዚህ ላይ በቀጥታ ያልተገለፀው ምሥጢራዊ አነጋገር መኖሩንና ዮሴፍም የድንግል ማርያም ጠባቂ እንደሆነ እንድንረዳ ያደርገናል:: አልዓዛር ማታንና ቅስራን ይወልዳል:: ማታን ያዕቆብን ያዕቆብ ደግሞ ዮሴፍን ይወልዳል ቅስራ ደግሞ እያቄምን እያቄም ድንግል ማርያምን ይወልዳል:: ድንግል ማርያም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች::

አልዓዛር ........ .... .... ........ 10ኛ
ማታን ቅስራ ............ 11ኛ
ያዕቆብ እያቄም .......... 12ኛ
ዮሴፍ ድንግል ማርያም. ...... 13ኛ
ኢየሱስ ክርስቶስ ..... ...14ኛ

እሥራኤላውያን የትውልድ ሐረግ ሲቆጥሩ በወንድ እንጂ በሴት በኩል አይቆጥሩም ነበርና ወንጌላዊ ማቴዎስ በዮሴፍ በኩል ቆጥሮ ድንግል ማርያምን ጠቆመን::

**«አትፍረድ»**

በወንድምህ ጥፋት
በዛሬው ውድቀቱ
ሥጋው አሸንፎት
እጅ በመስጠቱ
ወይ ባለማወቁ
በንዝህላልነት
ጊዜው በማለፉ
በዓለም ሲንከራተት
አትፍረድ ደግፈው
ፀንቶ እስኪቆም
በትዕግስት ሆነህ
ድካሙን ተሸከም
ማን ያውቃል ምክንያቱ
አንተው ትሆናለህ
አምላክ ለድኅነቱ
መርጦ ያዘጋጀህ

*ሙሉነሽ(ከአ.አ)*

# ከታሪክ አንድ ገጽ

እንደዚህ ሆነ::

በአንዲት መንደር ውስጥ አንድ ሰው ነበረ:: አንደበቱ ከጸሎት እጁ ከምጽዋት ልቡ ከየዋሕት ተለይቶ የማያውቅ:: ሰው ተጣላ ማን ያስታርቅ፣ ልጅ አገባ ማን ይመርቅ ቢባል በመጀመሪያ የሚጠራው እርሱ ነው::

ለሽማግሎች መኩሪያ ለታዳጊዎች አርአያ መሆኑን የማያነሣ የለም:: ኃጢአትን ሊሠራት ቀርቶ ስሟን ያውቃታል ብሎ የሚገምት የመንደሩ ነዋሪ ከማግኘት አንድ ቀን ሰይጣን ሊመለስ ይችላል ብሎ ተስፋ የሚያደርግ ማግኘት ይቀላል::

ለብዙዎች መለወጥ፣ ለብዙዎች ለጽድቅ መመረጥ፣ ለብዙዎች ከዓለም መመለስ፣ ለብዙዎች ዓለምን ጥሎ መመንኩስ አንድም መሪ ያለያም አበረታች መካሪ እርሱ ነው::

የተናገረው ከልቡና ያስተማረው ከኅሊና ጠብ ሲል ልብ ያደርሳል ኩላሊት ያድሳል::

ያለ ሠርክ ሰዓት እህል የማይቀምስ ያለ ተርታ ነገር ነጠቅ መንጠቅ ያለ የማይለብስ መሆኑን በአካባቢው ሐይቅ ስለሌለ የባሕር ዓሦች ካልሆኑ በቀር የማይመሰክር ፍጥረት አለ ማለቱ ይቸግራል::

ትዳሩን አክባሪ ባለቤቱን አፍቃሪ በመሆኑ ከአብርሃምና ከሣራ ቀጥሎ ለሰርግ ምርቃት እርሱና ባለቤቱ ሳይጠሩ አይውሉም:: አንድ ቀን ከቤተ ክርስቲያን መልስ ወደ ቤቱ በማምራት ላይ እያለ ዓይኑ አንድ የማይወራውን ነገር ተመለከተ:: አንድ አገር ያስቸገረ መናፍቅ ከርሱ ቤት ገቢ ወጣ:: ለምን?

ባለቤቱን አግኝቶ እስኪጠይቃት ነፍሱ የቸኮለችውን ያህል የመኪና እሽቅድድም ተወዳዳሪዎች ቸኩለው አያውቁም::

ገባ::

«ይኸ ሰውየ እንዴት መጣ?»

«ሬጋ በልና አስረዳሃለሁ::»

«ለመናፍቅ ምን ርጋታ ያስፈ ልገዋል»

«እኮ ሬጋ በል»

«ለምን ታረሳሽኛለሽ?»

«ምኑን?»

የሆነ ነገር ብልጭ አለበት:: ሰይጣን እሳት ጫረና ቤንዚን ለቀቀበት::

«ምን ሊሠራ መጣ?»

«ለምን ትቈጣለህ?»ሰይጣን እሳቱን እፍ በማለት ላይ ነው::

እርስዋ ራስዋ ሰይጣን መስላ ታየችው:: ደክሞታል:: ተናዷል:: ዝሏል:: አእምሮው ዕረፍትን ብቻ ነበር የሚሻው:: ውሳኔ ለመስጠት ፡ ነገር ለማመዛዘን ዐቅሙም አልነበረው፤ አልነበረውም ብቻ ሳይሆን ዐቅሙ እንደሌለውም አላወቀም::

አድርጌት የማያውቀውን ዓይኑን አጉረጠረጠና ገፈተራት:: ወደ ኋላ ተንደረደረችና አንገትዋ ኰመዲኖው ጠርዝ ላይ አረፈ:: በስተመ ጨረሻም መሬት ላይ ተኛች:: ላንዴም ለመጨመሻም::

ነቃ፣ ነቃና አያት፣ ያደረገውን ለማስታወስ ሞከረ:: እርሱ ወይስ ሌላ ሰው? ምንድን ነው የፈጸመው? ሚስቱን ገደላት ማለት ነው? ገዳይ- ወንጀለኛ–ጨዋ–ሰላማዊ–አርአያ–ምሁር–መምህር–ገዳይ–ወንጀለኛ::

ጮኸ–ከማለት ይልቅ የጩኸቱ ድምጽ ፈነዳ ማለቱ ይቀላል::

አካባቢው በሰው ተጥለቀለቀ::

እርሱ ያለቅሳል:: ሰውም ያለቅሳል:: አለቃቀሳቸው ግን ለየቅል ነበር:: አንዱ «ክፉ ተናግራው መልአክ ቀስፏት ነው» ይላል:: አንዱ ደግሞ «የጻድቅ ሰው ዕንባ:: ድሮም የማይናገር ሰው ዕን ባው ሰይፉ ነው» ሌላው « አሁንኮ ወይ እማታለሁ ወይም እገላለሁ ብላ ይሆናል:: ይቺ ሰው መሳይ በሸንጐ የርሱ ደግነት ክፋቷን ሸፍኖላት ዛሬ እግዜር አጋለጣት::»

እርሱ ይገላል ቀርቶ ዝንብ ያባርራል ብሎ የጠረጠረ የለም:: ወንጀሉ ሁሉ የርስዋ ሆነ::

እርሱ ግን የደም ዕንባ አለቀሰ:: የሰዎችን ንግግር በሰማ ቁጥር ዕንባው ይጨምር ነበር:: «እኔ ነኝ እኔ ነኝ እኔ ነኝ» አለ ድምፁን ከፍ አድርጐ

«አይ የዋሕ ሰው:: ከባቴ አከሳ አይደል:: ስሟ በክፉ እንዳይነካ ብሎ ኰነው::» ይላል አንዱ

« ስላዘንኩባት ነው ማለቱ ኰነው» ቀጠለ ሌላው::

ሊያምነው ቀርቶ ሊሰማው የወደደ የለም:: ሰው የሚናገርለት እና እርሱ የሆነው እየተጋጨበት ኅሊናው ዞረ:: ማን ይመነው::

ለያዥ ለገራዥ ቢያስቸግርም በሽማግሌ ጥረት ሊቀመጥ ቻለ::

«አይዞህ አንተ አልገደልካት እግዜር መታት እንጂ» ይሉታል ሽማግሎች ሰብሰብ ብለው:: ያ ለርሱ መርፌ ነው ልብ የሚወጋ::

«እንዲያው እግዚአብሔርን ማመስገን አለብህ:: ፊትህ ላይ ተአምሩን ሲያሳይህ» ሲሉት ደግሞ የተወጋው ልቡ መድማት ጀመረ::

«እኔ አይደለሁም እንዴ አለና መጠራጠር ያዘ::» አሰበው/ ድርጊቱን ሁሉ አሰበው/ ነው እርሱ ነው እኔ ነኝ:: እኔ ነኝ ገዳይዋ– ተንሰቀሰቀ::

«ወይ ግሩም ጻድቃን የወንድማቸው ኃጢአት ከሚገለጥ የራሳቸው ኃጢአት ቢገለጥ የተባለው ደረሰ » አሉ አንዲት ወይዘሮ::

«የነ አባ እንጦንስ ታሪክ ሲደገም በዓይናችን አየንኰ» ሌላዋ ተቀበሉ::

ማን ይመነው:: የልቡን ማን ይወቅ:: እሳት እየከመሩበት መሆኑን ማን ይረዳ::

ጊዜያት ነጐዱ:: ሰው ሁሉ ሊረሳው ጀመረ ጉዳዩን:: እርሱ ግን የሚንተገተግ እሳት ሆኖበታል::

በመጨረሻ እንዲህ ወሰነ:: ለአንድ ለሚወደው ጓደኛው ሊነግረው:: ሐሳብ ቢከፍልልኝ ምክር ቢለግሰኝ ብሎ::

ያደረገውን:: የሆነውን ሁሉ ነገረው:: እየማለ እየተገዘተ የጓደኛው ፊት ሲለዋወጥ ታየው ነጣ–ከዚያ ቀላ መጨረሻ ላይ ጠቈረ:: «በስመ አብ ወወ ልድ ወመንፈስ ቅዱስ... ለካ አንድ ሰው የለም ባገሩ::አንተ ስናምንህ ስና

ከብርሀ–ለካ አውሬ ኑረሃል...»ሰቀጠጠው:: እናም ሸሸው «ለኔም ፈራሁህ» አለው::

«እኔኮ የነገርኩህ» አላስጨረሰውም:: « ዝም በል»

ልቡ ሌላ ነገር ፀነሰ:: የነገርኩት እንዲቀልድብኝ አይደለምኮ አለና «ባይሆን ነገሩን በልብህ ያዘው» ሲል ለመነው::

«ገና በአደባባይ ትሰቀላለህ» ሲል መለሰለት::

ብልጭ አለበት–ሰይጣን እሳት ጫረ::

ዓይኑ ዘወር ዘወር አለ–ክትክታ አነሣና ሡነዘረ

ተጥመልምሎ ወደቀ

ትኩር ብሎ ሲያየው ነፍሱ ሸሽታዋለች::

እያለቀሰ:: ደረቱን እየደቃ ወጣ:: ከቤቱ ብቻ ሳይሆን ከመንደሩ ወጣ:: ወደ በረሃው ሰው ወደ ሌለበት ዘለቀ::

ልክ መንገዱን ሲጨርስ አንድ ሽማግሌ አገኘ::

«እንደምን ዋሉ አባቴ»

«እግዚአብሐር ይመስገን ይኼ ደም ምንድነው ልጄ» ልብሱን አሳዩት ደነገጠ::

«እይውልዎት» አለና ታሪኩን መናገር ሲጀምር–ደነገጡና አፈገፈጉ::

«ዘወር በል አንተ ሰይጣን::!»

«ይምከሩኝ አባቴ ምን ላድርግ እባክዎ አያውግዙኝ»

«ዘወር በል ዲያብሎስ በል እኔንም እንዳትጨምረኝ »

«እኔኮ ከቁስሌ ትፈውሰኝ ብየ እንጂ በቁስሌ ላይ እንጨት የሚሰድማመች አጣሁ::» አለና ክትክታውን አነሣ እኒያ ሽማግሌ ወደቁ::

ሰው ሁሉ አውሬ መሰለው:: ልቡ እየደነደነ መጣ:: « ታዲያ ምን ይሁን» አለው ሰይጤ «አንተ የመጀመሪያው አይደለህ»

«ካሁን በኋላ ማንም ቁስሌን ሊነካ አይችልም» አለና በፍጥነት በረሃውን ማቋረጥ ጀመረ::

ማዶ ማዶ ነው አንድ አረጋዊ ካህን ደበሏቸውን ለብሰው ዛፍ ሥር ተቀምጠው ጸሎት ያደርሳሉ::

«ለመጨረሻ ጊዜ» አለ «ለርሳቸው ነግሬ መፍትሔ ካልሰጡኝ፣ በቁስሌ ላይ ዘይት መጨመር ትተው ኩምጣጤ ከድፉብኝ የሰው ልጅ ሁሉ ጠላቴ ነው ማለት ነው» ወሰነ::

ቀና ብለው አዩት:: ያስፈራል:: ልብሱ ደም ነክቶታል::

«ምን ሆንክ ልጄ» አሉና ከመቀመጫቸው ተነሡ:: ሠይጣን አንድ ርምጃ አፈገፈገ::

«ተቀመጥ ደክሞሃል» ድንጋዩን ለቀቁለት:: ሰይጣን ተናደደ::

«ምን ሆነሃል»

በዕንባ ጀምሮ በዕንባ ጨረሰው::

«በተሰቀለው ክርስቶስ ዛሬ ጓደኛ አገኘሁ::» ዕልል አሉ::

ሰይጣን ፈረጠጠና ዛፍ ሥር ተሸጉጦ ማየት ቀጠለ:–

በመገረም ተመለከታቸው::

«ይገርምሃል:: ሚስቴን ገድየ፣ ልጆቼን አርጄ፣ የሰው ሀብት ዘርፌ ስንት ልጃገረዶችን አባልጌ ሰው መቀመጫ ሲነሣኝ ጻድቅ መስየ እዚህ ተቀምጫለሁ:: ያንተማ ምን አላት:: በኔ አይነትኮ ያንተ በጥቂት ቀኖና ትሻራለች::»

የፊቱ ጥቁረት ቀነሰ::

ክትክታው ከእጁ ወደቀ::

«በል አሁን ካንድ ሁለት ይሻላል:: ሰው እንደሆነ ቂመኛ ነው ይቅር አይለንም:: እግዚአብሔር ግን መሐሪ ነው:: በዚህ ከቀጠልን እኛ ራሳችን ከሰይጣን መብለጣችን ነው:: ስለዚህ ገደል እንቆፍርና እዚያ ውስጥ ገብተን ንስሐ እንግባ::» አሉት:–ፈነደቀ:: ዘሎ ተነሣና ዐቀፋቸው::

እናም በዚያው ክትክታ መቈፈር ጀመረ::

እጅግ አድካሚ ሥራ ነው:: አባ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም ይደግማሉ:: ቀና ብሎ አየና እርሱም ጸሎቱን ቀጠለ::

ቀን–ሳምንት–ወር–ሁለት–ሦስት ወር ፈጀ ቁፋሮው::

ቅጠል ይበላሉ:: አብረው ስለጥንቱ እያወሩ:: ከዚያ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር መሐሪነት ያስተምሩታል ዐረፍ ሲሉ:: ይቀጥሉና ደግሞ ይቈፍራሉ::

በሰው ቁመት ልክ ገደሉ ተቈፈረ::

እንዴት እንግባ::

«አንተ እዚያው ቆየኝ ዕቃውን ሰብስቤ ምግባችንን ይዤ እኔ መጣሁ::» ተስማማ::

በገመዱ ተንጠልጥለው አባ ወጡ:: እላይ ከደረሱ በኋላ ገመዱን ሳቡት:: ደነገጠና ቀና ብሎ አያቸው::

«ልጄ አሉት አባ» የነገርኩህ ታሪክ ሁሉ ውሸት ነው:: «አንተን እንዳይሰማህ ብየ ነው ከአሁን በኋላ ምግብህን አመጣልሃለሁ እየሰገድህ፣ እየጾምክ ጸልይ:: እግዚአብሔር ይምራል» አሉት ተናደደ ክትክታው አጠገቡ የለም:: ከግራ ገደል ከቀኝ ገደል አለቀሰ:: አነባ::

«ዕንባ የኃጢአትን ክምር ትንዳለች» አሉ አባ:: ምንም አማራጭ የለም::

ጸሎቱን ጀመረ:: አባም በዘጠኝ ሰዓት ምግቡን አስበው ያመጡ ነበር::

ከሰባት ዓመት በኋላ አባ ምግቡን ሊያደርሱለት ሲሄዱ ክንፍ አውጥቶ ሲበር አዩት::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር::

## ክንፈ ኪሩቤል

• ኪሩቤል /አርባዕቱ እንስሳ/ የሥላሴን መንበር የሚሸከሙ መላእክት ሲሆኑ ስድስት ክንፍ አላቸው:: በሁለት ክንፋቸው ፊታቸውን በመሸፈን ወደላይ ይዘረጋሉ፤ በሁለት ክንፋቸው እግራቸውን በመሸፈን ወደ ታች ይዘረጋሉ፤ ቀሪውን ሁለት ክንፋቸውን ግራና ቀኝ በመዘርጋት ፀንተው ይቆማሉ:: ይህም የትእምርተ መስቀል ምሣሌ ነው::

–ስመሆኑ እኛ ከኪሩቤል ክንፍ ምን እንማራለን?

• በሁለት ክንፋቸው ፊታቸውን መሸፈናቸውና ወደላይ መዘርጋታቸው

* ትእምርተ ፍርሃት ነው /ፊትህን ማየት አይቻለንም ሲሉ ነው/

* አንድም ባህርይህን መመርመር አይቻለንም ሲሉ ነው

* አንድም ወደላይ ቢወጡ ቢወጡ አትገኝም አንተ ረቂቅ ምጡቅ ነህ ሲሉ ነው

• በሁለት ክንፋቸው እግራቸውን ሸፍነው ወደታች መዘርጋታቸው

* ከፊትህ መቆም አይቻለንም ሲሉ ነው

* አንድም ባህርይህን መስማመድ መተሳሰፍ አይቻለንም ሲሉ ነው

* አንድም ወደታቸ ቢወርዱ ቢወርዱ አንተ ረቂቅ ጥልቅ በመሆንህ አትገኝም ሲሉ ነው

• በሁለት ክንፋቸው ወዲያና ወዲህ መብረራቸው /መዘርጋታቸው/

* ትእምርተ ተልእኮ /መላላካቸው /ነው

* አንድም ከአእምሮ ወደ አእምሮ ስመፋለሳቸው ምልክት ነው

* አንድም ወደ ግራ ወደቀኝ ቢሉ በአምነት ካልፀኑ አትገኝም ሲሉ ነው::

ምንጭ:– ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ

# እናስተዋውቃችሁ

## አባ አኖሬዎስ

### /ትልቁ/

ቅዱስ አኖሬዎስ በ13ኛው ክፍለ ዘመን ከአባቱ ከቄስ ሰላማና ከእናቱ ከክርስቶስ ዘመዳ ሙገር ውስጥ ልዩ ስሙ ማትጌ በሚባል ቦታ ተወለደ:: ይህችም ቦታ የምትገኘው የሰላሌ አውራጃ አቋርጦ በሚወርደው በሙገር ወንዝ አጠገብ ነው::

/እንደ ገድለ ዜና ማርቆስ አባባል አባቱ ዘርአ አብርሃም ይባላል:: እርሱም የጸጋ ዘአብ የአቡነ ተ/ሃይማኖት አባት ዘመድ ነበር::/

ቅዱስ አኖሬዎስ ከወላጆቹ የወጣለት ስም ናርዶስ ነበር:: በሕፃንነቱ የዳዊትን ንባብ፣ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ከተማረ በኋላ በወቅቱ ከነበረው ግብጻዊ ጳጳስ ዲቁናን ተቀበለ:: ከዕለታት አንድ ቀን ሐራንኪስ የሚባል ሰው የያሬድን ዜማ በሚገባ የሚያውቅና ትርጓሜ መጻሕፍትንም ያጠናቀቀ መጥቶ ከአባቱ ቤት ዐረፈ:: ዐርፎም ረዘም ላለ ጊዜ ስለቆየ አኖሬዎስን ዜማ አስተምሮታል:: ከዚያም ወደ ደብረ አስቦ በመሄድ ከአቡነ ተ/ሃይማኖትና መነኮሳታቸው ጋር ተቀላቀለ:: ለዓመታት በገዳሙ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ አቡነ ተ/ሃይማኖት አመንኩሰው ስሙንም አኖሬዎስ አሉት::

ካመነኮሱትም በኋላ የአቡነ ተ/ሃይማኖት ተማሪዎች ሊቀ ዲያቆናት ሆኖ እንዲያስተዳድራቸው መረጡት:: በዚሁ ጊዜ ከአስተዳደሩ ጋር ከመምህሩ ከሐራንኪስ ዘንድ የተማረውን የመጻሕፍት ትርጓሜ ያስተምራቸው ነበር:: ርኀራኄውንና ትጋቱንም ከአዩ በኋላ ከአቡነ ተ/ሃይማኖት በታች የገዳሙ መጋቢ እንዲሆንላቸው መረጡት:: እስከዚህ ጊዜ ድረስ በገዳሙ ወንዶችና ሴቶች መነኮሳት በአንድነት ይኖሩ ነበር:: ነገር ግን አባ አኖሬዎስ አቡነ ተ/ሃይማኖትን «አባቴ እኛ መነኮሳት ከሴቶች መነኮሳት ማኅበር መለየት አለብን:: የወንዶች መነኮሳትና የሴቶች መነኮሳት በአት ተለይቶ ለየብቻቸው ይቀመጡ» አላቸው:: አቡነ ተ/ሃይማኖትም ነገሩን ተቀብለው መርቀው ከዚያን ቀን በኋላ የሴትና የወንድ ማዕድ ተለየ:: በዚህ ትጋቱ የተደሰቱት አቡነ ተ/ሃይማኖ ትም የቅስናን ሹመት እንዲቀበል ብለው አኖሬዎስን ወደ ጳጳሱ ላኩት:: ቅስናውን ተቀብሎም አገልግሏቸዋል::

አባ አኖሬዎስ አቡነ ተ/ሃይማኖት ካረፉ በኋላ በትግሬ ውስጥ ፀአዳ ዒምባ ወደ ተባለው ቦታ ሄደ:: በዚያ ምንም እንኳ አባ በጸሎተ ሚካኤልን ቢያገኛቸውም ብዙም አብረው ሳይቆዩ ሐምሌ 21 ቀን ዐረፉ:: አባ አኖሬዎስም ወደ ደብረ አስቦ ተመለሰ:: በዚያ ጊዜ የደብረ አሰቦ ገዳም አበምኔት አባ ፊልጶስ ነበረ::

አባ አኖሬዎስ በቆየበት ገዳም ተቀምጦ ገዳማዊ ሕይወቱን አጽንቶ ይዞ ሳለ የገዳሙ አበምኔት አባ ፊልጶስ በወቅቱ በነበረው ሊቀጳጳስ አቡነ ያዕቆብ አማካኝነት በአሥራ አንድ መምህራን ላይ ተሾመ:: አበምኔቱ ከተሾመባቸው 11 መምህራንም አንዱ አባ አኖሬዎስ ስለነበር በእጣ እንደግብጣን (ጣቁ) የተባለች አገር ደረሰችው::

አባ አኖሬዎስ ሰባት ታቦት ይዞ በመሄድ በዚያ በመትከል ማስተማር ጀመረ:: ከአገሩ ገዥ ከዘካርያስ ጋርም እንደአባትና ልጅ ይተያዩ ነበርና ዘካርያስ ለአኖሬዎስ ጉልት ሰጠው::

አባ አኖሬዎስ በዚያ እንዳለ ንጉሥ ዓምደ ጽዮን የአባቱን ዕቁባት እንዳገባ በሰማ ጊዜ ብዙ ቅዱሳንን አስከትሎ ንጉሡ ወደአለበት ከተማ ሄደ:: ከንጉሡ ጋር ከተገናኙም በኋላ «ከዚህ ምን አመጣችሁ?» ብሎ ጠየቃቸው: በዚህ ጊዜ አባ አኖሬዎስ ተነሥቶ «የአባትህ ዕቁባት እናትህ ስለሆነች ማግባትህ አግባብ አይደለም» አለው:: ንጉሡም ይኸንን በሰማ ጊዜ ተቆጥቶ «በሉ ደብድቧቸው» ብሎ አስደበደባቸው:: ጥቂት ከቆየም በኋላ «መምታታችሁን ትታችሁ የኋሊት አስራችሁ አምጧቸው» የሚል ትእዛዝ በማስተላለፉ መነኮሳቱ የኋሊት ታስረው በንጉሡና በሕዝቡ ፊት ቆሙ:: በዚህ ጊዜ አባ አኖሬዎስ በሕዝቡ መካከል ቆሞ «የአባትህን ሚስት ልታገባ አይገባህም» ብሎ ተናገረ:: ይህንን የሰማው ንጉሥም የበለጠ ተናዶ ግርፋቱን እንዲያጠኑባቸው ትእዛዝ አስተላለፈ:: በዚያን ጊዜ ደማቸው ሲፈስ ኃይለኛ እሳት ተነሥቶ ነበልባሉ እስከ ቤተ መንግሥቱ ደጅ አፍ ደርሷል:: ከዚህም የተነሣ ንጉሡና ሠራዊቱ ደንግጠው ዳግመኛ ምን እንደሚያደርጓቸው ተማከሩ:: ሆኖም ሠራዊቱ «ንጉሥ ሆይ እነዚህ መነኮሳት ሁለተኛ ወደ አንተ እንዳይቀርቡ ወደ ሩቅ አገር እናባራቸው» አሉት:: አጼ ዓምደጽዮን በዚሁ ሀሳብ በመስማማት ተከታዮቹን ቅዱሳን ወደ ተለያየ አገር ሲወስዷቸው አባ አኖሬዎስንም ወለቃ ወደሚባል ሀገር ወሰደውት በዚያ ይኖር ነበር:: ያም የደብረ ሊባኖሶች ስደት ተብሏል::

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ንጉሥ ዓምደጽዮን ሲሞት ልጁ ንዋየ ክርስቶስ /ሠይፈ አርዕድ/ መንግሥቱን ወርሶ ነገሠ:: ንጉሡ ንዋየ ክርስቶስ አባቱ ቅዱሳንን እንዳሳደደ ያውቅ ስለነበር ከየቦታው እንዲሰበስቧቸው መልእክተኞችን ላከ:: በጥቂት ቀናት ሰብስበው አመጧቸው:: አኖሬዎስም ወደቀድሞ በአቱ ጽጋጋ ተመለሰ:: በዚያም እያ[illegible] ተማረ ተቀምጦ ሳለ ንጉሥ ንዋየ ክርስቶስ እንደ አባቱ የአባቱን ዕቁባት ማግባቱን ሰማ:: እንደሱ ሌሎች ይህንን ክፉ ድርጊት የሰሙት ቅዱሳን ሁሉ ተሰብስበው ከአኖሬዎስ ጋር ንጉሡን በትህትና ለመምከርና ለማስተማር እንቢ ቢል ግን እስከሞት ድረስ ሊገሰጹት ተስማሙ::

አባ አኖሬዎስም በሞቱ ቆርጦ ፍሬምናጦስ የተባለ ደቀመዝሙር በአቱን እንዲጠብቅለት አዞ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ ወደ ንጉሡ ሄደ:: የንጉሡም ሠራዊት የመነኮሳቱን መምጣት ለንጉሡ ነገሩት:: ንጉሡም «አምጧቸው ከፊቴ አቁሟቸው» ብሎ አዘዘ:: ሲቆሙም «ስለምን መጣችሁ?» ብሎ ጠየቃቸው::

አባ አኖሬዎስም ቀበል አድርጐ «ንጉሥ ሆይ፤ ስለአንተ አንድ ነገር በመስማታችን ሐዋርያት በሲኖ[illegible]ሳቸው እንዳዘዙን ነገረ መለኮትን ልንነግርህ መጥተናል»አለው::

ይህንን ከሰማ በኋላ ንጉሥ ንዋየ ክርስቶስ ተቆጥቶ ሠራዊቱ አኖሬዎስን ከመሀል አውጥተው በመሬት ላይ እንዲጐትቱት አዘዘ:: በዚህ ጊዜ ከአፉና ከአፍንጫው ደም ፈሰሰ:: አባ አኖሬዎስ ምንም እንኳ መከራ ቢጠናበትም ከንጉሡ ጋር ክርክሩን አላቋረጠም ነበር:: ኋላም ሀገረ ጻራ ወይም ጸወን ወደምትባል አገር እንዲወሰድ በንጉሡ ትእዛዝ ተላለፈ:: ነገር ግን በዚያም ልዩ ልዩ ተአምራታዊ ሥራ እየሠራ የሕዝቡን አክብሮት አተረፈ:: ንጉሡም ይኸንን ባለመፈለጉ ከዚያ አስይዞ ዝዋይ ወደምትባል ደሴት አስወሰደው:: የአባ አኖሬዎስ ድንቅ ሥራ በዚያም እንዳበራ ባወቀ ጊዜ ከዝዋይ ዳሞት ውስጥ ገማስቄ ወደምትባል ቦታ /ወደ ገጽ 24 ዞሯል/

# ከደብረ ብርሃን ሥላሴ እስከ ሕዝበናኝ ቤተመንግሥት

*ዲ.ዳንኤል ክብረት እና*
*ሲ/ር ትዕግሥት ከበደ*

እንደምን ሰነበታችሁ
ደጎና ናችሁ ወይ
ልጆቹ ከብቶቹ
ኧረ የዝናቡ ነገር እንዴት ነው ጉበዝ?
እስቲ እሱ ፊቱን ይመልስልን::

አሁን ያለንበት ከተማ ሸኖ ይባላል:: 70 ኪ.ሜ ከአዲስ አበባ ወደ ሰሜን:: አልቆምንም እየሄድን ነው:: «ሑሩ ወመሐሩ» በሚለው አይደለም «ሑሩ ከመ ትርአዩ» በሚለው ነው:: ግራና ቀኝ ያለው መሬት ታርሶ ዝናመ ምሕረቱን ጠለ በረከቱን እየጠበቀ ነው::

ደብረ ብርሃን 130 ኪ.ሜ ከአዲስ አበባ::

ከተቈረቆረች 300 ዓመታትን ያሳለፈችው አሮጌይቱ ከተማ ደብረ ብርሃን ስሟን ያገኘችው የዛሬ አምስት መቶ ዓመት በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1426–60 ዓ.ም) በተፈጸመ ተአምር ነው::

የጥንት ስሟ ደብረ ኢባ ትባል ነበር አሉ:: በ1440ዎቹ መጀመሪያ ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ሲጉበኟት ነፍስ ያቸው ወደዳትና የድንኳን ከተማቸው አደረጉዋት:: ዛሬ የሥላሴ ቤተክር ስቲያን በታነፀበት ቦታ ሦስት አብ ያተ ክርስቲያናት ነበሩ::

በዚህ ዘመን ለሥዕልና ለመስ ቀል ስግደት አይገባም የሚሉ ደቂቀ እስጢፋ ተነሥተው ሕዝቡን አወኩት:: ንጉሡና ሊቃውንቱ በ1446 ዓ.ም ጉባኤ አድርገው መናፍቃኑ በነገረ ሃይማኖት ቢረቱም ሐሳባቸውን ከመ ለወጥ ይልቅ ውስጥ ለውስጥ ነገራ ቸውን ማስፋፋታቸውን ቀጠሉ:: በዚህም ምክንያት በጉባኤ የተረቱ በትን በሸፍጥ አስተምረዋልና ሕዝቡ ንም አውከዋልና በዘመኑ ለነበረው ፍርድ ቀረቡ:: ጉባኤውም የሞት ፍርድ ፈረደባቸው:: ፍርዱም የካቲት 2 ቀን 1446 ዓ.ም ተፈጸመ::

ቀጥሎ ያለውን ታሪክ ተአ ምረ ማርያም ተአምር 24÷66 እንዲህ ይተ ርከዋል::

ከአይሁድ ጋር አንድ የሚሆኑ እኒህን ከሃድያን ከወገሯቸው ወዲህ ሠላሳ ስምንት ቀን በሆነ ጊዜ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ስለ ጸናች ስለ እናቱ ስለ እመቤታችን ስለከበረ መስቀ ሉም የክርስቶስ መስቀል በሚከበርበት በመጋቢት 10 ቀን ሰኞ ሌሊት እግዚ አብሔር ድንቅ ተአምር አደረገ::

በንጉሡ ድንኳን በላይ ፍጹም ብርሃን ወጥቶ እንደ ጉርፍ ፈሰሰ:: ከንጉሡ ከተማ ጀምሮ በሩቅ አውራ ጃም ላይ ጐረፈ:: ያም ብርሃን በአብ ያተ ክርስቲያናት ላይ፣ በልብሳቸው ዘንድ፣በውስጠኛው መጋረጃቸውና በው ጭው በሐር መጋረጃ ላይ፣ በዓል በሚ ያከብሩበት መጋረጃም ላይ ተገለጠ::

ዳግመኛም በሰዎች ድንኳን ላይ፣ በመጋረጃቸውም ላይ፣ በሚለብ ሱትም ልብሳቸው ላይ፣ በሚታጠቁበት ትጥቃቸውም ላይ ያ ብርሃን በዕቃው ሁሉ በላይ ሰፍሮ ታየ::

በንጉሡ ድንኳን ላይም ፍጹም ደስታ ሆነ:: ያም ብርሃን ብዙ ቀን ተገልጦ ኖረ:: የዚያ ብርሃን መልኩም እንደ እሳት ላንቃ ይመስላል:: ነገር ግን አያቃጥልም ነበር:: ወደ ሰውም መታየት ልቡናን ደስ ያሰኛል::

በዚህ የተነሣ ቦታው ደብረ ብርሃን (የብርሃን ዓምባ) ተባለ

ቤተ መንግሥታቸው የነበረው በከተማዋ እምብርት ዛሬ የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተሠራበት ቦታ ላይ ነው:: በሁኔታው የተደሰቱት ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ የቅድስት ሥላሴን ቤተክ ርስቲያን ብርሃን በወረደበት ቦታ አጠ ገብ አሠሩት:: በዚያ ዘመን የደብረ ብርሃን ሥላሴ የትምህርት ማዕከል ነበረ:: አጼ ዘርዐ ያዕቆብ ድርሰቶቻቸ ውን የጻፉትና የመካከለኛው ዘመን የትርጉም ሥራዎች በአብዛኛው የተሠ ሩት በዚህ ቦታ ነበረ::

ዛሬ የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በሰፊ ግቢ መሐል መልካም ሽማግሌ መስሎ ተቀምጧል:: ውስጡ በ17ኛውና በ18ኛው መ/ክ ዘመን ቅዱ ሳት ሥዕላት ያሸበረቀ ነው:: በግራኝ ዘመን የመቃጠል ዕጣ ቢያጋጥመውም በኋላ ዘመን እየተ ደጋገመ ታድሷል::

ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ስትገቡ በስተቀኝ በኩል ከ500 ዓመት በፊት ብርሃን የወረደበት ቦታ በአጥር ታጥሮ ይታያል::

በነጋታው ሰው በሰው ተጭነን



ጉዞ ወደ ሞረትና ጅሩ ሆነ:: ወደ እነ
ዋሪ:: ወደ አዲስ አበባ መንገድ ተመ
ልሰን ወጣ እንዳልን ወደ ግራ (ለኛ
ወደቀኝ) ታጥፈን በተገመሰው ማሳ
መሐል እያቋረጥን የ60 ኪ.ሜ መንገ
ዳችንን ተያያዝነው:: አሥር ኪ.ሜ
ያህል እንደተጓዝን በስተግራችን የአን
ጐለላ ኪዳነ ምሕረትን ተሳለምናት::

አንጐለላ በሸዋው ንጉሥ ሳሕለ
ሥላሴ (1803–40ዓ.ም) እንደተመሠረ
ተች የታሪክ መረጃዎች ይጠቁማሉ::
በዚያ ዘመን ለሸዋ ሁለተኛ ትልቅ
ከተማ ነበረች:: አጼ ምኒልክ የተወ
ለዱት በዚህች ቦታ ነው:: ክርስትና
የተነሡትም በኪዳነ ምሕረት
ቤተክርስቲያን ነበር::

የንጉሥ ሳሕለ ሥላሴ ቤተ
መንግሥት የሚገኘውም በዚህች ቤተ
ክርስቲያን አጠገብ ነው:: የአድዋው
የጦር ጀግና የፊታውራሪ ገበየሁ የመቃ
ብር ሥፍራ የሚገኘው በአንጐለላ ኪዳነ
ምሕረት ነው:: የፊታውራሪ አጽም
በመስተዋት በተሠራ ማስቀመጫ በጉብ
ኝዎች በመታየት ላይ ይገኛል::

እንዲህ እንዲህ እያልን በመን
ዲዳና ደነባ በኩል ወደ እነዋሪ ዘለቅን::
የመኪናው መንገድ አበቃ:: በማኅበረ
ቅዱሳን የደብረ ብርሃን ንዑስ ማዕከል፣
የእነዋሪ ወረዳ ማዕከል ልጆችን ፈልገን
አገኘናቸው:: በረሃውን ለመውረድ
የግድ ሽኝ ሰው ያስፈልገን ነበር::

ከጠዋቱ አምስት ሰዓት ዲያ
ቆን ነቢዩን አገኘነው:: ወደዚያ የሚጓዙ
መንገደኞችን ሁሉ በመሸኘት የታወቀ
ነው:: ዕቃችንን ሁሉ ጠቅሎ ተሸክሞ
«እራሳችሁን ከተሸከማችሁ መቼ አነሳ
ችሁ» አለን::

ለቀቅናት ከተማዋን ሜዳ ሜዳ
ውን ገሠገሥን:: ሁለት የባላገር ሴቶች
ተቀላቀሉን::

እንዴ ዋላችሁ!
እግዚአብሔር ይመስገን
ወዴነው ምቴዱት?
ወደ ገዳም
ውብ ነው እኛም እንለጥቃችኋለን::
ለጠቁን::

ሜዳው ለመንገደኛ የ20 ደቂቃ
መንገድ ነው:: በስተግራ የእቴጌ ዘው
ዲቱ ሠገነት ማርያም መልካም ወይዘሮ
መስላ ትታያለች:: ዐጸድዋ «እሰግድ
ለኪ እሰግድ ለኪ» ይላል:: በስተቀኛችን
ደግሞ ንግሥት ዘውዲቱ የተወለዱባት
'ማኅደሬ' የተባለችው መንደር

« እንዴ አረፈዳችሁ» አለችን
« ዲንቅ ነን»
ገጭ አለ በረሃው ገጭ
አገሩ ሁሉ በተስኪያን ብቻ
ነው:: ያቺ ኪዳነ ምሕረት ናት፣ ያ
ሚካኤል ነው፣ ያቺ ክርስቶስ ሠምራ፣
ደግሞ ያ እዚያ ማዶ ያለው ተክለ
ሃይ ማኖት ነው

የተባረከ አገር፤

'በነሱ ነው ይ ተጠብቕን የምን
ኖር' አሉን አብረውን ከሚጓዙት የገ
ጠር ወይዛዝርት አንዷ

«ባለፈው ጊዜ መከራ መጥቶ
ብን ያተረፉን እነርሱ ናቸው»

'የምን መከራ?' ሲ/ር ትዕግ
ሥት ጠየቀች

«የተዘራውን ሁሉ ትሉ ስለለ
ኸመው:: ወረደበት፣ ወረደበትይ::
ማን ይመልሰው አዲያ! ግብርናውም
አኣ ተው»

«አዲያ እንዴ ሆናችሁ?»
አል ኳቸው ባገሩ ቋንቋ:: « የየጐጡ
ሰው መጥቶ ለጻድሑ አቤት አለ::
መስኾሉን ይዘው ቢባርኩት ጊዜ
አንዴ ወፍ ለኸ ኸበትና ለኸመው»
' ተስላችሁ ነው?' ሲ/ር ጠየቀች

«አዲያሳ ነውይ:: እናፈሳለን
ብለን ተስለን» ሌለኛዋ ነጠቅ
አደረጉና

«እያስኸሩ ኩነው:: በያመቱ
አሥራቱን ሲያስኸሩ ማት ይመጣል::
አዲያ ዘንድሮ በዴንብ አፈስስን እሳ
ቸውም ሰጡን»

የዜና ማርቆስ ገዳምን
ለማየት የሚጓዝ ሰው ሁለት
ፈተናዎች ከፊቱ ይጠብቁታል::
ሜዳው አልቆ በረሃው ሲጀመር
በአንድ ጊዜ አንድ ሰው ብቻ
የምታሳልፍ ከዘጠኝ ሜትር
የምትበልጥ ሠርጥ አለች:: ተዳፋቷ
በአፍጢም የም ትተክል ነው
የምትመስለው:: መያዣ መጨበጫ
ያላት ላመል ያህል ነው:: ከግራ
አለት ከቀኝ አለት ከላይ ሰማይ
ከመሐል እኛ:: እንደ ጣርማ በር መን
ገድ አንዱ ሲያልፍ አንዱ እንደ
ሚቆመው በየተራ ነው የሚታለፈው::

እኛም ግራቀኙን አለት እየተ
ደገፍን፤ እግራችንን ያገኘነው የአለት
ጡት ላይ እያሳረፍን ቁልቁል ወረድ
ነው:: የበረሃውን በር:: ...ጠዋት በመ
ሆኑ ወላፈኑ ገና አያቃጥልም::
በቋጥኙ ግርጌ የ45 ደቂቃውን
መንገድ ተያይ ዘነዋል:: ደፋቀና
እንላለን::

አብረውን ጉዞ የጀመሩት የገ
ጠር ወይዛዝርት ሠርጡ ላይ ተሰናብ
ተውናል:: በምትካቸው አባ ሠይፈ
ከኋላችን ለጥቀውን ደረሱብን:: እነሆ
ከፊታችን ዜና ማርቆስ ረዣዥም
ዛፎቹ ፣ጥንታዊው አጥር:: ጸጥ ረጭ
ያለው መንደር:: እነሆ ዜና ማርቆስ::

ይቀጥላል

# አባ አኖሬዎ.....

ከገጽ 22 የዞረ

አስወሰደው:: ነገር ግን ከዚያ ሁሉ
መጋዝ በኋላ ንጉሡ በቅዱሳኑ ጥንካሬ
በመሰበኩ እንዲሰደዱ ያደረጋቸውን
መነኮሳት ሁሉ እንዲመ ለሱ አድርጐ
እነሱ በጸሎታቸው እሱም በመታዘዝ
ተደጋግፈው መኖር ጀመሩ::

ይሁን እንጂ አባ አኖሬዎስ
የቆመለት ሰማያዊ ዓላማ ሠይጣንን እን
ዲተኛ አላደረገውም:: በቀደመ በአቱ
በጽጋጋ በጸሎትና በማስተማር እየተጋ
ሳለ አንድ ሰይጣን የሸመቀበት ሰው
ወደ ንጉሡ ሄዶ «ንጉሥ ሆይ፤ አኖ
ሬዎስ ሠራዊትክን ሁሉ እያመነኮሰ
ለራሱ ደቀመዛሙርት እያደረጋቸው
ነው:: አንተ በዚህ ቤተክርስተያን ትሠ
ራለህ፤ እሱም ወረብ ከሚባለው አገር
እየሠራ ነው:: እሱንም በአንተ ልክ
የሸዋ ሰዎች ይገዙለታል:: አሁንም የሚ
ሻለው ወታደሮች ልከህ እዚህ አስመ
ጣውና ቢመረመር ነው» አለው:: ንጉ
ሡም የዚያን ሰው ምክር በመስማት
አባ አኖሬዎስን ያመጡት ዘንድ ወታደ
ሮችን ላከ:: ወታደሮችም አባ አኖሬ
ዎስን የፊጥኝ አስረው ንጉሡ ፊት አቀ
ረቡት:: ነገሩን ሳያጣራ እንዲያው እን
ደተናገረው ግድሞ ወደሚባል አገር
እንዲያግዙት አዘዘ:: ከዚያም ለዓመ
ታት በስደት እንደቆየ ወደ በአቱ እን
ዲመለስ ፈቀደለትና ወደ ጽጋጋ ተመ
ለሰ:: እዚያም እንደተለመደው ጉባኤ
ዘርግቶ ደቀመዛሙርትን አሰባስቦ ማስ
ተማር ጀመረ:: እንዲህ እያስተማረ
በሚኖርበት ጊዜ ጓደኞቹና ሌሎቹ ቅዱ
ሳን የአቡነ ተ/ሃይማኖትን ዐጽም ቆፍ
ረው ለማውጣት ስለፈለጉ መልእክተኛ
ላኩበት:: እሱም በመስማማት የተክ
ለሃይማኖትን ዐጽም ከጓደኞቹ ጋር
አውጥተው በሌላ መቃብር /አዲስ
ቦታ/ ቀበሩ :: ወደ በአቱ መጥቶ
ጥቂት ከታመመ በኋላ በመቶ አራት
ዓመቱ መስከረም 18 ቀን ዓረፈ::
ዕለተ ዕረፍቱም በዚሁ ቀን ይከበራል::
አምላከ ቅዱሳን እግዚአብሔር ለአባ
ታችን የሰጠውን ጽናት ለእኛም ያድ
ለን:: የአባታችን ጸሎትና በረከቱ
አይለየን:: አሜን::

ምንጭ:- ዜና ቤተክርስቲያን ዘኢት
ዮጵያ 2ኛ ዓመት ቁጥር 23 መስከረም
30 ቀን 1940 ዓ.ም

Basset, Etudes Sur l'Histoire d' Ethiopie, (Paris, 1888), P.10; EMML 2824 fol25. C.cinti Rossini Acta Anorewos, csco scr Aetht.11 (Louvainm 1962) EMML 2824.

# ኑሯችን «እንዲጣፍጥ» እንደደሮዋ «መመረቅ» ግድ ነው እንዴ?

(አሉላ ሰይፈገብርኤል)

ሁሌም ቢሆን «መመረቅ» ያስደስታል:: ትርጉሙ ደግሞ ብዙ ነው:: በጠቅላላው ግን «መመስገን፣ ቡራኬ–ምሥጋና መቀበል፣ መብዛት፣ መበርከት» የሚለውን ፍቺ ይወስዳል በግዕዙ «ቡራኬ» የሚለው አቻው ነው:: እንደ ትርጉሙ ሁሉ ዓይነቱም ብዙ ነው:: ሕፃን ልጅ የእናቱን ወይም የጎረቤቱን ወይም የታላቆቹን መልእክት ለማድረስ ብር...ር...ር ብሎ ሄዶ ሲመለስ «ተባረክ፣ ያሳድግህ» ከሚባለው ጀምሮ በሐዋርያት ሥልጣን እስከተቀመጡት ካህናት አባቶች ቡራኬ (አይጠብቅም) ድረስ ሁሉም «ምርቃት» ነው:: ቃሉ በአንድ ትርጉም አያበቃም:: ዘመኑ ተለውጦ፣ ዘመናዊነትን አክሎ ሌላ ፍቺም አምጥቷል:: «ኮሌጅ የበጠሰ»፣ ከተማሪነት ወደ ሠራተኛነት ለመግባት የዲግሪ ወይም የዲፕሎማ ወይም የሌላ ካባ የደረበውም የሚባለው «ተመረቀ /ቀች» ነው::

ይህ ዓይነቱ ምረቃ «ገነት» መንግሥተ ሰማያት ያግባህ፣ የወለድኸው ይደግ የዘራኸው ይብቀል፣ ጠላትህን እግሩን ቁጠማ፣ ዓይኑን ጨለማ ያድርግልህ አይነቱ አይደለም:: «በተማርከው ትምህርት በሰለጠንክበት ሙያ ብቁ ሆነኻል፣ ይህንን ሙያ በተመለከተ በማንኛውም ዘርፍ መሠማራት ትችላለህ፤ ከሰው ጫንቃ ወርደህ ራስህን ችለሃል፤ አገርህን፣ ቤተሰቦችህን፣ ‹ሳይማር ያስተማረህን ወገንህን› መርዳት ትችላለህ» እንደማለት ነው::

ለዚህ መድረስ፣ ለዚህ መብቃት ደግሞ ትልቅ ነገር ነው:: ትልቅነቱ ለተመራቂዎች ብቻ አይደለም:: ለእናት–አባት፣ ለወንድም–እኅት፣ ለአኅት–አክስት ሁሉ እንጂ:: ሁሉም ደስተኞች ይሆናሉ አገርም ትደሰታለች:: የችግሯን ቀዳዳ የሚደፍን አንድ «ምሁር» አግኝታለችና:: ቤተክርስቲያንም ደስተኛ ናት:: ጉቦን፣ አድሎን ዘራፊነትን የጠላ /የተጠየፈ/፣ በገንዘቡ፣ በዕውቀቱና በጉልበቱ የሚያገለግላት ልጅ ታገኛለችና:: ምሩቃኑን እንዲህ ያደረጋቸው ደግሞ ሌላ ምንም አይደለም:: በየተቋማቱ በነበሩባቸው ዓመታት የገበዩአቸው መንፈሳዊ ዕውቀቶች እንጂ:: ለዚህ ነው ይህንን «ክብርና ዕውቀት» የሰጣቸውን አምላክ የሚያመሰግኑት፤ «ኮሌጅ በመበጠሳቸው» የማይኩሩት፣ «አትንኩኝ–የሹም ዶሮ ነኝ» የማይሉት፤ በአትሕቶ–ርዕስ (ራስን ዝቅ በማድረግ) ለሁሉ የሚታዘዙት::

ከሁሉም ከሁሉም ይህ ዓይነቱ መመረቅ ለአንድ ነገር ዋስትና ነው ተብሎ ታምኗል:: ሥራ ለማግኘት:: ወር ጠብቆ፣ ፔሮል ፈርሞ ገንዘብ ለመቀበል፣ ባለ ነጭ ኮሌታ ሥራ ለመያዝ:: ሥራው ይሠራም–አይሠራ ዋናው «ወረቀቱ» ነው–ሰርተፊኬቱ:: መግቢያ–መውጫ ፈቃዱ «ማኅተሙ» ለርሱ ነው:: ይህም አድጎ–አድጎ «ሥራ» ለመያዝ መመረቅ እንደ ግዴታ ለመቀመጥ በቅቷል:: የተመረቀ ሁሉ ሥራ ለመሥራት የበቃ ይመስል:: ቁጭ ብሎ ሰዓቱን ሲመለከት–ሲያዛጋ የሚውል እንደሌለ ሁሉ::

በመሠረቱ ትምህርት የሥራ መሠረት ነው:: ብዙ ዕውቀት የሚገበይበት ገበያ ነው:: ይሁን እንጂ የዘወትር መገኛው–መገብያው በክፍሉ ውስጥ ከሚሰጥ ዲስኩር (Lecture) አይደለም:: በንባብ፣ በልምድ፣ በመሥራትም ትምህርት ይገኛል:: ልዩነቱ መደበኛ (Formal) አለመሆኑ፣ በሰርተፊኬት አለመደገፉ ላይ ነው:: ነገር ግን ትምህርት ሁሉም ቦታ አለ:: በወረቀት አይለካም:: መለኪያው ውጤት ብቻ ነው:: ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ለዚህ ዓይነቱ ዕውቀት ትልቅ ትኩረት መስጠት ይገባቸዋል:: በመደበኛው ትምህርት (Formal Education) የተገኘውንና በሰርተፊኬት የተረጋገጠውን ብቻ በመመልከት፣ «እርሱን ካላገኘን ሞተን እንገኛለን» ማለቱ ተገቢ አይሆንም::

ኮሌጅ ባለመግባታቸው ዓለም የተደፋባቸው፣ ራሣቸውን «ያልተማሩ፣ ለሥራ የማይበቁ» አድርገው የሚቆጥሩ ወጣቶች አሉ:: ለነዚህ ዓይነቶቹ ወጣቶች «ሥራ» ማለት በሌላ ድርጅት ውስጥ መቀጠር፣ በየወሩ ገንዘብ መቁጠር፣ ሰዓት ጠብቆ ገብቶ–ሰዓት ጠብቆ መውጣት ብቻ ነው:: ሐሳቡን እንዲሰጠኝ የጠየቅሁት «ወጣት–ነጋዴ» ግን ይህንን አምርሮ ይቃወማል:: ለዚህም ራሱን አብነት አድርጎ ያቀርባል:: መርካቶ መካከል ለብዙ ዓመታት በመቀመጡ ንግድን «ተምሮታል»:: ዛሬ ግን ከጓደኛው ጋር በቅንጅት አንድ የንግድ ኩባንያ ከፍቷል:: ለርሱ ከሁሉ ነገር የሚበልጠው «የሥራ ፍቅርና ፍላጎት» ነው:: «ሥራ ለመሥራት የግድ ዲግሪና ዲፕሎማ አያስፈልግም» ባይ ነው:: እኔም እስማማለሁ:: የገበሬ ልጅ ግብርናን፣ የአናጺ ልጅ እነፃን ከቤተሰቡ ይማራል:: ከበረታ ሊያሳድገው ይችላል:: ከዚህ «የቤተሰብ ዕውቀት» ላይ ዘመናዊ ትምህርት ሲታከልበት ደግሞ ሥራው የበለጠ የተሳካ ይሆናል::

ዕድሉ፣ አጋጣሚው፣ የሁኔታዎች መመቻቸት ካለ «መማር፣ መመረቅ፣ ኮሌጅ መበጠስ» እጅግ በጣም ጥሩ ነው:: ካልተቻለ ግን ሌሎች አማራጮችን መፈለግ ግዴታ ነው:: ለዚህም ምሳሌ የምትሆን አንዲት ወጣት ልጥቀስ::

ከጥቂት ዓመታት በፊት «ሥራ» አልነበራትም:: ኮምፒውተር ተማረች:: ግን ምንም ሥራ አልተገኘም:: ለቤተሰቦቿ ሀሳብ አቀረበች:: አንድ ኮምፒውተር ገዝተው እንዲሰጧት:: ማንም አልተቀበላትም:: በሐሳቧ ጸናች:: መቁረጧን ሲመለከቱ ውኃ ላይ እንደወደቀ ጨው፣ እንደጠፋ ሀብት ቆጥረው ገዝተው ሰጧት:: ቀን–ከሌሊት ሰርታ ያወጡትን ብር መለሰች:: ዛሬ ኮምፒውተሩ የግሏ ነው:: ጥሩ ገቢ አላት:: ሥራው በዝቶባት አንድ ኮምፒውተር እስከመከራየት ደርሣለች:: ዛሬ ችግሯ «ሥራ» አይደለም:: ከደንበኞቿ መብዛት የተነሣ ሁሉን በጊዜው ለማስረከብ መቸገር እንጂ:: በዚህ ሁሉ ላይ መንፈሳዊ አገልግሎት ትሰጣለች:: ጊዜዋን ትጠቀምበታለች::

በዚህ መልኩ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል:: ለሁሉም ግን መሠረቱ የወጣቶች ውስጣዊ–ጥንካሬ መሆኑን እንረዳለን:: ብልጥ ልጅ ያለውን ይዞ ያለቅሣል:: ሰነፉ ግን ያለውን ጥሎ የሌለውን ለማንጠልጠል ይሞክራል:: ወተቷን የማያየውን በሰማይ ያለች ላም ይናፍቃል:: ለዚህም ምሳሌ አለኝ:: ትንሿ እህቴ:: ሥራ አላት:: በርግጥ ደሞዙ ከርሷ ተርፎ 10 ቤተሰብ የሚያስተዳድር አይደለም:: ግን ሁሌም ታማርራለች:: ታለቅሣለች:: ታንጎራጉራለች:: በልጅነቷ አርጅታለች:: በትዝታ መኖር ጀምራለች:: ስላላት ወይም ልታገኘው ስለምትችለው ሳይሆን ልታገኘው ስለማትችለው ነገር ታወራለች:: ስለትምህርት እንኳን ማሰብ ትታለች:: የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናዋን አንድ ጊዜ ከተፈተነች ወዲህ ለማሻሻል አስባም አታውቅ:: ሬዲዮ ማዳመጥ የለ፣ ቴሌቪዥን መመልከት የለ፣ ጋዜጣም ሆነ መጽሐፍ ማንበብ የለ:: በቃ:: የዲግሪ ወይም የዲፕሎማ ባለቤት ባለመሆኗ ዋጋ የሌላት አድርጋለችና ነገር ዓለሙን ትታዋለች::

ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ሊጠሉት፣ ሊጠየፉት፣ ሊተውት የሚገባው እንዲህ ዓይነቱን የተሣሣተ ሐሳብ ነው:: በመጀመሪያ ያላቸውን ዕውቀትና ችሎታ ለይተው ለማወቅ ይጣሩ:: ከዚያ በኋላ ያንን ያላቸውን ነገር ለማሳደግ ይማሩ:: ሁሉ ነገር በአንድ ጊዜ የሚሳካ አይደለም:: ጊዜ ይጠይቃል የጀመሩት ሥራ ፍሬ እንዲያፈራ ከተፈለገም ጊዜ /ወደ ገጽ 28 ዞሯል/

# ጭንቀት- መንስኤውና መፍትሔው

ከኤዶም

ሁልጊዜ እንኳን ባይሆን አንዳንድ ቀን አለው ነገር:: ባየነው÷ በሰማነው ወይም በኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ በሚገጥመን ችግር÷ የፈለግነውን ነገር ስናጣ÷ ብቸኝነት ሲሰማን÷ ወዳጅ ዘመድ ሲታመምብን... ከፍተኛ ሃሳብ ውስጥ እንወድቃለን፤ አእምሯችን በጭንቀት ይወጠራል:: በዚህን ጊዜ ማሰብ ማሰላሰል÷ አንዱን ማንሣት ሌላውን መጣል÷ መብከንከን÷ ከራስ ጋር እየተነጋገሩና እጅን እያወራጩ መጓዝ÷ ሲያስቡ ውሎ ሲያስቡ ማደር÷ እንባም ካልገደደ ማንባት... መለያችን ሊሆን ይችላል:: ታዲያ እግዚአብሔር ረድቶን ያቺ ጊዜ እስክታልፍ የሰማይ ወስከን ቢያው የተደፋብን÷ የቆምንባት መሬት የከዳችን÷ ፀሐይም ከሌሎች ለይታ ብርሃኗን የነፈገችን ይመስለናል::

ከዚህም ሌላ አንዳንድ ሰዎች በጭንቀት ሲያዙ ሰው ባያናግራቸው ይመርጣሉ:: ከፍተኛ ደረጃ ጭንቀት ላይ ያሉት ደግሞ ሁሉም ቀን «ደባሪ አቸው»፤ ሁሉም ሰው ጠላታቸው÷ የሚያዩትና የሚሰሙት ነገር ሁሉ በሽታቸው ነው:: ከሰው ጋር ቢጫወቱ አይጥማቸውም:: መዝሙር ቢዘመር÷ ልቅሶ ቢለቀስ÷ ለእነርሱ ምናቸውም አይደል:: አስር ቀልድ ቢቀለድ ጥርሳቸውን ብልጭ ማድረግ አይችሉም:: ዘወትር የሚያሳዩት ጨፍጋጋ ፊት ነው:: በአጭሩ የቁም በድኖች ይሆናሉ::

የአንዳንዶቹ ደግሞ የባሰ ነው:: በትንሽ ነገርም ይሁን ጭንቅ ባላቸው ጊዜ ምድራዊ ኑሮአቸውን ከሲኦል ጋር በማመሳሰል «በሞትኩና በተገላገልኩ÷ ተንጠልጥዬ ባረፍኩ÷ »ወዘተ... ማለት ያዘወትራሉ:: «የት አባቴ ልግባ÷ ምን ባደርግ ይሻለኛል?÷ ምን ቅብጥ አድርጌኝ ፈጸምኩት÷...» የተለመዱት ንግግሮቻቸው ናቸው::

በጭንቀት ከተያዙት ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ያለምንም ማስመሰልና ፍርሃት ጭንቀት የፈጠረባቸውን ችግር በጊዜው ለማስወገድ መፍትሔ ፍለጋ ሲሯሯጡ÷ አንዳንዶቹ ግን መጨነቃቸው እንዳይታወቅ ሲሉ በሚያደርጉት ጥረት ጭራሽ ለሌላ ጭንቀት ሲዳረጉ ይታያሉ:: በሰላምታ መሐል ፊታቸው እንደጨፈገገ ፈገግ ለማለት ይሞክራሉ:: ደስተኛ መስለውም ለመታየት ይጥራሉ:: ነገር ግን አስተውሎ ለተመለከታቸው የውስጣቸውን መረበሽ ለመለየት አይቸገርም:: መፍዘዛቸው÷ ቢጠሩ አለመስማታቸው÷ ጣፋጭ የእንቅልፍ ሌሊት አለማሳለፋቸው÷ በቁም የስመመን ስሜት ተውጠው መጓዛቸው÷ በተቀመጡበት መተከዛቸው÷ «የእህህ...» እንጉርጉሮ ማብዛታቸው... በጭንቀት ምን ያህል እንደተወጠሩ ያሳውቅባቸዋል::

ደረጃው የተለያየ ይሁን እንጂ ሁሉም ሰው ሊጨነቅ ይችላል:: ምን አልባትም ክርስቲያኖች የተሰማቸው ጭንቀት ያን ያህል ከባድ ችግር ሳይፈጥርባቸው መፍትሔ ሊያገኙለት በመቻላቸው ከሌሎች ይለዩ ይሆናል እንጂ ከጭንቀት ነፃ ሊሆኑ አይችሉም:: ምክንያቱም የሰው ልጅ በዓለም ሲኖር ችግር አይደርስበትም÷ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አሳሳቢ ነገር አይገጥመውም ማለት አይቻልምና::

ጭንቀት የአእምሮ መከፋፈል÷ መበታተት÷ የልቡና አለመረጋጋት በመሆኑ የሰውን ጤናማ መንፈስ በማመሰቃቀል ሰላምነስቶ ከፍተኛ የጤና መታወክና አደጋ ሊያስከትል ይችላል:: አንዳንድ ሰዎች ዝም ብለው ለሚረባውም ለማይረባውም ከመጨነቃቸው የተነሣ ለልብ ድካም፣ ለከባድ የራስ ምታት÷ ለጨጓራ ቁስለትና አስምን ለመሳሰሉ በሽታዎች ይዳረጋሉ:: አንዳንዶችም የተረጋጋ ሕይወት ስለማይኖራቸው ማኅበራዊ ኑሮአቸውም ሆነ ሥራቸው ምስቅልቅሉ ይወጣል:: የእነርሱ መጨነቅ ሳያንስ ቤተሰባቸውንም ከማስጨነቅና አልፎው ተርፈውም ኅሊናቸውን ከመሳት÷ ብሎም ራሳቸውን ከማጥፋት ወደኋላ አይሉም::

የጭንቀት መንስኤው የተለያየ ነው:: ቀላሉም ሆነ ከባድ ጭንቀት በአእምሮአችን የሚጫረው ባደረግነው ወይም በተደረገብን ነገር በሚሰማን ስሜት ምክንያት ሥነ-ልቡናዊ የማመዛዘን ችሎታችን ሲዛባ በመሆኑ ለከፍተኛውም ሆነ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኘው ጭንቀት መነሻው ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል:: ይህም የሚሆነው ሁለንተናችን ማለትም አካል÷አእምሮና ስሜት በአንድነት ተባብረው በመዘጋጀት ከዚህ አዲስ ከተከሰተው የስሜት ለውጥ ራሳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ በሚፈጥሩት አፋጣኝ መልስ ነው:: በዚህ ሂደት ውስጥ ያሉ አንዳንድ መንፈሰ ጠንካራ ሰዎች ጭንቀት የፈጠረባቸውን ችግር ጤናማ በሆነ መንገድ በቀላሉ ተቆጣጥረው መልካም ውጤት የማግኘት ችሎታ ሲኖራቸው ሌሎች መንፈሰ ልል የሆኑ ሰዎች ደግሞ ችግራቸውን ይበልጥ አባብሰው የከፋ ጭንቀት ውስጥ ሊዘፈቁ ይችላሉ::

የሆነው ሆኖ ለጭንቀት ዋንኛ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ ከሚባሉት ነገሮች መካከል የኑሮ አለመሳካት (ሥራ አጥነት÷ የፈለጉትን አለማግኘት÷ የኑሮ ውድነት)÷ ብቸኝነት÷ በዓይን ፍቅር (Sight Love) በመያዝ÷ የቅርብ ዘመድ ሕመም÷ አካለ ጎደሎነት÷ ፍርሃት÷ የበታችነት ስሜት÷ ሌሎችን ለመሆን ያለዐቅም መንጠራራትና አጉል ምኞት (የዐቅምና የፍላጎት አለመመጣጠን)÷ኃጢአት (ወንጀል መሥራት)÷ በሌ ሎች ላይ ክፉ ቃል መናገር...ወዘተ ይጠቀሳሉ::

ለምሳሌ ኃጢአት የሰውን ውስጣዊ ሰላም በማሳጣት ልቡናን ያውካል:: የነፍስ መታመም እንደመሆኑ ጭንቀትን በሰው ውስጥ በመፍጠር ሰላምን ያሳጣል:: ኅሊናን ያቆስላል:: ለዚህ ነው ኃጢአትን የሚፈጽሙ ሰዎች ሰላም የማይኖራቸው፣ ተቅበዝባዥና ጭንቀታም የሚሆኑት «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር» ኢሳ.48÷22::

አንዳንዶቹን ደግሞ ፈጽሞ ለጭንቀት ምክንያቶች ይሆናሉ ተብለው የማይታሰቡ ነገሮች ሁሉ ያስጨንቋቸዋል:: ለሚረባው ለማይረባው÷ ባነሰ በጎደለው ሁሉ ይጨነቃሉ:: ያቀዱት ካልተሳካላቸው÷ የፈተና ቀናቸው ሲቃረብ÷ የተዋሱትን ወይም በአደራ የተቀበሉትን ዕቃ እስኪመልሱ ድረስ እንቅልፍ በዓይናቸው የማይዞርባቸውም አሉ:: የአንዳንዶቹማ የሚገርም ነው:: ሲፈጠሩ 'ተጨነቁ' የተባሉ ይመስል ለማይሆን ነገር ሁሉ ይጨነቃሉ:: ለምሳሌ:- «በድንገት ብሞት ቤተሰቤ እንዴት ሆኖ ይኖር ይሆን?» ይታያችሁ ድንገት እርሱ (እርሷ) ሞተው ቤተሰባቸው በችግር ሲሰቃይ? ይህም ብቻ አይደለም «አያምጣብኝ እንጂ...» እያሉ የሌለ ነገር እያሰቡና እየፈጠሩ የሚጨነቁ እጅግ በጣም ብዙ ሰዎችን ማግኘት ይቻላል:: ከዚህም ሌላ «አያምርብኝም» ብለው የሚገምቱት አካላቸው እንዳይታይባቸው በመጨነቅ

እንደተሳቀቁ ዕድሜያቸውን የሚገፉ፣ አካለ ጎዶሎ መሆናቸው እያሳፈራቸው ይህንን አካላቸውን ለመደበቅ ከመሞከራቸውም በተጨማሪ ከፈጠሪ ጋር እየተሟገቱ በስቃይ የሚኖሩ ሰዎች ቁጥርም ጥቂት አይደለም:: አፍንጫዬ አጠረ÷ ሳላገባ ወይም ሳልወልድ ዕድሜዬ ገፋ÷ ጸጉሬ ተመለጠ÷ ሸበተ... ብለው የሚጨነቁና የተፈጥሮ ውበታቸውን ለመቀየር የሚ ጥሩ የቀሆችንም ቤት ይቁጠራቸው::

ከዚህም ሌላ ጭንቀት ከሰይጣን ጾርም ሊመጣ ይችላል:: አንዳንድ ሰዎች በሆነው ባልሆነው መጨነቃቸውን እንጂ ለምን እንደሚጨነቁ አያውቁም:: በእምነታቸው መረጋጋት አይታይባቸውም:: ከመሬት ተነሥተው «እግዚአብሔርን ካዱ÷ ተሳደቡ÷ ራሳችሁን አጥፉ» የሚል ስሜት ይፈጠርባቸዋል:: እየጸለዩ ክፉ ነገር ይታሰባቸዋል:: ታዲያ ይህም ቢሆን እዚህ ደረጃ ከመድረሱ በፊት ከኋላው የራሱ መነሻና ምክንያት ይኖረዋል:: ሰይጣን በሚያገኘው ትንሽ ቀዳዳ ገብቶ ነፍሳቸውን ያስጨንቃል::

መነሻቸው ምንም ይሁን ምን አንዳንድ ጊዜ ቀላል ናቸው ተብለው የሚታሰቡት የጭንቀት ዓይነቶች እያደር ሲደጋገሙና ምንም ዓይነት መፍትሔ ሳይፈለግላቸው ሲቀር ወደ ከፍተኛ ደረጃ ጭንቀት ሲልም ወደ አእምሮ መታወክ ደረጃ ሊያደርሱ ይችላሉ:: ስለዚህ ለጭንቀት ጊዜ ሳይሰጡት አፋጣኝ መፍትሔ መፈለግ ይገባል::

## ለመሆኑ ጭንቀት መፍትሔ ይኖረዋል?

«በእንቅርት ላይ ...» እንዲሉ አንዳንድ ሰዎች ለተፈጠረባቸው ጭንቀት መፍትሔ ይሆናል ብለው ሕይወታቸውን ወደማይፈልጉት አቅጣጫ ይለውጣሉ:: ከጭንቀት ለመሸሽ (ለመደበቅ) ሲጋራን የመሳሰሉ ዕፆችና የአልኮል ሱሰኛ (ጥገኛ) ይሆናሉ:: እንደ ቡናና ሻይ ያሉ ካፌን የበዛባቸውን ምግቦች ያዘወትራሉ:: በየዳንስ ቤቱ ሌሊቱን ሲዞሩ ማሳለፍን ይመርጣሉ:: የዕንቅልፍ ማስወገጃ መድኃኒቶችን የዕለት ምግባቸው ያደርጋሉ:: በዚህ ደግሞ ሌላ ጭንቀትን ይጨምሩ እንደሆነ እንጂ መፍትሔ አያገኙም:: ስለዚህ እንደ ዚህ ያሉትና የሰውን ልጅ ጥገኛቸው የሚያደርጉት ነገሮች በፍጹም የጭንቀት መፍትሔ ሊሆኑ አይችሉም:: እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለጭንቀት መፍትሔ ሊሆኑ ከሚችሉት ነጥቦች መካከል የተወሰኑትን ለማየት:-

### 1. ጸሎት

ጸሎት የሰው ልጅ ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር የሚነጋገርበት መንገድ ነው:: ወደ ቤተክርስቲያን ሄደን ወይም ባለንበት ሥፍራ ሆነን ጸሎት በምናደርግበት ጊዜ ችግራችንን ለአምላካችን ስንነግረው÷ ቁጥር ስፍር የሌለው ጭንቀታችን ከላያችን ላይ ይራገፋል:: ለመሆኑ ጸሎት እንዴት?

#### ሀ. በእምነት

«...እናንተ እምነት የጐደላችሁ» እናንተንማ ይልቁን እንዴት? እንግዲህ... ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ:: ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና:: ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ÷ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋልና::» ያለንን አምላክ በእምነት ብንጠይቀው አባታችን ነውና የጠየቅነውን ያደርግልናል:: ማቴ .6÷31–33:: ጭንቀት በሚሰማንና አእምሮአችን በሚወጠርበት ጊዜ በሥዕል ፊት ወይም ከቤተክርስቲያን ሄደን በእምነት ልንጸልይ ይገባል:: ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና:: «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበዳችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ÷ እኔም አሳርፋችኋለሁ::» ያለ ጌታ ከጭንቀታችን እንደሚገላግለን አምነን በጸሎት ልንጠይቀው ያስፈልጋል:: ማቴ.11÷28:: እግዚአብሔር እኛ ለእኛ ከምናስበው በላይ ስለእኛ ያስባል:: በፀሎት ተግተን ከጠየቅነው የፈለግነውን ይሰጠናል፤ የምንጠይቀው ነገር እኛን የሚጎዳን እስካልሆነ ድረስ:: «ለምኑ ይሰጣችሁማል÷ ፈልጉ ታገኛላችሁ÷ መዝጊያውን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና÷ የሚፈልግም ያገኛል:: መዝጊያውንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል:: «ሉቃ. 11÷9–11»:: ስለዚህ ተግተን በእምነት ስንጸልይ እግዚአብሔር የጭንቀቱን ምክንያት የምናውቅበትን ጥበብና መፍትሔውንም ይገልጥልናል::

#### ለ. ምስጋናን በማብዛት

አንዳንድ ጊዜ ጸሎታችን ራሱ ጭንቀት ሊፈጥርብን ይችላል:: የማይገባ ነገር መለመናችን÷ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ አለማወቃችን÷ ዘወትር «ስጠኝ÷ አድርግልኝ...» የሚል ጸሎት ብቻ ማብዛታችን... ጭንቀት ሊፈጠርብን ይችላል:: ነገር ግን ክርስቲያን ሲጸልይ ከእንደዚህ ዓይነቱ ጸሎት ይልቅ ምስጋናን ሊያበዛ ያስፈልጋል:: ሁሉን ማድረግ የሚችል÷ ይህችን የጸሎት ጊዜ የሰጠኝ በፊቱ እንድቆምም ያበቃኝ እርሱ እግዚአብሔር ነውና ሊመሰገን ይገባዋል:: እንዲሁም እኛ ከለመነው ነገር ይልቅ ሳንለምነው እንዲያው በቸርነቱ ያደረገልን ይበዛል::

ስለዚህ በጭንቀት የተወጠሩ ሰዎች ሌላ ዓይነት ጸሎት ሳያደርሱ ምስጋናን ብቻ ቢያደርሱ ጭንቀታቸው ቀለል ይልላቸዋል:: ካጡትና የለንም ከሚሉት ነገር ይልቅ ያላቸው እንደሚበልጥ ማሰብ ይችላሉና::

#### ሐ. ዘወትር

ጸሎትን አልፎ አልፎ ያውም ሲጨንቀን ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም አምላካችን በጠራነው ጊዜ የሚደርስልንና ቅርብ እንደሆነ በማመን ማድረስ ያስፈልጋል::

#### መ. ከኑዛዜ ጋር

ኑዛዜ ራስን ለካህን መግለጽ ነው:: ያስጨነቀንን በደል (ካለ) ከልብ በመናዘዝ ነፍሳችን ዕረፍት ታገኛለች:: ማድረግ የሌለብንን ነገር ፈጽመን ተጨንቀን እንደሆነም (በሰውም በእግዚአብሔርም) ከኑዛዜ በኋላ ቀልል ይልልናል::

### 2. ለንደኛ ማማከር

ጥሩ የልብ ጓደኛ ለጭንቀት መድኃኒት ነው:: በችግር ጊዜ የሚደርስልን እውነተኛ ወዳጅ ካለን የተሰማንን ሁሉ ስንገልጽለት ችግራችን መፍትሔ ያገኛል:: ጭንቀታችንም ይቀልልናል:: ስለሆነም ከልብ ጓደኛ ጋር የምናደርገው ግንኙነት በአጋጣሚ ብቻ መሆን የለበትም:: ዘወትር እየተገናኙ መወያየትና መመካከር ያስፈልጋል::

### 3. ሃሳብን መግለጽ

ጭንቀት ያለባቸው ሰዎች መፍትሔ ይሰጠኛል ለሚሉት ለወዳጅ ለዘመድ ወይም ለንስሐ አባት ወይም ለሐኪም... ቢያማክሩ በሚያገኙት ጠቃሚ ምክር ከብቸኝነት÷ ተስፋ ከመቁረጥና÷ ከጭንቀት ስሜት ይላቀቃሉ:: በቃላት መግለጽ የማይቻል እንኳን ቢሆን በጽሑፍ አስፍሮ ማንበብ መፍትሔ ያስገኛል:: እንዲሁም ከሰዎች ጋር መሳቅ መጫወት ሌላው የጭንቀት መፍትሔ ነው::

### 4. በቂ ዕረፍት ማድረግ

ለሰው ልጅ ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን የተለመደው ሥራ የማይሠራበት የዕረፍት ጊዜ ሊኖረው ያስፈልጋል:: ዘሌዋ.25÷3–4:: በዕረፍት ቀንም ከሥራችን ጋር የሚገናኙ ቁሳቁሶችን ማራቅ ይገባል:: ስለዚህ የዕረፍት ጊዜን ቤተክርስቲያን ሄዶ በማስቀደስ÷ ቃለ እግዚአብሔርን በመስማት÷ መዝሙር በማዳመጥ÷ በመተኛት... ወዘተ ማሳለፍ ጭንቀትን ያስረሳል፤ መንፈስንም ያድሳል::

**5. ሥራን በጊዜው መሥራት**

አንዳንዶች የሚጨነቁት÷ ፈተና በመውደቃቸው÷ ሥራአጥ በመሆናቸው... ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ያለፈውን ውድቀት÷ እያሰቡ ዘወትር በጸጸትና በጭንቀት ከመኖር ያለፈውን ረስቶ በአዲስ መንፈስ ዛሬ መሥራት ያለባቸውን ብቻ መሥራት ቢችሉ ጭንቀታቸው ይለቃቸዋል:: ለዚህም ተማሪ ከሆነ ማጥናት÷ ሠራተኛም ከሆነ የተሰጠውን ሥራ በጊዜው መሥራት ያስፈልጋል:: ሳይሠሩ÷ አንድ ነገር ለማግኘት ምንም ዓይነት ጥረት ሳያደርጉ ዝም ብሎ በባዶ ሜዳ መጨነቅ ዋጋ የለውም:: እግዚአብሔር አምላክም «የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» ያለው እኮ በወጣትነትህና መሥራት በምትችልበተ ጊዜ መሥራት ያለብህን ሥራ ማለቱ ነው:: ንስሐ መግባት ባለበት ጊዜ መግባት ያልቻለ ሰው ኋላ ዝም ብሎ ቢጨነቅ ጥቅም የለውም:: እንዲሁም አንድ ገና ሥራ የጀመረና የመጀመሪያ ወር ደሞዙን የተቀበለ ሠው አሁኑኑ ቤት ካልሠራሁ በማለቱ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም:: ይህንንም በጊዜው ሊያስብ ይችላልና!

**6. እውነታን መቀበል**

አንዳንድ ሰዎች ቁመናቸው እንደሚፈልጉት ባለመሆኑ÷ በመልካቸው «ቆንጆ» ባለመባላቸው÷ አካለ ጐደሎ በመሆናቸው ዘወትር እንደ ተጨነቁና እንደተማረሩ ይኖራሉ:: ይህ ግን የዋህነትና የራስን ዐቅም አለማወቅ ነው:: አንድ በቁመቱ ላይ አንዲት ስንዝር የመጨመር ስልጣንና ዐቅም የሌለው ሰው እየተጨነቀ ቢኖር የባሰ ራሱን ይጐዳ÷ የወደፊቱን ሕይወቱን ያበላሽ እንደሆን እንጂ ምንም ለውጥ ሊያመጣ አይችልም:: ስለዚህ በበሽታ ወይም በሌላ ምክንያት የተፈጠረን ነገር እንዳለ ተቀብሎ የራስን የወደፊት ኑሮ ማስተካከል እንጂ በሆነ ነገር ላይ መጨነቅ ተገቢ አይደለም:: ይልቁንም በተሰጠንና ባለን ነገር ተደስቶ በመ ኖር ከራስ አልፎ ለሌሎችም መትረፍ ይቻላል::

**7. መወሰን መቻል**

አንዳንድ ጊዜ ሁለት ነገሮች በአንድ ጊዜ ይገጥሙንና ከሁለት አንደኛውን መምረጥ ይሳነናል:: ለምሳሌ አንድ ሰው ሁለት ሥራ በአንድ ጊዜ ቢያጋጥመው ከሁለት አንዱን መርጦ መሥራት ካልቻለ መሐል ሆኖ ቢዋልል ጭንቀት እንጂ ሌላ ነገር አያተርፍም:: ስለዚህ ምንም ይሁን ምን ክርስቲያን የሚገጥመውን ነገር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በእምነት ለመወሰን መቸገር የለበትም::

**8. ቃለ እግዚአብሔርን መስማት**

በዓለም ስንኖር በዕለት ተዕለት ኑሮአችን የሚገጥሙን ችግሮች ሊያስጨንቁን ይችላሉ:: በተለያዩ ነገሮችም አእምሮአችን ሊወጠር ይችላል:: ታዲያ በዚህን ጊዜ ቤተክርስቲያን ሄዶ ወይም በካሴት (ካለ) ቃለ እግዚአብሔርን መስማት ዕረፍት ይሰጣል፤ መንፈስን ያረጋጋል:: ቃለ እግዚአብሔር መንፈስን ያድሳልና::

ከዚህም ሌላ መንፈሳችንን ሊያድሱና ሊያዝናኑን የሚችሉ እንደ ስፖርት ያሉ ነገሮችን ማዘውተርም ለጭንቀት መፍትሔ ሊሆን ይችላል:: በተረፈ ቀላልም ይሁን ከባድ ጭንቀት ሲሰማ ለብቻ ይዞ ከመጨነቅ መፍትሔ ለመፈለግ መጣር ይገባል:: በጭንቀት የተወጠረ ሰው እርሱ ተረብሾ ሌሎችን ከመረበሽ በቀር ምንም መሥራት አይችልም:: ስለዚህ በጭንቀት ተወጥሮ ራስን እየጐዱ ከመኖር ዛሬን በአግባቡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ያስፈልጋል:: ለሁሉም የእግዚአብሔር ረድኤት÷ የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## «በቅርብ የማውቃቸው...»

ከገጽ 17 የዞረ

በሰማዕትነት ያለፉበት ጉባኤ ነው በማለት በተጠናከረ መልኩ ለሦስት ቀናት እንዲ ቀጥል አድርገዋል:: በእውነቱ ብፁዕ አቡነ ሰላማ መንፈሰ ጠንካራ በመሆናቸው እጅግ አስደናቂ አባት ናቸው:: እንግዲህ ሁላችንም ብንሆን በሰማዕትነት ካለፉት አባቶቻችን ብዙ ነገሮችን ልንማር ይገባል:: የክርስቲያን ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን ሞቱም ይሰብ ካልና::

*ሐመር:- በመጨረሻ እጅግ የተደሰቱበትና ያዘኑበት አጋጣሚ ካለ ቢነግሩኝ?*

*ብፁዕነታቸው:-* የተደሰትኩበት ጊዜ አለ ብዬ የምለው በልጅነቴ ፊደለ ሐዋርያ፣ ወንጌለ ዮሐንስ በሚባሉ መጻሕፍት ፊደል ስቆጥር ኢየሩሳሌም፣ ቅፍርናሆም፣ ጥብርያዶስ፣ ደብረታቦር፣ ደብረዘይት፣ ጌቴሴማኒ ወዘተ... የሚሉትን ጌታችን ልዩ ልዩ ተአምራት ያደረገባቸውን ቦታዎች አነብ ነበር:: እና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እነዚህን ቦታ ዎች ለማየትም እጅግ እጓጓ ነበር:: ኢየሩሳሌም ሲባል ልቤ ድንግጥ ይል ነበር:: ለማየት እጅግ አድርጌ እጓጓ ነበር:: ምኞትም ቢኖረኝ አቅም አልነበረኝም:: ነገር ግን ድንገት ሳላስበው በ1983 ዓ.ም በቤተክርስቲያን ጉዳይ እንድሄድ ተነገረኝ:: እውነት ነው የምልህ አየሩ ላይ እስከ ምወጣ ድረስ አላመንኩም ነበር:: አየሩ (አውሮፕላን) ላይ ከወጣሁም በኋላ እውነት እደርስ ይሆን? እያልኩ እግዚአብሔርን እያ መሰገንኩ እመቤታችን ከተሰ ደደችበት ቦታ ግብጽ አረፍን:: ምንም እንኳን ከአየር ማረፊያው ባንወጣም እመቤታችን ልጇን ወዳጇን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዛ የተሰደደችባትን አገር በመርገጤ እጅግ ተደስቻ ለሁ:: ከዚያም ተነሥተን ቴላቪቭ ስንገባ መሬቱን ሳምኩት:: ቆይቶም ኢየሩሳሌም ገብተን ቀራንዮ ተሳልመን ጌታ የታሠረበት ቦታ ነው በተባለው ምድር ቤት ስንገባ በእውነቱ የደስታ እንባ እጅግ አድርጌ አንብቻለሁ:: እና በዚያ ጉዞዬ ደብረታቦርን፣ ቅፍርናሆምን፣ ጥብርያዶስን፣ ጌቴሴማኒን፣ ደብረ ዘይትን፣ ቆሮንቶስን፣ የኤልሳዕ ውሃን ምናለፋህ ያንጊዜ በልጅነቴ ያነበብኳቸው ውን ቦታዎች ሁሉና ሌሎችንም አየሁ:: እና በእውነቱ ያኔ በሕይወቴ ትልቁን ደስታ ተደስቼአለሁ::

ኃዘን ሳልከኝ ግን አሁን አባቶቼን ከፊቴ ባጣሁ ጊዜ እጅግ አዝኛለሁ:: በቅርብ የማውቃቸውና የምወዳቸው የወንጌል መልእክተኞች የእግዚአብሔር አገልጋዮች በፊቴ በዚያ ሁኔታ አሰቃቂ መከራ ሲደርስባቸው፣ አወዳደቃቸውንም በማየቴ እጅግ አዝኛለሁ:: በራሴ በኩል በብዙ መከራ ተፈትኛለሁ:: ገና በተማሪነት ሕይወቴ ነቀርሳ በተባለው በሽታ ተይዤ ጉሮሮዬ ውኃ እያፈሰሰ ልብሴን እያበሰበሰ ለሰባት ዓመታት ያህል በእጅጉ ተሰቃይቻለሁ:: በዚያ ጊዜ ተስፋ የማደርገው ሞትን ስለነበር እጅግም አይሰማኝም ነበር:: የተሰማኝ በጣም በጣም አሁኑኑም በዓይኔ ተስሎ እያስቸገረኝ ያለ ጉዳይ የአባቶቼ አወዳደቅ ነው:: በባዕት ተወስነው ውዳሴ ማርያም እየደገሙ በተድላ በደስታ መኖር ሲችሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት ብለው ወንጌልን ለማዳረስ ብለው በዚያ ሁኔታ ማለፋቸው ያሳዝነኛል ሽማግሌው አባቴ ብፁዕ አቡነ ኤልያስም ብዙ ሲጠበቅባቸው በፊቴ ድፍት ብለው በእኔ እጅ በመነሣታቸው በጣም አዝኛለሁ:: እግዚአብሔር ነፍሳቸውን በአብርሃምና በይስሃቅ ነፍስ አጠገብ እንዲያስቀምጥ እጸልያለሁ::

*ሐመር :- እግዚአብሔር ረጅሙን ዕድሜ ይስጥልኝ*

*ብፁዕነታቸው:- አሜን::*

## ኑሮችን ...

/ከገጽ 25 የዞረ/

መስጠት ያስፈልጋል:: ሰኔ ላይ የዘሩትን ሐምሌ ካላጨድሁ ማለት ግን ትርፉ ቀቢፀ-ተስፋ ብቻ ነው::

በሰንበት ት/ቤቶች ውስጥ የሚገኙ «ሥራ አጥ» ወጣቶች በመሰባ ሰብ ሥራ ሊፈጥሩ ስለሚችሉባቸው መንገዶች መመካከር ይኖርባቸዋል:: ለዚህም በዕውቀትም ሆነ በልምድ ከነርሱ የተሻሉትን በመጋበዝ ምክራቸውን ይለግሷቸው ዘንድ መጠየቁ መልካም ይሆናል:: በዚህ ሁሉ ላይ ፈቃደ-እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ በጸሎት ቢተጉ ረድኤተ-እግዚአብሔር ይታከልበታል:: ዕውቀቱንና ጥበቡን ይገልጥላቸዋል:: መንገዶችን ያመለክታቸዋል:: የሰውን ልብ ያራራላቸዋል:: በመንገዳቸው ሁሉ ይመራቸዋል:: መውጣታቸው እና መግባታቸውን ይጠብቃል::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## ተደብቄ ልቁረብ?

*__ጥያቄ__:- ከጓደኞቼ ጋር ሆነን ብዙ ጊዜ ወደ ገዳማት መሄድና በአባቶች መመከር እንወዳለን:: በተለይም ከአንድ በቅርብ ካለ ገዳም ያሉ አባት ዘንድ ሄዶ የተወሰነ ጊዜ አሳልፎ መንፈስን አድሶ መመለስ ደስ ይለናል:: እርሳቸውም በተገናኘን ቁጥር የሚያስተምሩን ስለ ንስሐና ቅዱስ ቁርባን ነው:: ነገር ግን በከተማ ያሉት የንስሐ አባቴ ሴት ልጅ የወር አበባ ካየችበት ጊዜ ጀምሮ እጮኛ ካልያዘች ወይም ካላገባች መቁረብ የለባትም ብለው አንዳንድ ምክንያቶችን ገለጹልኝ:: እኔ ደግሞ ልቤ ሊቀበለው አልቻለም:: የሰው ልጅ ድንገት ምን እንደሚገጥመው አይታወቅምና ድምጼን ሳላሰማ የሌሎች አባቶቼን ትምህርት ተቀብዬ ራቅ ወዳለ ሥፍራ ሄጄ ለመቁረብ ወስኜአለሁና ምን ትሉኛላችሁ?*

*ፍቅርተ ሃና*
*/ አ.አ/*

__መልስ__:- እንደቤተክርስቲያናችን ትምህርት አንድ ሰው ወደ ገዳም የሚሄድበት በቂ ምክንያት ሊኖረው ያስፈልጋል:: በረከት ለማግኘት÷በዓላትን ለማክበር÷ ለምንኩስና÷ለመሳሰሉት ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን አንዳንድ ወጣቶች ከዚህ ውጭ በሆነ መልኩ ያለ በቂ ምክንያት ወደ ገዳም መሄድ ያዘወትራሉ:: አባቶችንም ሥራ ያስፈታሉ:: ለአንዳንዶቹም የተለያዩ ነገሮችን በመስጠት ከዓላማቸው ያዘናጓቸዋል:: በራሳቸውም ላይ ፈተና ያመጣሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ የተለያዩ አባቶችን በንስሐ አባትነት በመያዝ ከአንዱ ገዳም ወደ ሌላው እንደዞሩ ዕድሜአቸውን በከንቱ ያሳልፋሉ:: ከዚህ አንጻር እናንተም ለምን ወደ ገዳማት መሄድ እንደም ታዘወትሩ ራሳችሁን ልትመረምሩ ያስፈልጋል:: በተለይ «እንመከራለን» በሚል ሰበብ ብቻ በየጊዜው እየሄዳችሁ ከሆነ ኑሮአቸውን በገዳም ወስነው በጸሎት የሚተጉትን አባቶች ሥራ ባታስፈቱና ጊዜአቸውንም ባታባክኑ መልካም ነው:: አንዳንድ ወጣቶች እንደሚያደርጉት በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደ ገዳማት እየሄዱ ለመመከር በሚል ሰበብ ስለወደፊቱ ዕድላቸው እንደ ጠንቋይ አባቶችን መጠየቁ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ውጪ ነው::

በተጨማሪም ንስሐ የሚገባው ለአንድ ንስሐ አባት እንጂ እንደ ሁኔታው እየታየ ከአንድ በላይ ለሆኑ አባቶች መሆን የለበትም:: እናንተም እንደዚህ ባታደርጉ ኖሮ ከተለያዩ አባቶች የተለያየ ትምህርት ባላገኛችሁ ነበር::

ያም ሆነ ይህ በገዳም ያሉት አባት ትክክለኛውን የቤተክርስቲያን ትምህርትና ማንኛውም ክርስቲያን ማድረግ የሚገባውን ነው ያስተማሯችሁ:: በመሆኑም አንድ ክርስቲያን ዘወትር ራሱን እየመረመረ (ንስሐ እየገባ) ቅዱስ ቁርባን መቀበል አለበት:: ቅዱስ ቁርባንን ንስሐ የገባ ምእመን ያለ ዕድሜ ገደብ ሊቀበል ይችላል:: ከዚህ ውጪ በደፈናው«ሴት ልጅ የወር አበባ ማየት ከጀመረች በኋላ እጮኛ ሳትይዝ ወይም ሳታገባ መቁረብ የለባትም»የሚባለው አባባል ግን ትክክል አይደለም:: ይሁን እንጂ በከተማ ያሉት መምህረ ንስሐሽ ከአንቺ የመንፈሳዊ ሕይወት ብስለት ደረጃና ከዕድሜሽ ጋር አገናዝበው ማድረግ ያለብሽንና የሌለብሽን ለይተው ሊሆን ይችላል ያስተማሩሽ:: ምን አልባምትም «ቅዱስ ቁርባን መቀበል የለብሽም» ሲሉሽ÷በሚገባ ሥርዓቱን አታውቂም÷ በመንፈሳዊ ሕይወትሽ አልተረጋጋሽ ወይም በስሜት ተገፋፍተሽ ታደርጊዋለሽ የሚል ምክንያት ይኖራቸው ይሆናል:: ለዚህም ሊሆን ይችላል «እጮኛ ሲኖርሽ ወይም ስታገቢና ስትረጋጊ ትቆርቢያለሽ»ያሉሽ:: በመሆኑም በሚገባ ቃለ እግዚአብሔርን ብትማሪና የሚሰጡሽን ቀኖና ብትፈጽሚ መልካም ነው:: የአንቺ በመንፈሳዊ ሕይወት መብሰል÷መረጋጋትና ለቅዱስ ቁርባን ምቹ ሕይወትን ይዞ መገኘት ከዚያ በፊትም እንድትቀበይ ያደርግሻልና በቅድሚያ የራስሽን መንፈሳዊ ሕይወት መርምሪ::

በተረፈ ከንስሐ አባትሽ ፈቃድና ትምህርት ውጭ ተደብቀሽ ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ማሰብሽ ግን ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጪ መሆን ነው:: እኔ ዐውቃለሁ የሚል ትዕቢትም ሊያስመስልብሽ ይችላል:: ስለዚህ በቅድሚያ ከመምህረ ንስሐሽ ጋር በግልጽ ተወያይተሽ የሚሰጥሽን ቀኖና ፈጽሚና ትቆርቢያለሽ ካሉሽ ብቻ ቁረቢ::

## ያለፈው ሕይወቴ አስጨነቀኝ

*__ጥያቄ__.2 በአሁኑ ወቅት ባለ ትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነኝ:: ከትዳር ጓደኛዬ ጋር ትዳራችንን የመሠረትነው በቤተክርስቲያን ሥርዓት አይደለም:: በአጋጣሚ በመጠጥ መንፈስ ሆቴል አድሬ እርሷም እዚያው ትሠራ በነበረችበት ጊዜ በመቀራረባችንና በመዋደዳችን ነው:: በአሁኑ ጊዜ ኑሮአችን ተመቻችቶልናል:: ሁለት ልጆችንም ወልደናል:: ነገር ግን ባለፈው የፈፀምነው ኃጢአት (ዝሙት) እያስጨነቀን ነው:: እባካችሁን እንዴት ንስሐ ገብተን ኃጢአታችንን እንደሚሠረይልን ዘርዘር ባለ ሁኔታ ብታስረዱን::*

*ኀ/ጊዮርጊስ /አ.አ/*

__መልስ__:- ንስሐ ለክርስቲያኖች ለመዳናችን የተሰጠን ታላቅ ጸጋ ነው:: ብንበድል ከበደል የምንነጻው÷በኃጢአት ብንወድቅም የምንነሣው በንስሐ ነው:: ስለዚህ የበደለ ራሱ ንስሐ ሊገባና ያለፈ ማንነቱን ትቶ በአዲስ መንፈስ ሊጓዝ ያስፈልጋል:: ሰው ሆኖም የማይበድል ስለሌለ ሁሉም ክርስቲያን በየጊዜው ንስሐ መግባት ይኖርበታል::

ወንድማችን እናንተም በማንኛውም መንገድ ትዳራችሁን ብትመሠርቱ የእግዚአብሔር ጥሪው ደርሷችሁ ልቦናችሁ ወደ ንስሐ ማምራቱ እጅግ የሚያስደስት ነው:: በክርስትና ሕይወት ትልቁ ነገር ያለፈውን የኃጢአት ሕይወት ዘወትር እያሰቡ መቆዘምና ባለፈው መቆጨት ሳይሆን በንስሐ ተመልሶ አዲስ ሕይወት መጀመር ነው:: ስለዚህ ዛሬ ነገ ሳትሉ ንስሐ ገብታችሁ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ልትቀበሉ ያስፈልጋል:: ይህም ኑሮአችሁን የተሟላና አንድነታችሁን የጸና ያደርገዋል:: ትዳራችሁም ይባረካል:: ለዚህም በቅድሚያ በአጥቢያ ቤተክርስቲያናችሁ ካሉት አባቶች መካከል አንድ መምህረ ንስሐ (የንስሐ አባት) ይዛችሁ ስለ ንስሐ ተማሩ:: ከዚያ በኋላ ንስሐ ገብታችሁ መቁረብ ትችላላችሁ:: በመሆኑም ንስሐ አባት ፊት ለመቅረብ እንዳትፈሩ::

በተረፈ ባለፈው ሕይወታችሁ መጨነቅ የዛሬውንና የነገውን ሕይወት ማበላሸት ነው:: ስለዚህ ያለፈውን ሕይወት ረስታችሁ ያንን የኃጢአት ኑሮ ትታችሁ በአዲስ መንፈስ መጓዝ ልትጀምሩ ይገባል:: እግዚአብሔር ማንንም አይንቅም:: ፈያታዊ ዘየማንን (በጌታ ቀኝ የተሰቀለውን ሽፍታ) በንስሐ የተቀበለ ጌታ እናንተን የማይቀበልበት ምንም ምክንያት አይኖርም:: በክርስትና ሕይወት ስትኖሩም ዋንኛው ነገር ያለፈ ማንነታችሁ ሳይሆን የዛሬውና የወደፊቱ መንፈሳዊ ሕይወታችሁ ነው::

## እርማት

በሐመር 7ኛ ዓመት ቁጥር 2 እትማችን በ«ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ» ዓምድ ገጽ 31- 6ኛ አንቀጽ ላይ «ነገር ግን አንድም ብሎ ከአተረጓጐም ሕጉ ውጭ ትርጉም የተረጐመ ብዙ ሐተታ አትቶ በቂ አስረጅ ያመጣ የተደበቀውን ያወጣ እንደሆነ መናፍቅ ይባላል::»የሚለው ዐረፍተ ነገር «ነገር ግን አንድም ብሎ ከአተረጓጐም ሕጉ ውጭ ትርጉም የተረጐመ መናፍቅ ይባላል» ተብሎ እንዲነበብ ከይቅርታ ጋር እንጠይቃለን::

# የግእዝ ቅኔ

*ከ(አቡጊዳ)*

ቅኔ የሚለው ቃል « ቀነ
የ» ካለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን
ትርጉሙም ጮኸ፣ አጉረመረመ፣
ቆዘመ፣ ሙሾ አወጣ፣ ቀነቀነ፣
መራ፣ ተቀኘ፣ ዘፈነ፣ ገጠመ፣
ግጥም አወጣ፣ ባለቅኔ ሆነ፣ ተፈላ
ሰፈ፣ ፈላስፋ ሆነ ማለት ነው።

ቅኔ ምናልባት
በዚህ ዘመን በዚህ
ዓመተ ዓለም ብሎ
ወስኖ መናገር አይቻል
ይሆናል እንጂ የተጀመ
ረበት ዘመን ከጌታ
ልደት በፊት በብዙ ሺህ
የሚቆጠሩ ዓመታት እንዳሉት የታ
መነ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል።
ይኸውም ቅዱስ መጽሐፉችን ነው።

ለመጥቀስም ያህል «እግዚ
አብሔርን አመስግኑ፤ ስሙንም ጥሩ
ለአሕዛብ ሥራውን አውሩ ተቀኙ
ለት፣ ዘምሩለት» መዝ.99÷1–2
/1ኛ ዜና. 16÷8–9፤/ «ለእግዚአብ
ሔር አዲሱን ቅኔ ተቀኙለት»
መዝ.149÷1፤ «አሁን ስለወዳጄና
ስለወይን ቦታው ለወዳጄ እቀኛለሁ»
ኢሳ. 5÷1፤ «ታላቅ ሥራ ሠርቷልና
ለእግዚአብሔር ተቀኙ» ኢሳ. 12÷5

በሐዲሳትም ስለቅኔ ጥን
ታዊነትና መንፈሳዊነት የሚያስረዱ
ጥቅሶችን እናገኛለን። « በመዝሙ
ርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ
እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፥ ለጌታ
በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ»
ኤፌ.5÷19፤ « የእግዚአብሔር ቃል
በሙላት ይኑርባችሁ፥ በጥበብ ሁሉ
እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገስፁ፤
በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም
ቅኔ በፀጋው በልባችሁ ለእግዚአ
ብሔር ዘምሩ» ቆላ.3÷16–17

የግእዝ ቅኔ በኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
መገልገያ ከሆኑት መንፈሳውያን
ድርሰቶች አንዱ ነው። በመሆኑም
በቤተክርቲያናችን ውስጥ ሰፊ የሆነ
የአገልግሎት ቦታ (ስፍራ) አለው።
በዚህ ጽሑፍ ስለቅኔ አመጣጥ፣ ምን
ነት፣ ዓይነቶች፣ ክፍሎችና መንገ
ዶች ለመመልከት እንሞክራለን።

የግእዝ ቅኔ ከየት መጣ?
ማንስ ደረሰው? ለሚሉት ጥያቄዎች
ሊቃውንት የየራሳቸውን መልስ
ይሰጣሉ። በመሆኑም እኩሎቹ
ቅዱስ ያሬድ፣ እኩሎቹ ደግሞ ተዋ
ነይ ነው፣ ሌሎቹ ደግሞ በፍጹም
ይህ ሁሉ ሐሰት ነው ዮሐንስ
ገብላዊ የደረሰው መንፈሳዊ
ድርሰት ነው ይላሉ። ሌሎችም
እንደዚሁ የሌ ሎችን ሊቃውንት
ስም እየጠቀሱ ይናገራሉ። ነገር ግን
እንደ እውነቱ ሌሎች የተጠቀሱት
ሊቃውንት ሊያስፋፉት ይችሉ
ይሆናል እንጂ የመጀመሪያው
የግእዝ ቅኔ ደራሽ ቅዱስ ያሬድ
መሆኑ አያጠራጥርም። በእርግጥ
በድጓው የሚገኙት ቅኔያት የቤት
አገጣጠም እንደ አሁኖቹ በቤት
ያልተከፋፈለ እንደ ጉት ያለ ነበር።
የቅኔ ቤቱ የተወሰ ነው በአፄ
እስክንድር ጊዜ ነውና። ይህንንም
አስመልክቶ አንድ ሊቅ
የሚከተለውን ቅኔ ተቀኝቷል።

ተትሕተ ያሬድ ዘኢተትሕተ
ለቅኔያቲሁ ደቂቅ እስመ ኢሐነፀ ቤተ

ፍችውም፦ ያልተዋረደ ያሬድ ተዋ
ረደ፡ ለቅኔ ልጆች ቤት አልሠ
ራምና።

## የግእዝ ቅኔ ዓይነቶች

የቅኔ ዓይነቶች ዘጠኝ
ሲሆኑ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው
ስም፣ ትርጉምና ሐተታ አላቸው።
እነዚህን የቅኔ ዓይነቶች ከአንዳንድ
ምሳሌ ጋር እንደሚከተለው ለማየት
እንሞክራለን።

ቅኔዎቹ የተገኙት ከመም
ህር ሙሴ ገ/ጻድቅ በመንበረ ፓት
ርያርክ ቅድስት ማርያም የቅኔ
መምህር ከሆኑት ነው። ዝግጅት
ክፍላችን መምህር ሙሴን ያመሰግ
ናል።

### 1. ጉባኤ ቃና ቅኔ

ይህ የቅኔ ዓይነት ' ጉባኤ
ቃና' የሚለውን ስያሜ ያገኘው
በቃና ዘገሊላ ዕለት ስለተደረሰ
ነው። የደረሰውም ንጉሥ በዕደ
ማርያም ነው። ሌሎች ናቸው የሚ
ባሉ ምክንያተ ስያሜዎችም አሉ።
ለምሳሌ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ቃና
በሚባል ሀገር የተደረገ ጉባኤ የተደ
ረሰም ግጥም በመሆኑ ጉባኤ ቃና
ተባለ ይባላል።

ጉባኤ ቃና ቅኔ
ሁለት ሁለት ቤት ያለው
ሲሆን ዕዝል፣ ግእዝ፣
አጭርና ረጅም ጉባኤ ቃና
የሚባሉ የዜማ ዓይነቶች
አሉት። ሁለት ቤት
የሆነበትም ምክ ንያት
የትስብእትና የመለ ኮት
ምሳሌ ነው።

ይህ ቅኔ ነገረ መስቀልን
የሚያዘክር በመሆኑ ረቡዕና ዓርብ
ስብሐተ ነግህ በተቆመ ጊዜ ይደረ
ሳል። በትምህርትም ጊዜ የአፍ
መፍቻ የስልት መልመጃ ነው፤
ምክንያቱም ቤቱ ሁለት ብቻ በመ
ሆኑ ለጀማሪዎች በቀላሉ ለመግጠ
ም ይረዳቸዋል።

<u>ምሳሌ፡</u>–
ቀኖና ወጾም ለኢሳይያስ ውሉዱ
ተቀነዩ እንከ ለእግዚአብሔር አሃዱ

<u>ፍቹ</u>፡– የኢሳይያስ ልጆች ቀኖናና
ጾም ከእንግዲህ ወዲህ ለአንዱ
እግዚአብሔር ተገዙ።

### 2. ዘአምላኪየ ቅኔ

ይህ የቅኔ ዓይነት
ዘአምላኪየ የተባለው የአምላኬ ነገር
(ምሥጢር) እንደዚህ ዕፁብ ድንቅ
ነው ለማለት ነው።

ይህ ቅኔ ቤቱ ሦስት ነው፤
ይኸውም የሥላሴ ምሳሌ ነው፤ ቤቱ
ሳይፋለስ አንድ መሆኑ ደግሞ የአ
ንድነት ምሳሌ ነው። ዜማው ግን
ሁልጊዜ ዕዝል ብቻ ነው። በቤተክ
ርስቲያንም የሚደረሰው በጌታችን
ዐበይት በዓላት ጊዜ ነው።

ይህ የቅኔ ዓይነት ስሙ
ዘአምላኪየ የተባለበት ምክንያት
የቅኔው መጀመሪያ «አምላኪየ አም
ላኪየ እገይሥ ኀቤከ» (መዝ.62÷1)
የሚለው የዳዊት መዝሙር እየተዘ
መረ ስለሚደረስ ነው።

<u>ምሳሌ፡</u>–

እግዚአብሔር ክረምት ዘነብየ
ጽድቅ ሰብሖዎ
ዘይጠፍር በማየ ደመና ሐመልማል
ጽርሆ
ወላዕለ ፍጡራን ፈትሀ ድምፀ ቃለ
ዝናብ ፍትሆ

ፍቺ :- የእውነት ቃል ነቢይ ያመሰገነው እግዚአብሔር ክረምት ልምላሜ ቤቱን በደመና ውሃ ሠራው በፍጡራኑም ላይ የዝናብ ድምጽ ፍርድን ፈረደ

## 3 ሚ በዝኑ ቅኔ

የስሙ ትርጉም የሥላሴ ምሥጢራት ምንኛ እጅግ ይበዙ ማለት ነው:: እንደ ሁለተኛው የቅኔ ዓይነት ሁለተኛው ቤት መንደርደሪያ ይባላል::

ይህ የቅኔ ዓይነት ስሙ ሚ በዝኑ የተባለበት ምክንያት «እግዚኦ ሚ በዝኑ እለ ይሣቅዩኒ:: ብዙኃን ቆሙ ላዕሌየ» [መዝ.3÷1] በተባለው የዳዊት መዝሙር የሚነሣ ስለሆነ ነው:: ቅኔው በቤተክርስቲያን የሚደረስበት ሁልጊዜ እሑድ፣ በዐቢይ ጾምና በሌላው መወድስ በሚደረስበት ጊዜ ነው:: አንድም ሦስት ቤት መሆኑ አብ ልብ፣ ወልድ ቃል መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ሆነው ገለፁልኝ ማለቱ ነው::

ምሳሌ:-
ተክለ ሃይማኖት ትጉህ እመኳንንቲሁ
ኪሩቤል ምንተኒ ኢይንዕስ
እስመ ልብሰ ኪሩቤል ክንፈ ዘይለ
ብስዎ ይለብስ
ወዘይበልዕዎ ምግበ ስብሐተ ቅዳሴ
ይበልዕ እንበለ አርምሞ ተፅናስ

ፍቺ :- ትጉህ ተ/ሃይማኖት ከመኳንንቱ ኪሩቤል ምንም አያንስም እነሱ የሚለብሱትን የክንፍ ልብስን ይለብሳልና፤ የሚበሉትንም የምስጋና ቃል ምግብን ያለዝምታ ችግር ይበላልና::

## 4. ዋዜማ ቅኔ

ይህ የቅኔ ዓይነት በሰርክ የሚቀርብ (የሚደረግ) በመሆኑ የሠርክ መሥዋዕት ይባላል:: በየታላላቁ በዓላት በዋዜማው የሚቀኙት ቅኔ የሚገጥሙትም ግጥም የሚያቀርቡትም ምስጋና ነው::

ዋዜማ ቅኔ ረጅምና አጭር ዓይነቶች ሲኖሩት ረጅሙ አምስት ቤት ያለው ነው:: ይኸውም የአምስቱ አእማደ ምሥጢራት ምሳሌ ነው፤ ዜማው ግን አራራይ ነው:: አጭር ዋዜማ የሚባለው ደግሞ ሁለት ቤት ያለው ሆኖ ምሳሌው የትስብእትና የመለኮት ነው::

ምሳሌ:-
ተክለ ሃይማኖት ይቤሎሙ ለመላ
እክት ክብር ማኅበር በስመ አሃዱ
እብኖዲ
ደምሩኒ እማኅበርክሙ ቅዳሴ ነዐዲ
እስመ ጽዋአ ክብር ስብሐተ
ዘትፈድዩ እፈዲ
በዘኢአክሙ ሕግ እንበለ እጐንዲ
ወበዝንቱ ኢይዴሀር አዲ

ፍቺ :-ተ/ሃይማኖት የክብር መላእክት ማኅበርተኞችን በአንድ እግዚአብሔር ስም ወደ አማረ ማኅበራችሁ ምስጋና አስገቡኝ አላቸው:: እናንተ የምትከፍሉትን የክብር ምሥጋና እከፍላለሁና:: በእናንተ ሕግ ሳልዘገይ፤ ከእንግዲህም በዚህ ወደኋላ አልልም::

## 5. ሥላሴ ቅኔ

በሥላሴ ቸርነት ሦስተኛ ቅኔ ደረሰኝ ማለት ነው:: የዚህ ቅኔ ቤቱ ስድስት ነው:: ምሳሌውም የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ነው:: ዜማው ግን ሁልጊዜ ዕዝል ነው፤ ይኸንም ቅኔ የሚቀኙት በታላላቅ በዓላት ዋዜማ ጊዜና በክስተ አርአያም ጊዜ ነው::

ሥላሴ ቅኔ የሽማግሌዎች ወይም የዐዋቂዎች ቅኔ ነው እየተባለ ስለሚገመት የሚሰጠው በዕውቀት ለበሰሉ ሰዎች ብቻ ነው:: ሥላሴም የተባለበት ምክንያት «ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ...» በሚለው በጸሎተ ሰለሥቱ ደቂቅ ድርሰት እየገባ የሚነገር ስለሆነ፤ አምላከ አብርሃም፣ አምላከ ይስሐቅ፣ አምላከ ያዕቆብ እያለ ሦስትነትን የሚገልጠውን እየዘመሩ ስለሚጀምሩት ነው::

ምሳሌ :-
ምቅዋሞሙ ለመላእክት ሊቃውንተ
ክብር ደብረ ምጥማቅ
ዘመሰራቲሃ ክርስቶስ ኬንያ አንሶሳዌ
ታኅቱ ወላዕሉ
ማርያም መጽሐፈ ብርሃን ትትነበብ
ለኩሉ
እስመ ላዕሌሃ ተግህደ ለብርሃነ
ጽድቅ ጸዳሉ
ወከመ ያንብብዋ ለዘክሁሉ አንብቦ
ማርያም መጽሐፍ እንበለ ያብጥሉ
አዘዞሙ ሊቅነ በቃሉ

ፍቺ :- የክብር ሊቃውንት መላእክት የሚቆሙባት ወደታችና ወደላይ የሚመላለስ ጥበበኛ ክርስቶስ የመሠረታት ደብረ ምጥማቅ፤ ከደብረ ምጥማቅ ውስጥ መጽሐፈ ብርሃን ማርያም ለሁሉ ትነበባለች፤ በላዩዋ ላይ የእውነት ቃል ብርሃን ተገልጧልና:: ማርያም መጽሐፍንም ማንበብ ለሚችሉ ሳያስታጉሉ እንዲያነቧት ፈጣሪ በቃሉ አዘዛቸው::

## 6. ዘይእዜ ቅኔ

ይህ ቅኔ «ይእዜ ትስእሮ ለገብርከ» [ጸሎተ ስምዖን] በማለት የሚጀምር ስለሆነ 'ዘይእዜ' የሚል ስያሜን አግኝቷል:: ዘይእዜ ቅኔ አጭርም ረጅምም አለው:: የረጅሙ ዘይእዜ ቤት አምስት ነው፤ ይህም የአምስቱ አእማደ ምሥጢር ምሳሌ ነው:: ዜማው ግእዝ ነው:: አጭሩ ዘይእዜ ቤት ሦስት ብቻ ነው:: ስሙም ሣህልከ ይባላል:: የዚህኛው ዜማ ደግሞ አራራይ ነው:: ስሙንም ሣህልከ እያሉ የሚጠሩት 'ተሣሃለኒ እግዚኦ በከመ ዕበየ ሣህልከ' የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ስለሚጀምሩት ነው:: [መዝ. 50÷1]

በተጨማሪም ረጅሙ ዘይእዜ የሚደረሰው በታላላቅ በዓላት ዋዜማ ጊዜና በስብሐተ ነግህ አደራረስ ጊዜ ነው:: አጭሩ ግን መወድስ በሚደረስበት ጊዜ ብቻ ነው::

ምሳሌ:-
ታኅቴሃ ለኦም ኢትዮጵያ ምዕራፊ
ብዙሀን ጻድቃን ለተክለ ሃይማኖት
አህባሉ
ተሰቲሆመ ቅዱሳን ለጽዩን
ሐዋርያቲሃ ኅቡረ አጽለሉ
ወበጽላሎታ ሠናይ ርዕሰሙ ይኬልሉ
ላዕለ ፍና ሮሜ ነዊህ አምጣነ ወአሉ
ለአምስጦ ክህደት ዶሮሙ እንበለ
ያዕርፋ እሉ

ፍቺ :- የተ/ሃይማኖት ዘመዶች የሆኑ የበርካታ ቅዱሳን ማረፊያ በሆነች በኢትዮጵያ ዛፍ ስር ወደ ጽዮን የሚሄዱ ዘጠኙ ቅዱሳን አረፉ (ተጠለሉ):: በጥላዋም ራሳቸውን ጋረዱ:: እነርሱ ሳያርፉ ከጠላታቸው ክህደት ለማምለጥ ከረዘመው የሮም መንገድ ውለዋልና::

## 7. መወድስ ቅኔ

በዕለተ እሑድ የሚቀርብ ምስጋና ነው:: ይህ ቅኔ ሁለት ዓይነት ሲሆን የመጀመሪያው ፍታሕ ሊተ የተባለው ነው:: ይህ የመወድስ ቅኔ ዓይነት ቤቱ ስምንት ሲሆን ይህም የስምንቱ ብሔረ አሪት ምሳሌ ነው:: ዜማው አራራይ ነው:: ፍታሕ ሊተ የተባለበት ምክንያት ፍታሕ ሊተ እግዚኦ እስመ አንሰ በየውህትየ አሐውር [መዝ.25÷1] የሚለው የዳዊት

መዝሙር እየተዘመረ ስለሚጀመር ነው::

ሁለተኛውም ኲልክሙ የተባለው ሲሆን፤ ቤቱም ዘጠኝ ነው:: ምሳሌውም የዘጠኙ ሐፀ-ረ መስቀል ምሳሌ ነው:: ኲልክሙ የተባለበትም ምክንያት 'ኲልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ' የተባለው መዝሙር እየተዘመረ ስለሚጀመር ነው::

ሁለቱም መወድሶች በተለይም ኲልክሙ ለሽማግሌ ሰው ተመርጦ የሚሰጥ ቅኔ ነው፤ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ወይም በተለይ በታወቀ በዓል ለቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ (አለቃ) የሚሰጥ ቅኔ ነው::

8. ክብር ይእቲ

ይህ ቅኔ የጌታችንን ነገረ ስቅለት የሚያስታውስ፣ በዕለተ ዓርብ ለሰው ልጆች የከፈለውን መሥዋዕትነት የሚያዘክር፣ የተቀበለውን ፀዋትወ መከራ የሚናገር ነው:: በመሆኑም እንደ መርዶ ስለሚቆጠር ሲቀኝም በጣም በለሆሳስ ነው:: ስሙን ክብር ይእቲ ያሉት 'ክብር ይእቲ' [ መዝ.149] የሚለው መዝሙር ከዚህ ጋር ስለሚዘመር ነው::

<u>ምሳሌ</u>:-

ጠቢበ ዓለም ክርስቶስ ለጥበበ ዓለም ዘሀተቶ ፤

ገዳመ ቀራንዮ ጌሠ እንዘ ያነስዕ ኲናቶ ፤

ለህሙመ ፍዳ አዳም እሁብ ዘፍን ተትህቶ ፤

ጊዜ ዕለታ ለዓርብ አምጣነ ይከርያ መድኃኒቶ::

<u>ፍቺ</u> :-

የዓለምን ጥበብ የመረመረ የዓለም ጥበበኛ ክርስቶስ ጦሩን ይዞ ወደ ቀራንዮ ዱር ገሠገሠ ከውርደት ጋራ በፍዳ የተያዘ ለበሽተኛ አዳም በዓርብ ቀን መድኃኒት ይቆፍራልና::

9. ዕጣነ ሞገር ቅኔ

ዕጣነ ሞገር ማለት ማሳረጊያ፣ መደምደሚያ፣ መጨረሻ ማለት ነው:: በመሆኑም ዕጣነ ሞገር ከተቆመ በኋላ ምንም ዓይነት ጸሎትም ሆነ መዝሙር አይደረግም::

ዕጣነ ሞገር የተባለው የቅኔ ዓይነት ሁለት ነው:: እርሱም ግእዝ ዕጣነ ሞገር ሰባት ቤትና ዕዝል ዕጣነ ሞገር አሥራ አንድ ቤት ነው:: ሁለቱም የዕጣነ ሞገር ዓይነቶች ትልልቅ የሆኑ ሁለት ክፍል አላቸው:: ይኸውም እስከ መንደርደሪያው ያለው የሁለቱም ቅኔዎች ግጥም በዓሉን ወይም ዕለቱን የሚመለከት ሲሆን፤ ከመንደርደሪያው ጀምሮ ያሉ ግን ስሙም አሠረ ንጉሥ ይባላል፤ የሚሰጠውም ለንጉሥ ክብር ብቻ ነው:: ማለትም ምስጋና ታሪክ ሌላም ሁናቴ ቢሆን የንጉሥንና የታላላቅ ሰዎችን ሁናቴ የሚገልጥ ክፍል ነው::

<u>ምሳሌ</u> :-

ሳይዳ ሕላዌ ዓለም እንዘ ትብል እነ ብር ወእሄስ በመዐዛ ፋኒኤል ጽጌረዳ ፤

ምዑዘ ምዑዛን ኪሩቤል ነገሥተ በረከት ወጋዳ ፤

ነፋሳቲሃ ለአዜብ ሕማማቲሃ ለፍዳ ፤

ቀሰፍዋ እንበለ ዕድሜሃ ለዓለም ሳይዳ ፤

ለቤተክርስቲያን እምነ ሊቃውንት ስርጉዋነዘያሬድ ከለሜዳ ፤

ያስተፌስህዋ ዘልፈ በፈጽሞ ቃለ ሃይማኖት ፈቃዳ ፤

ወጽኑአ ግብረ ተዋሕዶ ውስተ ዐውዳ::

<u>ፍቺ</u> :- የመኖር እመቤት ዓለም ምዑዛን ክብር የሆኑ የበረከትና የእጅ መንሻ የሆኑ ኪሩቤል ዘንድ መዐዛ ያለው ፋኑኤል ጽጌረዳ መዐዛ ፈጽሜ እኖራለሁ ስትል፤ የአዜብ ነፋሳት የፍዳን ሕማማት ያለዕድሜ ዓለም ሊቃውንት እናታችን ቤተክርስቲያንን የሃይማኖት ቃለ ፈቃዷን በመፈጸም ጽኑ የሆነ የአንድነት (የተዋሕዶ) ሥራን በመፈጸም ከአደባባይዋ ደስ ያሰኟታል:: ዘወትር ደስ ያሰኟታል::

*የቅኔ ክፍሎች*

ከላይ ከተገለጹት የቅኔ ዓይነቶች በማንኛውም የቀረበ አንድ ቅኔ የራሱ የሆኑ ክፍሎች አሉት:: እነዚህም የቅኔ ክፍሎች ስድስት ሲሆኑ እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን::

1. *ሐረግ*፦ አንድን ቅኔ የሚመሠርቱ እያንዳንዱ ዐ.ነገሮች (ስንኞች) ሐረግ ይባላሉ::

2. *መንደርደሪያ*፦ ከዘጠኙ የቅኔ ዓይነቶች የዘአምላኪየ፣ የዋዜማ፣ የሥላሴና የዘይእዜ ሁለተኛው ቤት፤ የመወድስ ደግሞ ሦስተኛው ቤት፤ እንዲሁም የግእዝ እጣነ ሞገር፣ አራተኛውና የዕዝል ዕጣነ ሞገር ደግሞ ስድስተኛው ቤት ነው:: የቀሩት የቅኔ ዓይነቶች መንደርደሪያ የላቸውም:: [' ቤት' ስንል ዐ.ነገር ወይም ስንኝ ማለታችን ነው:: ]

3. *ቧኄ*፦ ከዘጠኙ የቅኔ ዓይነቶች መወድስ የተባለው ቅኔ አራተኛው ቤት ሲሆን የቀሩት የቅኔ ዓይነቶች ቧኄ የላቸውም::

4. *ለዓለም*፦ ይኸም እንደ ቧኄ ሁሉ በመወድስ ብቻ የሚገኝ ክፍል ሲሆን የመወድስ ስድስተኛው ቤት ነው::

5. *መጽፈያ*፦ የዋዜማ፣ የሥላሴና የዘይእዜ አራተኛው የመወድስ ዘጠነኛው፣ የግእዝ እጣነ ሞገር ሰባተኛው፣ የዕዝል እጣነ ሞገር ዘጠነኛው ቤት ነው:: የቀሩት የቅኔ ዓይነቶች ግን መጽፈያ የላቸውም::

6. *ሆኅ*፦ በየትኛውም ቅኔ ቤት ከመምታቱ በፊት የሚገኝ ቤት ወይም ሐረግ ነው::

*የቅኔ መንገድ*

*ይቀጥላል*

<u>ፍቅር</u>

እውነት መሠረቱ

መተዛዘን ፍሬው

ትዕቢትን ይጠላል

አመጽም ደስ አይለው

መታገስን እንጂ

ብስጭት አያውቅም

ፀንቶ ይጠብቃል

ተስፋ አያስቆርጥም

ከቅናት ውል የለው

እኔን ብቻ ይድላኝ

በአድመኝነት ቦታ

ኩቶውን አይገኝ

የምግባር ምሰሶ

የሃይማኖት ውጤት

ማሰሪያ ልጣቸው

የአንድነት ምልክት::

1ኛ.ቆሮ.13፥4–7

*ሱነማዊት(ከ6 ኪሎ)*

# ከሊቃውንቶቻችን

## ፈላታዎስ መምህር ዘእርባዕቱ ጉባኤያት

መምህር ፈላታዎስ በጎጃም ክፍለ ሀገር መርጡለማርያም አካባቢ በ1863 ዓ.ም ተወለዱ:: የቤተክርስቲያንን ትምህርት ገና በልጅነታቸው ነው የተያያዙት:: በተወለዱበት አካባቢ ጸዋት ደግመው ጸዋትወ ዜማን በየመልኩ ተምረዋል:: ለቀጣዩ ትምህርታቸውም እንዲበጃቸው ከቅኔ ቤት ገብተው ከተማሩ በኋላ ጥልቅና ምጡቅ የሆነውን የብሉያት ትርጓሜ ለመማር ፅላሎ ወደ ሚባለው ቦታ ሄዱ::

ከመምህር ወልደማርያም የ46 ቱን መጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ደብረወርቅ ዘልቀው ከመምህር ሰው አገኘሁ ብሉያቱን ደግመዉ ከለሱ:: የአንድን መምህር የትርጓሜ ስልት ከሌላው ጋር ለማስተያየትና ለማመቻቸት ያመቻቸው ዘንድ ለሦስተኛ ጊዜ ጐርማ ቅዱስ ሚካኤል ከሚባለው ደብር ከነበሩት አለቃ ገብረ ኤልያስ ብሉያቱን አጠናከሩ፡

መምህር ፈላታዎስ እንደቀደሙት አባቶቻቸው ሁሉ በዚሁ በቃ አላሉም:: አድካሚና ትዕግስት የሚጠይቀውን የሐዲሳት ትርጓሜ ከታዋቂው መምህር ከአለቃ ጎናይ ፈንታ በሚገባ አጥንተዋል:: አያይዘውም ወደ ወሎ ክ/ሀገር ዘልቀው ከመምህር አካለ ወልድ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና ሃይማኖተ አበው፣ ፍትሐ ነገሥት፣የመጻሕፍተ መነኩሳትን ትርጓሜ በመማር የአራቱ ጉባኤ መምህር ሆኑ::

ፈላታዎስ ዕድሜያቸውን በመማር ብቻ የፈጸሙ አልነበሩም:: ከተለያዩ መምህራን የቀሰሙትን ትምህርት ለራሳቸው ብቻም ይዘው አላስቀሩትም:: ከመሰሎቻቸው ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ጋር በመተባበር የመጻሕፍተ ብሉያትን የአንድምታ ትርጓሜ ጽፈው እንዲታተም አቅርበው ነበር:: ከዚህም በተጨማሪ በወቅቱ በነበረው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ት/ቤት ተመድበው መጻሕፍተ ብሉያትን በማስተማር ታላቅ አገልግሎት ለእናት ቤተክርስቲያናችን አበርክተዋል:: ከዚሁ ት/ቤት እነ ዶክተር አለቃ አየለ ዓለሙን የመሳሰሉትን አፍርተዋል:: በኋላም ወደተወለዱበት አካባቢ ተመልሰው በመርጡለማርያም ደብር በመምህርነት ተመድበው አስተዳድረዋል::

መምህር ፈላታዎስ መላ ዘመናቸውን ለመማር፣ ለማስተማር፣ መጻሕፍት ለመተርጎም የተለያዩ መንፈሳዊ ግልጋሎቶችን ለቤተክርስቲያን በማበርከት የኖሩ አባት ናቸው:: ሐምሌ 3/1942 አርፈው በመርጡለማርያም ደብር ቢቀበሩም ሥራቸው ግን ዛሬም በቤተክርስቲያን ያበራል::

ፈላታዎስ የሚለውን ስም ያገኙት ከመምህራቸው ከአካለ ወልድ ሲሆን የቀደመ ስማቸው «ፍላቴ» ይባል ነበር::

*ትንሣኤ መጽሔት*
*ቁጥር 32/ግንቦት 1972 ዓም*

## እግዚአብሔርን እናመስግነው

ከዛሬ 800 ዓመት በፊት እነዚያ ደጋግ አባቶቻችን ደክመው ለፍተው ያኖሩልን ታላቅ ቅርስ ማንነቱን በማያውቅና ራሱን ለገንዘብ አሳልፎ በሸጠ ደካማ ሰው ተሰርቆ የነበረው የአባታችን የቅዱስ ላሊበላ መስቀል በእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ተሰርቆ ከሄደበት ከቤልጅየም አገር መጥቶ ወደ አገረ ክብሩ እግዚአብሔር አምላካችን መልሶልናልና በእውነት እግዚአብሔርን እናመስግነው::

*ተፈሪ አርጋው(ኮልፌ)*
*ወለተማርያም (አምቦ)*

## በማስተዋል ይሁን

አባቶቻችን ዘመናት ለማይሽሩትና ለዘላለም ፀንቶ ለሚኖረው ቃሉ በንባብም ጊዜ ሆነ በሚያዜሙበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ:: ነገር ግን አሁን አሁን በብዙ ሰንበት ት/ቤቶች ተማሪዎች በጉባኤ ላይ ሥነ ጽሑፍ በሚያነቡበት ጊዜም ሆነ በሚዘምሩበት ጊዜ ትክክለኛውን አባባል አባቶችን ካለመጠየቅ የተነሣ ብዙ ስህተቶችን ሲፈጽሙ ይታያሉ:: ለምሳሌ «ኃጢአት» የሚለውን ቃል «ኃጺያት» በማለት ያነቡታል ወይም ያዜሙታል:: ስለ ዚህ እባካችሁ አባባሉን ከአባቶችና ከቤተክርስቲያን ሊቃውንት እንጠይቅ:: «አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል፤ ሽማግሌዎችህን ጠይቅ ይነግሩህማል» ዘዳ. 32÷7 ይላልና የእግዚአብሔር ቃል:: ስለዚህ አባባሉን እናስተውል:: ስንዘምርም በማስተዋል ይሁን:: ዜማው ደስ ብሎንና በስሜት እንዳይሆን እንጠንቀቅ::

*ዲ.ፈንታሁን አበበ*
*አዋሽ መልካ ደ/ብ/ቅ/ገብርኤል*
*ሰ/ት/ቤት*

*ማስታወቂያ*

*ከዚህ ቀደም አራት በአማርኛና በግእዝ እንዲሁም አንድ በኦሮምኛ ቋንቋ የተዘጋጁ የመዝሙር ካሴቶችን ያቀረበው የማኅበረ ቅዱሳን መዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለመጀመሪያ ጊዜ በትግርኛ ቋንቋ ያዘጋጀው ያሬዳዊ መዝሙር በቅርቡ በገበያ ላይ ይውላል::*

*በዚህ እትም ከሰይጣን ጋር የምናደርገውን ቃለ ምልልስ እንደምናቀርብ ቃል ገብተን ነበር:: ነገር ግን ከአንባብያን ጥያቄዎች ብዛትና ሌሎች ችግሮች የተነሣ በዚህ እትም ማቅረብ አልቻልንም:: ስለዚህ አንባብያንን ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥለው እትም ይዘን እንደምንቀርብ ቃል እንገባለን!*

## ችግርዎ ምንድነው?

* ትዕቢት ከሆነ ጐልያድ ወይም ሰናክሬም የት እንደወደቁ ይፈልጓቸው
* ተጠራጣሪ ከሆኑ ወደ ሀናኒያና ሰጳራ ጉዞ እንደጀመሩ ያስተውሉ
* በብድር ወይም በዕዳ ከተያዙ ነቢዩ ኤልሳዕን ያማክሩት
* በደዌ ሥጋ ከተለከፉ እንደ መጻጉ በመጠመቂያው ወይም በቤተመቅደስ ደጅ ይጥኑ
* በባዕድ ሀገር ስደተኛ ከሆኑ ከያዕቆብ ልጅ ከዮሴፍ ጋር ጥቂት ይጨዋወቱ
* የዕለት ጉርስ ቢያጡ በአብርሃም እቅፍ የገባውን አልአዛርን ይጠይቁት

ከሁሉም ከሁሉም የኃጢአት ዕዳ ወይም የነፍስ ደዌ እንዳይኖርብዎ ራስዎን በካህኑ ያስመርምሩ ለሥጋዎ በረከትን በነፍስዎም የዘላለም ሕይወት ያገኛሉና::

ሐምሌ 5 ቀን 1991 ዒ.ም. 16 ቆሞሳት በኤጳስ ቆጶስነት ተሹመዋል:: ሥርዓተ ሲመቱን በሚመለከት በስምዐ ጽድቅ 6ኛ ዓመት ቁጥር 10 እትማችን አቅርበናል:: ስዚህ ደረጃ የበቁት አባቶቻችን መልካም የሥራ ና የአገልግሎት ዘመን እንዲሆንላቸው በልጅነት እንደበት እንመኛለን::

| የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደምበኞች ይሁኑ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
| | የ 6 እትም | የ12 እትም | የ6 እትም | የ12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 10.00 | 20.00 | 18.70 | 37.40 |
| የክፍለ ሀገር | 10.50 | 21.00 | 19.00 | 38.40 |
| ከኢትዮጵያ ውጭ | 9 ዶላር. | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |

አድራሻዎንና የከፈሉበትን ማስረጃ
ለአቶ መስፍን ተ/ዮሐንስ ተሻለ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ
የባንክ ሂሳብ ቁጥር 75282 አዲስ አበባ ብለው
በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን::

# በ ማ ኅ በ ረ   ቅ ዱ ሳ ን

## ሐመርና ስምዐ ጽድቅ ማከፋፈያዎች

- ሐመር መጽሔት
- ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ
- መለከት መጽሔት
- የመዝሙርና ስብከት ካሴቶች
- መንፈሳዊ ፖስት ካርዶች
- የጸሎትና የትምህርት መጻሕፍት
- ቅ. ሥዕላት

በጅምላና በነጠላ ያገኛሉ

በተጨማሪም የካሴት ቅጅ አገልግሎት እና ለማንኛውም የመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓቶች የቪዲዮ ቀረጻ አገልግሎት እንሰጣለን፡፡

**አድራሻችን፡—**

⇨ አዲስ አበባ

❖ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ወደ አፄ ናዖድ ት/ቤት በሚወስደው መንገድ በስተግራ

❖ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ወደአዲሱ ገበያ በሚወስደው መንገድ በስተግራ 100 ሜትር ገባ ብሎ

⇨ በክፍለ ሀገርም

| | | |
|---|---|---|
| ✸መቀሌ | ✸ጎንደር | ✸ባሕርዳር |
| ✸ጅማ | ✸ጋምቤላ | ✸ አዋሳ |
| ✸አርባ ምንጭ | ✸ነቀምት | ✸ድሬዳዋ ያገኙናል፡፡ |

እንዲሁም
በማኅበሩ የንዋያተ ቅድሳት ማከፋፈያ ማዕከል

የካህናት አልባሳት ፣

የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ልብስና

ንዋያተ ቅድሳትን

እናከፋፍላለን፤ በትእዛዝም እናዘጋጃለን ፤

ለተክሊል ተጋቢዎችም ካባዎችን እናከራያለን

በተመጣጣኝ ዋጋ ጥሩ ሥራ ለማሠራት ወደኛ ይምጡ
ከገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ /አራዳ ጊዮርጊስ/ ቤተክርስቲያን ወደ 6 ኪሎ አደባባይ በሚወስደው መንገድ ከመቅደላ ሆቴል አጠገብ፡፡

ስልክ 128460
ፖስታ 80078

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው።